# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

## *በብሔራዊ የተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም*

# የ1991ዓ.ም ሀገር አቀፍ የሰው ኃይል ጥናት

# የመረጃ ሰብሳቢዎች መመሪያ

አዲስ አበባ
የካቲት 1991

# ምዕራፍ 1

## መ ግ ቢ ያ

የሰው ኃይል ስታቲስቲክስ መረጃዎች ለአንድ ሀገር የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የልማት ዕቅዶችን ለመንደፍ፣ ስለ አፈፃፀማቸው ለመከታተልና አስፈላጊ የፖሊሲ እርምጃዎችን ለመውሰድ መሠረታዊ በመሆናቸው በየወቅቱ እንዲሰበሰ ቡ ያስፈልጋል። የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣንም ከዚህ መሠረታዊ ዓላማ በመነሳት በአገር አቀፍ የተቀናጀ ሰርቬ ይ ፕሮግራም ሥር በ1973 እና በ1980 ዓ.ም የገጠር የሰው ኃይል ጥናት አካሂዶ ነበር። እንደዚሁም በ1976 እና በ19 87 ዓ.ም. በተካሄዱት ሁለት የሕዝብና ቤት ቆጠራዎች የሰው ኃይልን የሚመለከቱ መረጃዎች ተሰብስበዋል። የሰው ኃ ይል መረጃዎችን ወቅታዊ ለማድረግና ከሁለቱም ቆጠራዎች የበለጠ ጥልቀት ያለው መረጃ ለማግኘት እንዲረዳ እንዲሁ ም የከተማና የገጠሩን አካባቢ በአንድነት ያጠቃለለ ጥናት ማካሄድ በማስፈለጉ በ1991 ዓ.ም. ሀገር-አቀፍ የሰው ኃይል ጥናት ለማካሄድ ታቅዷል።

### <u>የጥናቱ ዋና ዋና ዓላማዎች፣</u>

1. ሀገሪቱ ያላትን ለሥራ የደረሰ የሰው ኃይል መጠን፣ የሥራ ስምሪቱንና ሥርጭቱን የሚያሳይ ስታትስ ቲካዊ መረጃ ለማቅረብ፣

2. በወቅቱ ሥራ የሌላቸው ሰዎችን መጠን፣ የሥራ ፍላጎታቸውን፣ ለሥራ ዝግጁነታቸውን፣ በሥራ አጥነት የቆዩበትን ጊዜ እና ተዛማጅ ባህርያትን የሚያሳይ መረጃ ለማስገኘት፣

3. የሀገሪቱን የሰው ኃይል አቅርቦት መጠን፣ ጥቅም ላይ ሊውል ከሚችለው የሰው ኃይል ምን ያህሉ ለሀ ገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት እገዛ እያደረገ እንደሆነ ወይም ደግሞ ምን ያህሉ ጥቅም ላይ ሳይውል እየባከነ እንደ ሆነ ሊጠቁም የሚችል መረጃ ለማስገኘት፤

4. ለሥራ ያልደረሱ ልጆችን በሚመለከት ተገቢ የፖሊሲ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችሉ በሥራ ስ ለመሰማራት ሁኔታዎች የሚያመለክቱ መረጃዎችን ለማስገኘት፤

5. በሥራ ሊሠማራ ስለሚችለው የሰው ኃይል ዋና ዋና የዲሞግራፊያዊና የማህበራዊ ባህሪያት መረጃ ለማስገኘት፤

6. በሀገሪቱ በየወቅቱ ስለሚካሄዱ የሙያና ፕሮፌሽናል/ ቮኬሽናል /ቴክኒካል/ ስልጠና በተመለከተ የስል ጠናው ዓይነትና ተዛማጅ መረጃዎችን ለማስገኘት፣

7. ከጥናቱ ዓመት በሁዋላ በሚቀጥሉት ዓመታት የሀገሪቱን የሰው ኃይል መጠን፤ የሥራ ስምሪቱን፤ ... ወዘተ አስመልክቶ ትንበያ /ግምት/ ለማስላት የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማስገኘት፤

8. በሥራ ስምሪት ረገድ በተለያዩ ምክንያቶች በሥራ የመሠማራት ዕድላቸው ዝቅተኛ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን (ሴቶችን) አስመልክቶ ጠቅለል ያሉ የሥራ ባህርያት መረጃዎችን ለማስገኘት፤

### <u>በጥናቱ የሚሰበሰቡ መረጃዎች አይነት</u>

በአሁኑ ጊዜ በሚካሄደው የሰው ኃይል ጥናት የሚከተሉት መረጃዎች ይሰበስባሉ፤

- የዲሞግራፊና ማህበራዊ መረጃዎች፡- ዕድሜ፣ ጾታ፣ የፍልሰት ሁኔታ፥ የጋብቻ ሁኔታ፥ የትምህርት ደረጃ ና የስልጠና አይነት፣
- ባለፉት 12 ወራት በስራ የመሠማራት ሁኔታ፣
- ባለፈው 7 ቀናት በስራ የመሠማራት ሁኔታ፡- በየዕለቱ የሠሩት የሥራ ሰዓት ብዛት፣ በስራ ላልተሰማሩት ምክንያት፣ በስራ ለተሠማሩ የሥራ አይነት፣ የድርጅቱ ምርት ወይም አገልግሎት አይነት፣ የቅጥር ሁኔታና አይነት፣
- ስለ ሥራ አጥነትና የሥራ አጥነት ባህርያት፣
- ለሥራ ያልደረሱ ልጆች (ዕድሜአቸው ከ5-14 ለሆናቸው) ማህበራዊ አቋምና በምን ተግባር ላይ ተሰማር ተው እንደሚገኙ፡- ትምህርት የመማር ሁኔታ፣ በስራ ስለመሰማራት፣ በሥራ ላይ ስለደረሱ ጉዳቶች፣ የልጆ ች እናት/አባት በህይወት ስለመኖር፣

ከላይ በተመለከተው መሠረት የሚገኘው መረጃ ከሌሎች የሰው ኃይል መረጃ ምንጮች ጋር በመዛመድ የሰው ኃይሉን ብዛትና ሌሎች ባህርያት፣ በየጊዜው የሚታዩትን ለውጦች ጭምር ለማወቅ እንዲያስችሉ ይደረጋል። ከዚህም በመነሳት በመጪዎቹ ዓመታት ሊኖር የሚችለውን የሰው ኃይል ብዛት ለመገመትና ሌሎች የሰው ኃይል የሥራ ስምሪት ሁኔታዎችን ለማወቅ ይቻላል።

## ጥናቱ የሚካሄድበት ጊዜ

የ1991 የሰው ኃይል ጥናት በሁለት ዙሮች የሚካሄድ ሲሆን የመጀመሪያው ዙር ጥናት በመጋቢት ወር 1991፣ ሁለተኛው ዙር ጥናት ደግሞ በነሐሴ ወር 1991 ለማካሔድ ታቅዷል። በጥናቱ የሚገኙትን መረጃዎች በጠቅላላ በአን ድ ላይ ለማጣመር እንዲቻልና ከየሥፍራው የሚገኙትንም መረጃዎች ለማስተያየት/ለማወዳደር እንዲያመች ጥናቶቹ በ ተመረጡት የቆጠራ ቦታዎች በተመሳሳይ ወቅት እንዲካሄዱ ይደረጋል። በተጨማሪም በየዙሩ የሚካሄዱ ጥናቶች ጥናቱ ከተጀመረ በኋላ ባሉት ሰባት ቀናት ውስጥ መረጃዎች ሁሉ ተሰብስበው መጠናቀቅ ይኖርባቸዋል። በሰባቱ ቀናት ውስ ጥ መረጃው ተሰብስቦ ካላለቀ፣ በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ውስጥ በተቻለ ፍጥነት ተሰብስበው እንዲጠናቀቁ ያስፈልጋል፡ ፡ ነገር ግን በመጠይቁ ግርጌ ላይ ለምን መጠይቁ በተጠቀሱት ሰባት ቀናት ውስጥ ሊጠናቀቅ እንዳልቻለ ምርመራ በሚ ለው ሥፍራ ላይ መገለጽ ይኖርበታል። የመጀመሪያው ዙርና የሁለተኛው ዙር ጥናት መጠይቆች ተሞልተው እንዲጠና ቀቁ የተወሰኑበት ቀን እንዲሁም የናሙና አመራረጡ ዘዴና አሠራሩ በተለየ መመሪያ ይገለፃል። _

## የመረጃ ሰብሳቢዎች ተግባርና ኃላፊነት

1.

መረጃ ሰብሳቢው ለጥናቱ ስራ መሳካት ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረው ይታወቃል። ስለሆነም የመረጃ መሰብሰቡን ተግባር በቅንነት፣ በታማኝነትና በታታሪነት ማከናወን ይገባዋል። መረጃ ሰብሳቢው ለሰው ኃይል ጥ ናት መረጃ ለመሰብሰብ ወደ ተመረጠው ቤተሰብ በሚደርስበት ወቅት ለቤተሰቡ ሰላምታ በመስጠትና ስለመጣ በት አላማ በመግለጽ የመረጃ መሰብሰቡን ተግባር መጀመር ይኖርበታል።

2.

መረጃ ሰጭዎችን በሚቀርቡበት ጊዜ ወደ መጠይቁ ከመግባት አስቀድሞ ስለተለያዩ ጉዳዮች /ስለወቅ ቱ ሁኔታ፣ ስለእርሻው፣ ስለጤናቸው፣ ስለልጆቻቸው ... ወዘተ/ መጠያየቅ ከመረጃ ሰጪዎች ጋር መቀራረብንና መግባባትን ስለሚፈጥር በዚህ መልክ የመረጃ መሰብሰቡን ሥራ መጀመር ያስፈልጋል። ይኸም መረጃ ሰጪዎ ች መልሶችን ለመስጠት የበለጠ ዝግጁ ስለሚያደርጋቸው መጠይቁን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመሙላት ይረዳል።

3.

ትክክለኛ መረጃ የሚገኘው መልስ ሰጪዎችን አግባብ ባለው መንገድ በመቅረብ፣ አስነዋሪ ከሆኑ ድርገ ቶች በመቆጠብ፣ መረጃ ሰጪዎችን ከማመናጨቅ፣ ንቀት ከማሳየት፣ ከመጸየፍ ... ወዘተ በመታቀብና ረጋ ብሎ ና ሳያቻኩሉ በማዳመጥ እና በመሳሰሉት ድርጊቶች ነው።

ከሰው ኃይል ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች የሚጠበቀውን ጥቅም እንዲያስገኙ ለማድረግ በከፍተኛ ጥንቃቄና ጥራት ባለው ሁኔታ መረጃዎችን መሰብሰብ ከመረጃ ሰብሳቢዎች ይጠበቃል። ጥራት ባለው መረጃ ላይ የተመረኮዙ ዕቅ

ዶች በትክክል በተግባር መፈጸም ሲቻል በአንፃሩ የመረጃው ጥራት የማያስተማምን በሚሆንበት ጊዜ ዕቅዶችን ተግባራዊ
በማደረግ ረገድ ችግር ይገጥማል፡፡ ለምሳሌ ፕሮጀክቶች ተቀይሰው በሥራ ላይ ለማዋል በሚያስፈልግበት ጊዜ እንደየፕ
ሮጀክቶቹ አይነት አስፈላጊና ተገቢውን የሰው ኃይል ለማግኘት ከሰው ኃይል ጥናት የሚገኙ መረጃዎች ከፍተኛ ጠቀማ
ታ አላቸው፡፡ በመሆኑም ለየፕሮጀክቶቹ በቦታ፣ በዕድሜ፡በፆታና በመሳሰሉት ባህርያት ላይ የተመሠረተ ትክክለኛ መረጃ
ከሌለ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ማድረግ ከማዳገት አልፎ የተሳሳቱና የታዛቡ አሠራሮችን ይፈጥራል፡፡ ስለዚህ ጥናቱ በማ
ካሄድበት ወቅት ለመልስ ሰጪዎች የሚቀርቡትን ጥያቄዎች በመመሪያው መሠረት በማቅረብና ከዚያም የሚገኘውን ት
ክክለኛ መልስ በተገቢው ሥፍራ/ዓምድ/ በጥንቃቄና ጥራት ባለው ጽሑፍ በማስፈር መጠይቁን ለመሙላት ከፍተኛ ት
ኩረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በሰው ኃይል ናሙና ጥናት የተካተቱ መረጃዎች በአብዛኛው የቤተሰብ አባላትን ግላዊ ህይወት የሚመለከቱ እ
ና አስቀድሞ ስለተከናወኑ ወይም እየተከናወኑ ስላሉ ክስተቶች የሚጠይቁ በመሆኑ በተቻለ መጠን መረጃዎችን የሚመለ
ከታቸው የቤተሰብ አባላት ባሉበት መሰብሰቡ የመረጃውን ጥራት ከፍ እንደሚያደርገው ይታመናል፡፡

በመሆኑም የሚሰበሰቡት መረጃዎች የበለጠ ጥራት እንዲኖራቸው አብዛኞቹ የቤተሰብ አባላት ባሉበት፣ በቤተሰ
ብ ኃላፊው አማካይነት መረጃ መሰብሰብ አለበት፡፡ ኃላፊው ካልተገኘ እሱ በሚገኝበት ሌላ ጊዜ ተመልሶ በመምጣት
መጠይቁን መሙላት የሚያስፈልግ ሲሆን ኃላፊውን ማግኘት ካልተቻለ ግን መልስ ሊሰጥ የሚችል አዋቂ የሆነ የቤተሰ
ብ አባልን በማነጋገርና ጥያቄዎቹን በማቅረብ መጠይቁ ይሞላል፡፡ <u>በምንም ዓይነት መንገድ ጎረቤት የሆኑ ግለሰቦችን ብቻ
በማነጋገር መጠይቁ መሞላት የለበትም ፡፡</u> በተጨማሪም መጠይቁ በሚሞላበት ጊዜ አንዳንድ መረጃዎችን ለማግኘት ካ
ልተቻለ ወደ ቤተሰቡ በሌላ ጊዜ በመመለስ መረጃውን የመሰብሰብ ተግባር መጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡

መረጃው ተሰብስቦ ካለቀ በኋላ ከቤተሰቡ ከመሰናበት አስቀድሞ ስለቤተሰቡ አስፈላጊው መረጃዎች በትክክል ተ
ሰብስቦ መጠናቀቁን ማረጋገጥ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ መረጃው በሚሰበሰብበት ወቅት ተፈጽመው የነበሩ ስሕተቶች እዚ
ያው ከታረሙ በኋላ መረጃ ሰጭዎችን ከመሰናበት በፊት ማመስገንም መዘንጋት የለበትም፡፡ በዚያው ቀን የመረጃው ጥ
ራት እንደገና ታይቶ ከተረጋገጠ በኋላ ቀንና ስም ተጽፎ መፈረም ይኖርበታል፡፡ የመረጃው ጥራት በዚያው ቀን መረጋ
ገጥ የሚኖርበት ብዙ ቀናት ካለፉ መረጃውን ተመልሶ ከቤተሰቡ ለማግኘት ስለሚያስቸግር ነው፡፡ በተጨማሪም የተደረገ
ው ቃለ መጠይቅ ስለሚረሳ መረጃዎቹን ለማረም አዳጋች ይሆናል፡፡

የ1991 የሰው ኃይል ጥናት በሀገር አቀፍ ደረጃ በከተማና በገጠር የሚካሄድ ሲሆን በተለይ በገጠር ጥናቱ በገ
በሬ ማህበሩ ነዋሪ ከሆኑ በዕጣ በተመረጡ በእርሻ ሥራ ላይ የተሠማሩና በእርሻ ሥራ ላይ ባልተሠማሩ ቤተሰቦችን ይመ
ለከታል፡፡ ጥናቱ ስለሚሸፈናቸው ቤተሰቦች አመራረጥ የተሰጠው መመሪያ በትክክል መፈፀሙንና እንዲሁም ለጥናቱ
ከተመረጡ ቤተሰቦች ሁሉ መረጃዎቹ በወቅቱ የተሰባሰቡ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡

# ምዕራፍ 2 የመመዝገቢያ ቅጾች አሞላል መመሪያ

ጥናቱ በገጠር በሚካሄድበት ጊዜ የቤተሰቦች ምዝገባ አይደረግም። ይህም የሆነበት ምክንያት_ቀደም ሲል በ1990 የግብርና ጥናት በገጠር ቆጠራ ቦታዎች የቤተሰቦች ምዝገባ ሲካሔድ ለሰው ኃይል ጥናትም እን ዲያገለግል ተደርጎ የምዝገባ ቅጹ (ቅጽ 90/0) በመዘጋጀቱ ነው። ስለሆነም በገጠር ለሰው ኃይል ጥናት የሚ ያስፈልጉ ቤተሰቦች አዲስ ምዝገባ ሳያስፈልግ በቅጽ 90/0 ክፍል 2 ዓምድ 1ን በመጠቀም እንዲመረጡ ይደ ረጋል። ነገር ግን ለከተሞች በተዘጋጀው የቤተሰቦች መመዝገቢያ ቅጽ (ቅጽ 91/0) እና ከታች በቀረበው የአ መዘጋገብ መመሪያ መሠረት የቤተሰቦች ምዝገባ በተመረጡት የከተማ ቆጠራ ቦታዎች ይካሄዳል።

## 2.1. የከተማ ቤቶችና ቤተሰቦች መመዝገብያ ቅጽ (ቅጽ/91/0) አሞላል መመሪያ

### ክፍል 1 ፡ የአካባቢ መለያ

#### የቤተሰቦች አመዘጋገብ ሁኔታ

በተመረጠው ቆጠራ ቦታ የሚገኙ ቤተሰቦች በሚከተለው ሁኔታ መመዝገብ አለባቸው።

ሀ. በመጀመሪያ ለጥናቱ የተመረጠውን ቆጠራ ቦታ በተሰጠው የቆጠራ ቦታ ካርታና መግለጫ መሠረት አካባቢውን ከሚያውቅ ሰው ጋር በመሆን ድንበሩን/ክልሉን ዞሮ ማየትና ማጥናት

ለ. የቤቶችን፣ የመንገዶችንና የመንደሮችን አቀማመጥ ማየት፣

ሐ. ምዝገባውን ከቆጠራ ቦታው ሰሜን ምዕራብ ከሚገኘው መንደር/አካባቢ/ በመነሳት ወደ ምስራቅ ከዚ ያ ወደ ምዕራብ /ጥምዝምዞሽ/ ሥርዓት ባለው መንገድ በመንዝ እያንዳንዱን ቤተሰብ መመዝገብ። እያንዳን ዱን ቤተሰብ ከመዘገቡ በኋላ በቤቱ በር ወይም ሊጠፋ ከማይችል ቦታ ላይ በቾክ/ጠመኔ በእያንዳንዱ ቤት ላይ እንደአመዘጋገባቸው ቅደም ተከተል MP001, MP002, MP010, MP123... ወዘተ በማለት መጻፍ ያስፈልጋል። በተጨማሪም ከተመረጠው ቆጠራ ቦታ በመውጣት ምዝገባ እንዳይካሄድ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። እንዲሁም በአንድ ቤት ውስጥ ከአንድ በላይ ቤተሰቦች/ደባሎች/ ከኖሩ እንዳይዘነጉ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፣ ደባል የሆኑ ቤተሰቦች ከተገኙም ለእያንዳንዱ ደባል ቤተሰብ የራሱ የሆነ የቤተሰብ ተከታታይ ተራ ቁጥር መስጠት እንዳለበት መገንዘብ ያሻል።

**ዓምድ 1-3፡ ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፡-**

በእነዚህ ዓምዶች የቆጠራ ቦታው የሚገኝበት ክልል፣ ዞን፣ እና ወረዳ ስም ይሞላል። ካርድ ኮለሞቹ ባዶ ይተዋሉ።

**ዓምድ 4፡ ከተማ፡-**

የቆጠራ ቦታው የሚገኝበት ከተማ ስም በዓምዱ ይሞላል። ካርድ ኮለሙ ባዶ ይተዋል።

**ዓምድ 5፡ ከፍተኛ/ወረዳ፡-**

የቆጠራ ቦታው የሚገኝበት ከፍተኛ/ወረዳ ስም በዚህ ዓምድ ይሞላል። ካርድ ኮለሞቹ ባዶ ይተዋሉ።

ማሳሰቢያ፡-

አብዛኛው ከተሞች ደግሞ በወረዳ ሥር ስለሚሆኑ በዓምድ 3 የሚገኙበት ወረዳ ስም ሲሞላላ ቸው በዓምድ 5 ደግሞ «ከፍተኛው» ይሞላል። ነገር ግን አንዳንድ ከተሞች በወረዳ ውስጥ ሳይሆኑ የ ራሳቸው አስተዳደር ያላቸው ሆነው የተሸነሸኑት ደግሞ በከፍተኛ ሳይሆን በወረዳ ይሆናል (ለምሳሌ አ

ዲስ አበባ)፡፡ በዚህን ጊዜ ዓምድ 3 በሰረዝ ይታለፍና በዓምድ 5 በከፍተኛው ምትክ የወረዳው ቁጥር/ ስም ይመዘገባል ማለት ነው፡፡

<u>ዓምድ 6፡</u> <u>ቀበሌ</u>፡-

የቆጠራ ቦታው የሚገኝበት ቀበሌ ስም/ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሞላል፡፡ ካርድ ኮለሞቹ ባዶ ይተዋሉ፡፡

<u>ዓምድ 7፡</u> <u>የቆጠራ ቦታ</u>፡-

የቆጠራ ቦታው ቁጥር ለዚህ ዓምድ በተዘጋጀው ካርድ ኮለም ክፍት ቦታ ይሞላል፡፡

## <u>ክፍል 2፡ የቤተሰቦች ዝርዝርና የአመራረጥ ቅደም ተከተል</u>

የቤት መረጃን ከመመዝገብ በፊት የቤትን፣ የመኖሪያ ቤትንና የቤተሰብን ትርጓሜ ጠንቅቆ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

### ሀ. <u>ቤት፣</u>

ቤት ማለት "በአሠራሩ ተለይቶ" እና "ራሱን የቻለ" ሆኖ ለመኖሪያ ብቻ፣ ለመኖሪያና ለድርጅት ወይም ለድር ጅት ብቻ የሚያገለግልና ለማገልገል የተዘጋጀ ነው፡፡

<u>የቤቱ አሠራር የተለየ ነው፣</u> የሚባለው ዙሪያውን በግድግዳ፣ የተከለለ ሆኖ ጣራውም በክዳን የተሸፈነ በመሆነ - በውስጡ የሚኖሩት ሰዎች በሚተኙበት ጊዜ፣ ምግባቸውን ሲያዘጋጁና ሲመገቡ ከሌሎች በዙሪያው ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ለመለየት የሚያስችል ነው፡፡ ሆኖም አንዳንድ ጊዜ በሳጠራ፣ በፕላስቲክ፣ በካርቶን፣ ... ወዘተ ግድ ግዳው የተሠራ ወይም የተከበበና ጣራው በፕላስቲክ ክዳን የተሸፈነ ሆኖ ለድርጅት ወይም ለመኖሪያ የሚያገለ ግል ቤት ሊያጋጥም ይችላል፡፡ ይህ ሁኔታ ሲያጋጥም ምንም እንኳን የቤትን ትርጉም ባያሟላም ከአገልግሎቱ አንጻር ሲታይ ቤት ስለሆነ እንደቤት ይወሰዳል፡፡ ነገር ግን በፕላስቲክና በመሳሰሉት ቁሳቁሶች የሚሠሩና ለ ማደሪያነት ብቻ ተጠቅመውባቸው ቀን ቀን የሚፈርሱና ለመዋያነት የሚያገለግሉ ከሆነ እንደ ቤት አይቆጠሩ ም፡፡ ድንኳኖችም ሰው የሚኖርባቸው ከሆነ እንደቤት እንደሚቆጠሩ ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡

<u>የቤቱ አሠራር ራሱን የቻለ ነው፣</u> የሚባለው ቤቱ ከመንገድ ወይም የጋራ በሆነ መተላለፊያ፣ መሬት ... ወ ዘተ የራሱ መግቢያና መውጪያ ያለው ሆኖ በውስጡ የሚኖሩት ሰዎች ወደ ቤት ሲገቡ ወይም ከቤት ሲወጡ የሚተላለፉት በሌሎች ቤት ውስጥ በማለፍ ሳይሆን በቀጥታ በራሳቸው መውጪያ ወይም መግቢያ ብቻ ሲሆን ነው፡፡

### ለ. <u>መኖሪያ ቤት፣</u>

መኖሪያ ቤት ማለት በአሠራሩ የተለየና ራሱን የቻለ ሆኖ ለመኖሪያነት ታስቦ የተሠራ ወይንም ምንም እንኳን ለሰው መኖሪያ ታስቦ ባይሰራም ጥናቱ ቀን ሰዎች ለመኖሪያነት የሚገለገሉበት ቤት ነው፡፡ ቤቱ ሙሉ በሙሉ ሰዎች የሚኖሩበት ወይም በከፊል እየኖሩ በቀረው ሌላ ተግባር ለምሳሌ ንግድ፣ ሽመና፣ የእንጨት ሥራ ... ወዘተ የሚያከናውኑበት ቤት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ቤቱ ለመኖሪያና ድርጅት ተብሎ ይመዝገብ፡፡ በአንድ መኖሪያ ቤት ከአንድ በላይ የሆኑ ቤተሰቦች (ደባሎች) ሊኖሩ ይችላል፡፡

### ሐ. <u>ቤተሰብ፣</u>

ቤተሰብ ማለት በአንድ ቤት ወይም በተቀራረቡ ቤቶች ውስጥ አብረው የሚኖሩትንና ምግባቸውን በአንድ ማ ድቤት አብስለው በአንድነት የሚመገቡ ሰዎችን ያጠቃልላል፡፡ የቤተሰብ አባሎች በሥጋ ወይም በጋብቻ የሚዛ መዱትንና የማይዛመዱትን ሊያጠቃልል ይችላል፡፡ በሥጋ ወይም በጋብቻ የሚዛመዱት ባል፣ ሚስት፣ ልጆች፣ የባ ል ወይም የሚስት አባት፣ እናት፣ እህት፣ ወንድም፣ ...ወዘተ ናቸው፡፡ በሥጋ ወይም በጋብቻ የማይዛመዱ ሌሎ ች የቤተሰብ አባላት ለምሳሌ በቤት ሠራተኛነት፣ በዘበኝነት የሚያገለግሉ ግለሰቦች ከቤተሰቡ ጋር አብረው የሚ ኖሩና የሚመገቡ ከሆነ እንደ ቤተሰብ አባል ይቆጠራሉ፡፡

የቤተሰብ አባላት ብዛት ሊለያይ ይችላል፡፡ ይኸውም አንድ ሰው ብቻውን እንደ አንድ ቤተሰብ ሊቆጠር ይችላ ል፡፡ ብዙ አባላት ያሉትም እንደ አንድ ቤተሰብ ይቆጠራል፡፡ ነገር ግን ከጥናቱ ጊዜ በፊት ቤተሰቡን ትቶ ወደ

ሌላ ቤተሰብ በመሄድ እዚያ ለስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ ከተቀመጠ አሁን ለሚገኝበት ቤተሰብ እንግዳ መሆኑ ቀርቶ ለቤተሰቡ አባል ይሆናል ማለት ነው፡፡

ጋብቻው በአንድ ሚስት ብቻ የተመሠረተ ከሆነ ቤተሰብ ባልን፣ ሚስትን፣ ልጆችን፣ የጉዲፈቻ ልጆችን፣ ሌሎች ዘመዶችንና ዘመድ ያልሆኑትን (የቤት ሠራተኞች ...ወዘተ) ሊያጠቃልል ይችላል፡፡ ነገር ግን ጋብቻው ከብዙ ሚስቶች ጋር የተመሠረተ ከሆነ (አንድ ወንድ ከአንድ በላይ ሚስቶች ካሉት) የሰውዬው ሚስቶች ከነልጆቻቸ ውና ዘመዶቻቸው ... ወዘተ በአንድ ቤት ወይም በተቀራረቡ ቤቶች የማይኖሩና ምግባቸውንም በአንድነት አብ ስለው የማይበሉ ከሆነ፣ ባልየው በቅድሚያ ካገባት ሚስቱ ጋር እንደ አንድ ቤተሰብ ተቆጥሮ ሌሎቹ የሰውዬ ው ሚስቶች የየራሳቸው ቤተሰብ እንዳላቸው ሆኖ መቆጠር አለባቸው፡፡

የቅርብ ዝምድና ያላቸው ሰዎች አንዳንድ ጊዜ በአንድ ጊቢ ውስጥ አንድ ላይ ተቀራርበው ይኖራሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች ግን ምግባቸውን በአንድ ላይ አብስለው እስካልተመገቡ ድረስ የተለያዩ ቤተሰቦች ተብለው ይቆጠራሉ፡፡ በአንድ ቤት ውስጥ ተዳብለው የሚኖሩ ቤተሰቦችም ምግባቸውን አብረው የሚመገቡ እስካልሆነ ድረስ እንደተ ለያዩ ቤተሰቦች ይቆጠራሉ፡፡

## መ. የቤተሰብ ኃላፊ፣

«የቤተሰብ ኃላፊ» ማለት የአንድ ቤተሰብ መደበኛ አባል የሆነ ወንድ/ሴት በቤተሰቡ አባላት እንደ ኃላፊ የ ሚቆጠር/የሚታይ ነው፡፡ ከአንድ በላይ ሚስቶች ያሉት ሰው ሚስቶቹ በተለያዩ ቤተሰብ የሚኖሩ ከሆነ እሱ የ ቤተሰቡ ኃላፊ ሆኖ ሊመዘገብ የሚችለው አሁን በሕይወት ካሉት ውስጥ በቅድሚያ ካገባት/አንጋፋ ሚስቱ ጋር ይሆናል፡፡ ሌሎች ሚስቶች ግን የየራሳቸውን ቤተሰብ ኃላፊ ሆነው ይመዘገሉ፡፡

ማሳሰቢያ፡ በቅጹ ግርጌ ጠቅላላ የቤተሰቦች ብዛት በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይሞላል፡፡

## ዓምድ 8 የቤት ተከታታይ ተራ ቁጥር፡-

በቆጠራው ቦታ ለሚገኙ ቤቶች እንደ አመዘጋገባቸው ቅደም ተከተል ተከታታይ ተራ ቁጥር 001፣ 002፣ ... ወዘተ በማለት ቤቶቹ ተመዝግበው እስከአለቁ ድረስ በዚህ ዓምድ ባሉት ካርድ ኮለሞች ይሞላሉ፡፡ በተጨማሪ ም በቤቱ በር ከፍ ብሎ በስተግራ ባለው ጥግ ወይም በር ከሌለው አመቺ በሆነና ዝናብና ልጆች ሊያጠፉት በማይችሉበት ቦታ በጠመኔ MP001፣ MP002፣ ... ወዘተ በማለት መጻፍ አለበት፡፡ በአንድ ቤት ውስጥ ከአን ድ በላይ ቤተሰቦች/ደባሎች ቢኖሩበት የእያንዳንዳቸው ኃላፊዎች በዓምድ 12 በየተራ በሚመዘገቡበት ጊዜ የቤ ቱ ተከታታይ ተራ ቁጥር አንድ ስለሆነ በዓምድ 8 አንዱ ቁጥር ተደጋግሞ መጻፍ ይኖርበታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ፎቅ በሆነ ቤት ውስጥ አራት መኖሪያ ቤቶች ካሉ የተለያዩ ቤቶች ስለሆኑ ለአራቱም ቤቶች ተከታታይ የሆነ የተለያየ ተራ ቁጥር በዓምድ 8 መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በሌላ አንጻር በአንድ አጥር ግቢ አንድ ቤተሰብ የሚኖርባቸው የተለያዩ ቤቶች ቢኖሩ እንደ አንድ ቤት ስለሚቆጠሩ አንድ የቤት ተራ ቁጥር ይሰጣቸዋል፡፡ ነ ገር ግን በአንድ አጥር ግቢ ውስጥ ከአንድ በላይ ቤተሰብ የሚኖሩባቸው ቤቶች ካሉ ለእያንዳንዱ ቤት የተለያየ የቤት ተራ ቁጥር በተከታታይ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በአንድ አጥር ግቢ ውስጥ ሆነው ለተመሳ ሳይ ዓላማ የሚያገለግሉ ህንጻዎች ካሉ ሁሉም እንደ አንድ ቤት ይቆጠራሉ፡፡

## ዓምድ 9 የቤት ቁጥር/ንዑስ ቁጥር፡-

በዚህ ዓምድ በቆጠራ ቦታው ለሚገኙ ቤቶች ሁሉ የቤት ቁጥር ያላቸው ከሆኑ የቤት ቁጥሩ ይመዘገባል፡፡ በቆ ጠራው ቦታ ለሚገኙ ለአብዛኛው ቤቶች በቀበሌው ጽ/ቤት የመለያ ቁጥር ተሰጥቷቸዋል፡፡ ይኸው ቁጥር በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል፡፡ አንዳንድ ጊዜ አንድ ቤተሰብ ከአንድ በላይ የሆነ የተለያዩ ቁጥሮ ች ያሉዋቸው መኖሪያ ቤቶች ሊይዝ ይችላል፡፡ እንዲሁም ደግሞ በአንድ መኖሪያ ቤት ውስጥ ከአንድ በላይ የሆኑ ቤተሰቦች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ የቤት ቁጥር በዚህ ዓምድ ከመሞላቱ በፊት የሚከተሉትን ነጥቦች በ ተጨማሪ ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡

1. በአንድ መኖሪያ ቤት ከአንድ በላይ ቤተሰቦች ከሆነ ይኸው ቁጥር ለእያንዳንዱ ቤተሰብ እየተ ደጋገመ በዓምድ 8 ይሞላል፡፡

2.

አንድ ቤተሰብ ከአንድ በላይ የሆኑና የተለያዩ ቁጥሮች የተሰጣቸው የመኖሪያ ቤቶች ከያዘ ቤ ተሰቡ የሚኖርበት የዋናው ቤት ቁጥር በዓምድ 9 ይሞላል፡፡

3. ከላይ በተራ ቁጥር 2 የተጠቀሱት ትናንሽ ቤቶች (" ሰርቪስ ") በተለያዩ ቤተሰቦች የተያዙ እንደሆነና የትልቅ ቤት ተቀጽላ ቁጥር የተሰጣቸው ካልሆነ በዓምድ በ ተሰጠው ቦታ የትልቁን ቤት ቁጥር በመሙላት ቤቶቹ የትልቅ ቤት ተቀጥላዎች መሆናቸውን በአስተ ያየት ዓምድ መግለጽ ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን ትናንሾቹን (ሰርቪሶች) የተለያዩ የራሳቸው ቁጥር በቀበ ሌው ጽህፈት ቤት ከተሰጣቸው ይህንኑ ቁጥር በዓምድ 9 መሙላት ያስፈልጋል፡፡

4.

በአንድ ግቢ ውስጥ የሚገኙ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ መኖሪያ ቤቶች በሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ቤተሰቦች ተይዘው ካሉ የተሰጠው የመኖሪያ ቤት ቁጥር ግን ለግቢው የሚያገለግል አንድ ቁጥ ር ብቻ ከሆነ ይኸው ቁጥር ለእያንዳንዱ ቤተሰብ በዓምድ 9 በእያንዳንዱ ቤት አቅጣጫ መመዝገብ አ ለበት፡፡ እነዚህ ተደጋጋሚ የቤት ቁጥሮች ለግቢው የተሰጡ መሆናቸው በአስተያየት ዓምድ መግለጽ ያስፈልጋል፡፡

5.

ቤቱ በጥናቱ ጊዜ (በምዝገባው ቀን) ቁጥር የሌለው ከሆነ ዓምዱ ባዶ ቦታ ይተዋል፡፡ አንዳ ንድ ጊዜ ቀበሌዎች በዞን የተከፈሉ ሲሆን የቤት ቁጥር አሰጣጡም በዞኖች የተመሠረተ በመሆኑ የቤ ቶቹ ቁጥር ሊደጋገም ይችላል፡፡ ይኸም ማለት ለምሣሌ በዞን 1 የቤት ቁጥር 001 ቢኖር በዞን 2, 3, ...
ወዘተ ቁጥራቸው 001 የሆኑ ሌሎች ቤቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ይህ ሁኔታ ሲያጋጥም የዞን ቁጥ ርና የቤቶች ቁጥር ይጻፋል/ለምሣሌ 1/001፣ 1/002 ... ወዘተ፡፡ ቤቱ በተለያዩ ንዑስ ቤቶች ወይም መኖሪያ ቤቶች ተከፋፍሎ የተለያዩ ቤተሰቦች የሚኖሩበት ሊሆን ይችላል፡፡ ለእነዚህ ንዑስ ቤቶች ወ ይም መኖሪያ ቤቶች ከዋናው ቤት ቁጥር ቀጥሎ ለእያንዳንዳቸው ንዑስ ቁጥር በቀበሌው ተሰጥቶ እን ደሆነ እነዚህ ንዑስ ቁጥሮች ከቤት ቁጥር ቀጥሎ ይመዘገባሉ፡፡ ለምሳሌ የፎቁ ቤት ዋና ቁጥር 50 ሆኖ በውስጡ አራት ቤቶች ካሉት ለእያንዳንዱ ቤት 1፣ 2፣ 3 እና 4 የሚል ንዑስ ቁጥሮች ካላቸው እነዚሁ ንዑስ ቁጥሮች ከቤቱ ቁጥር ጋር በማያያዝ በተከታታይ 50/1፣ 50/2፣ ወዘተ ተብለው ይመዘ ገባሉ፡፡ እንዲሁም በአንድ ግቢ ውስጥ ባሉ ብዙ ቤቶች የተለያዩ ቤተሰቦች የሚኖሩ ከሆነ ለግቢው ራሱን የቻለ ቁጥር ተሰጥቶት በግቢው ውስጥ ላሉት ቤቶች ለእያንዳንዳቸው የተለያዩ ቁጥሮች ወይም ፊደሎች ተሰጥቷቸው ከሆነ እነዚህ ቁጥሮች እንደ ንዑስ ተወስደው በዚህ ዓምድ ይመዘገባሉ፡፡

<u>ዓምድ 10፡</u> <u>የቤቱ አገልግሎት፡</u>-

በዚህ ዓምድ የቤቱ አገልግሎት ተጠይቆ ይመዘገባል፡፡ ዓምዱ ከመሞላቱ በፊት የሚከተሉትን ፅንሰ ሀሳ ቦች መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ሀ. <u>ለመኖሪያ ብቻ</u>

የተመዘገበው ቤት በጥናቱ ወቅት ለመደበኛ ቤተሰብ አባላት መኖሪያ ብቻ የሚያገለግል ከሆነ "ለመኖ ሪያ ብቻ" የሚል መልስ ተመዝግቦ ኮድ "1" በካርድ ኮለሙ ይጻፋል፡፡

ለ. <u>ለመኖሪያና ለድርጅት</u>

የተመዘገበው ቤት በጥናቱ ወቅት የሚሰጠው አገልግሎት በከፊል ለመደበኛ ቤተሰብ አባላት መኖሪያና በከፊል ደግሞ ለድርጅት አገልግሎት የዋለ እንደሆነ የቤቱ አገልግሎት "ለመኖሪያና ለድርጅት" ተ ብሎ ይመዘገብና ኮድ "2" በካርድ ኮለሙ ይሞላል፡፡ ለምሳሌ በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ጠላ የሚሸ ጡ ቤቱ ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት የሚል ስም ይሰጠዋል፡፡

ሐ. <u>ለሌላ</u>

ከመኖሪያ እና ከመኖሪያና ከድርጅት ውጭ ለሆነ የቤት አገልግሎት ባጠቃላይ በሌላ ውስጥ ይጠቃለላ ል፡፡ ይህም ማለት ለሆቴል/ሆስቴል መኖሪያ፣ ለሌላ ጋርዮሽ መኖሪያ፣ ለመንግሥት ወይም ለሌላ ድር ጅት ብቻ ያልተያዘ ቤት እና በመሰራት ላይ ያለን ያጠቃልላል፡፡

ዓምድ 11-12፡ ቤቱ ለመኖሪያ ወይም ለመኖሪያና ለድርጅት ከሆነ፣

**ዓምድ 11፡ የቤተሰብ ተከታታይ ተራ ቁጥር፡-**

በዓምድ 10 ኮድ 1 እና ኮድ 2 የተሞላላቸው ቤቶች/ለመኖሪያ እና ለመኖሪያና ድርጅት/ ውስጥ የሚገኙ ቤተ ሰቦች በሙሉ በዚህ ዓምድ ተከታታይ ተራ ቁጥር ይሰጣቸዋል፡፡ የናሙና ቤተሰቦች የሚመረጡት ከዚህ ዓም ድ ላይ በመሆኑ የቤተሰቦች ተከታታይ ተራ ቁጥር ሳይዛነፍ በጥንቃቄ በተከታታይ መመዝገብ አለበት፡፡ በተ ጨማሪም በዓምድ 10 ኮድ 3 የተሞላላቸው መደበኛ ቤተሰብ የማይኖርባቸው በመሆኑ ከዓምድ 12-14 ስለማይ መለከታቸው በ "__" ይታለፋል፡፡

**ዓምድ 12፡ የቤተሰብ ኃላፊ ሙሉ ስም፡-**

በዚህ ዓምድ የቤተሰብ ኃላፊው ሙሉ ስም ይመዘገባል፡፡

**ዓምድ 13፡ የአመራረጥ ቅደም ተከተል፡-**

በዚህ ዓምድ በናሙና ቤተሰቦች አመራረጥ ቅደም ተከተል መሠረት የተመረጡ ቤተሰቦች ተራ ቁጥር ከ01 በመጀመር እስከ 35 የሚሰጥ ይሆናል፡፡

**ዓምድ 14፡ አስተያየት፡-**

ቅጹን በተመለከተ አስፈላጊ አስተያየቶች በዚህ ዓምድ ይገለጻሉ፡፡

## 2.2. የ1991 የሰው ኃይል ናሙና ጥናት ቅጽ 91/1 አሞላል

በዚህ ቅጽ ላይ ለሰው ኃይል ጥናት የተመረጡትን 35 ቤተሰቦች እንደ አመራረጥ ቅደም ተከተላቸው ለከተማ ከቅጽ 91/0፣ ለገጠር ከቅጽ 90/0 በመወራረስ ይመዘገባሉ፡፡ እነዚህን የተመረጡትን 35 ቤተሰቦች መረጃ ሰብሳቢው ከቤ ት ወደ ቤት ተዘዋውሮ በመጠየቅ መረጃውን ይሰበስባል፡፡

### ክፍል 1. የአካባቢ መለያ

**ዓምድ 1. ክልል**

በዚህ ዓምድ ጥናቱ የሚካሄድበት ክልል፣ ዞን እና ወረዳ ስም፣ ለከተማ ከቅጽ 91/0 ዓምድ 1፣ 2 እና 3 ለገጠ ር ከቅጽ 90/0 ክፍል 1 ዓምድ 1፣ 2 እና 3 በመውሰድ ይሞላል፡፡ ካርድ ኮለሞቹ ባዶ ይተዋሉ፡፡

**ዓምድ 4 ከተማ**

በዚህ ዓምድ ጥናቱ የሚካሄድበት ከተማ ስም ከቅጽ 91/0 ክፍል 1 ዓምድ 4 በመውሰድ ይሞላል፡፡ ካርድ ኮለ ሙ ባዶ ይተዋል፡፡ ለገጠር በሰረዝ ይታለፋል፡፡

**ዓምድ 5 ከፍተኛ/ወረዳ**

ይህ ዓምድ የሚሞላው ለከተማ መጠይቆች ብቻ ሲሆን ለገጠሩ መጠይቅ በሰረዝ ይታለፋል፡፡ ከክፍል 1 ዓምድ 5 በመውሰድ ለከተማው ይሞላል፡፡ ካርድ ኮለሞቹ ባዶ ይተዋሉ፡፡

**ዓምድ 6 ቀበሌ/ገበሬ ማህበር**

በዚህ ዓምድ ጥናቱ የሚካሄድበት ቀበሌ/ገበሬ ማህበር መለያ ስም/ቁጥር ለከተማ ከቅጽ 91/0 ክፍል 1 ዓምድ 6 ለገጠር ከቅፅ 90/0 ክፍል 1 ዓምድ 4 በመውሰድ ይሞላል፡፡ ካርድ ኮለሞቹ ባዶ ይተዋሉ፡፡

**ዓምድ 7 የቆጠራ ቦታ ኮድ**

በዚህ ዓምድ ጥናቱ የሚካሄድበት የቆጠራ ቦታ ኮድ ለከተማ ከቅጽ 91/0 ዓምድ 7 ለገጠር ደግሞ ከቅጽ 90/1 ክፍል 1 ዓምድ 7 በመውሰድ ይሞላል፡፡

## ክፍል 2 የተመረጡ ቤተሰቦች ዝርዝር

### ዓምድ 8 - የቤተሰብ ተከታታይ ቁጥር

ለከተማ ከቅጽ 91/0 ክፍል 2 ዓምድ 11 በመውሰድ ይሞላል። ለገጠር ከቅጽ 90/0 ከክፍል 2 ዓምድ 1 በመ ውሰድ ይሞላል)።

### ዓምድ 9 የቤተሰቡ ኃላፊ ስም

በዚህ ዓምድ ለጥናቱ የተመረጠው የቤተሰቡ ኃላፊ ስም ለከተማ ከቅጽ 91/0 ዓምድ 12 ሲወሰድ ለገጠሩ ከቅጽ 90/0 ከክፍል 2 ዓምድ 2 በመውሰድ ይመዘገባል።

### ዓምድ 10 የአመራረጥ ቅደም ተከተል

የተመረጡት ቤተሰቦች የአመራረጥ ቅደም ተከተል ለከተማ ከቅጽ 91/0 ክፍል 2 ዓምድ 13 ሲወሰድ ለገጠር ከቅጽ 90/0 ከክፍል 2 ዓምድ 10 በመውሰድ ይሞላል።

### ዓምድ 11 አስተያየት

በዚህ ዓምድ ቅጹን ለመሙላት ያጋጠሙ ችግሮችና ሌሎች አስፈላጊና መገለጽ ያለባቸው አስተያየቶች ይሠፍራሉ።

በመጨረሻም የመረጃ ሰብሳቢው፤ የመስክ ሥራ ተቆጣጣሪውና የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ ስለሥራው ትክክለኛነት ስማቸውን ፊርማቸውንና ሥራው የተጠናቀቀበትን ቀን በተገቢው ቦታ ማስፈር አለባቸው።

# ምዕራፍ 3 - የክፍል 1 እና ክፍል 2 አሞላል መመሪያ

## ክፍል 1 <u>የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ</u>

ይህ ክፍል ለተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ መመዝገቢያ የሚያገለግል ሲሆን በእያንዳንዱ የመጠይቁ ገጽ ላይም በተመሳሳይ ሁኔታ የሚሞላ ነው:: ይህ ክፍል ለአሠራር ቀለል ያለ ቢሆንም ስህተቶችና ግድፈቶች ስለሚታዩ በጥንቃቄ መሞላት አለበት::

ስለዚህ:-

ሀ. የክልል፣ የዞን፣ የወረዳና የመሳሰሉት ስሞች በግልጽ በሚነበብ ሁኔታ መመዝገብ ያስፈልጋል:: ካርድ ኮለሞቹ ባዶ ይተዋሉ::

ለ. በቁጥር የሚታወቁ ዞኖች ወይም ወረዳዎች ወይም ገበሬ ማህበራት ቁጥሮቹ እንደ ኮድ እንዳይወሰዱ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል::

<u>ዓምድ 1</u>: <u>ክልል</u>:-

ጥናቱ የሚካሄድበት ክልል ስም የሚመዘገብበት ነው:: ካርድ ኮለሞቹ ባዶ ይተዋሉ::

<u>ዓምድ 2 እና 3</u>: <u>ዞንና ወረዳ</u>:-

ጥናቱ የሚካሄድበት ዞንና ወረዳ ስሞች በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ይመዘገባሉ:: ካርድ ኮለሞቹ ባዶ ይተዋሉ::

<u>ዓምድ 4</u>: <u>ከተማ</u>:-

ለከተማ መጠይቅ ጥናቱ የሚመለከተው ከተማ ስም የሚሞላ ሲሆን ለገጠር ግን በሰረዝ ይታለፋል:: ካርድ ኮለሙ ባዶ ይተዋል::

<u>ዓምድ 5</u>: <u>ከፍተኛ/ወረዳ</u>:-

ለከተማ መጠይቅ ጥናቱ የሚመለከተው ከፍተኛ/ወረዳ ስም ወይም የወረዳ ቁጥር ሲሞላ ለገጠር ግን በሰረዝ ይታለፋል:: ካርድ ኮለሞቹ ባዶ ይተዋሉ::

<u>ማሳሰቢያ</u>:-

አብዛኛው ከተሞች ደግሞ በወረዳ ሥር ስለሚሆኑ በዓምድ 3 የሚገኙበት ወረዳ ስም ሲሞላላቸው በዓምድ 5 ደግሞ «ከፍተኛው» ይሞላል:: ነገር ግን አንዳንድ ከተሞች በወረዳ ውስጥ ሳይሆኑ የራሳቸው አስተዳደር ያላቸው ሆነው የተሸነሹት ደግሞ በከፍተኛ ሳይሆን በወረዳ ይሆናል (ለምሳሌ አዲስ አበባ):: በዚህን ጊዜ ዓምድ 3 በሰረዝ ይታለፍና በዓምድ 5 በከፍተኛው ምትክ የወረዳው ቁጥር/ስም ይመዘገባል ማለት ነው::

<u>ዓምድ 6</u>: <u>ቀበሌ/ገበሬ ማህበር</u>:-

በዚህ ዓምድ ለከተማ የቀበሌው ቁጥር(ስም) ሲሞላ ለገጠር ደግሞ የገበሬ ማህበሩ/የጣቢያ ስም/ቁጥር/ ይሞላል:: ካርድ ኮለሞቹ ባዶ ይተዋሉ::

<u>ዓምድ 7</u>: <u>የቆጠራ ቦታ ኮድ</u>:-

በዚህ ዓምድ ሥር በሚገኙ ካርድ ኮለሞች ለጥናቱ ለተመረጠው የቆጠራ ቦታ የተሰጠው የመለያ ኮድ ይሞላል::

<u>ዓምድ 8</u>: <u>የተመረጠው ቤተሰብ የምርጫ ተራ ቁጥር</u>:-

በዚህ ዓምድ ሥር በሚገኙ ካርድ ኮለሞች ጥናቱ የሚመለከተው ቤተሰብ የምርጫ ተራ ቁጥር ይሞላል:: ይህ ተራ ቁጥር የሚገኘው በገጠር መመዝገቢያ ቅጽ/90/0 ክፍል 2 በዓምድ 10 ሲሆን ለከተማ ደግሞ በመመዝገቢያ ቅጽ/91/0 ክፍል 2 ዓምድ 13 ነው::

**ዓምድ 9፡** **የቤተሰብ ኃላፊ ሙሉ ስም፡-**

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ የቤተሰቡ ኃላፊ ማን እንደሆኑ አጣርቶ በመጠየቅ የኃላፊው ስም፣ የአባት ስምና የአያት ስም ጭምር መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል 2 ስለቤተሰቡ መደበኛ አባላት ዝርዝር መረጃዎች (ከዓምድ 10-27)

በዚህ ክፍል ውስጥ የመደበኛ ቤተሰብ አባላት ዝርዝር ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና፣ ጾታቸው፣ ዕድሜያቸው፣ ኃይማኖት፣ ብሔረሰብ፣ የፍልሰት ሁኔታ እንዲሁም ዕድሜያቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆናቸው የትምህርት ሁኔታ እና ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው አባላት የስልጠናና የጋብቻ ሁኔታ ዝርዝር መረጃ ይሰበሰባል፡፡

**ዓምድ 10** **የቤተሰብ መደበኛ አባላት ተራ ቁጥር**

ይህ ዓምድ በቅድሚያ ለአስራ አንድ ወይም ከዚያ ላነሰ የቤተሰብ አባላት ለመመዝገብ እንደሚበቃ ተደርጎ ተዘጋጅቷል፡፡ ነገር ግን የቤተሰብ አባላት ብዛት ከአስራአንድ በላይ ከሆነ ሌላ ተጨማሪ መጠይቅ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም በተጨማሪው መጠይቅ በዓምድ 10 ከ01-11 ያሉትን ቁጥሮች በመሠረዝ በምትካቸው 12፣ 13፣ . . . ወዘተ በማለት የቤተሰቡ መደበኛ አባላት በሙሉ እስከተመዘገቡ ድረስ ተከታታይ ተራ ቁጥሮች በዓምድ 10 ይሰጣል፡፡

**ዓምድ 11** **የቤተሰብ መደበኛ አባላት ሙሉ ስም፡-**

በዚህ ዓምድ ላይ በተመረጠው ቤተሰብ ውስጥ በመደበኛነት የሚኖሩ የቤተሰብ አባላት በጠቅላላ ይመዘገባሉ፡፡ በምዝገባው ጊዜ ከቤተሰቡ ጋር ያሉ መደበኛ የቤተሰብ አባላትና ለጊዜው እቤት ውስጥ ያልተገኙ መደበኛ አባላት ስም በዓምዱ ውስጥ ሲመዘገብ፣ በወቅቱ ከቤተሰቡ ጋር የሚገኙ እንግዶች ግን አይመዘገቡም፡፡

የቤተሰቡ አባላትን ስም በትክክል ከመመዝገብ በፊት የቤተሰብ መደበኛ አባላት የሚባሉት እነማን እንደሆኑ በቅድሚያ ጠንቅቆ መረዳት እንዲቻል ማብራሪያው ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡ እንዲሁም በምዕራፍ 2 ቅጽ 91/0 አሞላል መመሪያ ላይ የተገለጸውን የቤተሰብና የቤተሰብ ኃላፊ ትርጉም ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡

**መደበኛ የቤተሰብ አባል፡-** አንድ ሰው መደበኛ የቤተሰብ አባል ነው የሚባለው ቢያንስ ስድስት ወር ሙሉ ያለማቋረጥ ከቤተሰቡ ጋር የኖረ እንደሆነ ነው፡፡ ከቤተሰቡ ጋር ለዘለቄታው ለመኖር የመጡ ሁሉ ከቤተሰቡ ጋር መኖር ከጀመሩ ስድስት ወር ባይሞላቸውም እንደ ቤተሰቡ መደበኛ አባል ይቆጠራሉ፡፡ ከስድስት ወር በታች ከቤተሰቡ ለጊዜው ተለይተው የቆዩ የቤተሰብ አባላት እንደመደበኛ የቤተሰቡ አባል መቆጠር አለባቸው፤ ነገር ግን ከቤተሰቡ ተለይተው ከሄዱ ስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ የሆናቸው፤ ወይም ከስድስት ወር በላይ ለመቆየት አቅደው የሄዱ ከቤተሰቡ ከወጡ ስድስት ወር ባይሞላቸውም እንደ ቤተሰቡ መደበኛ አባል አይቆጠሩም፡፡

**የሚከተሉት የቤተሰብ አባላት እንደ መደበኛ የቤተሰብ አባል መቆጠር ይኖርባቸዋል፡፡**

1. በጥናቱ ጊዜ ከቤተሰቡ ጋር ቢያንስ ለስድስት ወር የቆዩ፡፡

2. ከቤተሰቡ ጋር መኖር ከጀመሩ ስድስት ወር ባይሞላቸውም ከቤተሰቡ ጋር ለስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ ለመቆየት ዕቅድ ያላቸው ሁሉ፡- ለምሣሌ ባል አግብታ ከወላጆችዋ ቤት ወደ ባልዋ የሄደች ሴት ስድስት ወር ባይሞላትም የባሏ ቤተሰብ መደበኛ አባል ትሆናለች ማለት ነው፡፡ እንዲሁም ሥራ አግኝቶ/ታ ለዘለቄታው ለመኖር ወደ ሌላ ቤተሰብ የሄደ/ች ስድስት ወር ባይሞላውም/ትም በጥናቱ ወቅት የተገኘበት/ችበት ቤተሰብ አባል ይሆናል/ትሆናለች፡፡

3. የቤት ሠራተኞች አብዛኛውን ጊዜ ከቤተሰቡ ጋር የሚያድሩና ሌላ መኖሪያ የሌላቸው ሁሉ፡፡

4. በጥናቱ ጊዜ ከስድስት ወር ላነሰ ከቤተሰቡ ለጊዜው የተለዩ፣ ለምሣሌ በዕረፍት ላይ ያሉ፣ በዓመት በዓል ወደ ሌላ ቦታ የሄዱ፣ ሆስፒታል የገቡ፣ ዘመድ ለመጠየቅ የሄዱና ከሥራቸው ጋር በተያያዘ ጉዳይ ላይ ያሉትን አባላት ሁሉ ያጠቃልላል፡፡

5. ሌላ መኖሪያ ሥፍራ የሌላቸውና በጥናቱ ወቅት ከቤተሰቡ ጋር የሚኖሩ አባላት ሁሉ፣

ለምሣሌ በተለያዩ ቤቶች እያቀያየሩ ለሚኖሩና መደበኛ መኖሪያ የሌላቸው ግለሰቦች በጥናቱ ወቅት በሚገኙበት ቤተሰብ እንደ መደበኛ አባል ተቆጥረው ይመዘገባሉ።

6. <u>ተማሪዎች፡-</u> ከቤተሰቦቻቸው፣ ከወላጆቻቸው፣ ከመደበኛ የመኖሪያ ሥፍራቸው ተለይተው

በመደበኛ ትምህርት ቤቶች፣ በኮሌጆች፣ በዩንቨርስቲዎች ... ወዘተ ትምህርታቸውን በመከታተ ል ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በሙሉ ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት አካባቢ መደበኛ

ነዋሪዎች ሆነው መመዝገብ አለባቸው። በአዳሪ ት/ቤት የሚማሩ ተማሪዎች እንዲሁም ከወላ ጆቻቸው ተለይተው ቤት ተከራይተው ወይም ከዘመድ ተጠግተው እየኖሩ የሚማሩ ተማሪዎች ምንም እንኳን በየሳምንቱ ወይም በየአሥራ አምስት ቀን ስንቅ ለማምጣት ወይም ወላጆቻቸውን ለመጠየቅ ወ ደ ቤተሰቦቻቸው ቢሄዱም እንደ መደበኛ

የቤተሰብ አባል የሚታሰቡት በሚኖሩበት አካባቢ እንጂ በወላጆቻቸው ቤት አይደለም። ነገር ግን ከመደበኛ መኖሪያቸው (ከቤታቸው) በየቀኑ ወደ ትምህርት ቤቶች እየተመላለሱ የሚማሩ ተማሪ ዎች ሁሉ የሚኖሩበት ቤተሰብ መደበኛ አባል ሆነው መመዝገብ አለባቸው።

የቤተሰብ አባላት የምዝገባ ቅደም ተከተል በሚከተለው መልክ መሆን ይኖርበታል።

- የቤተሰብ ኃላፊ
- የኃላፊው ሚስት ወይም ባል
- ያላገቡ ልጆች በዕድሜ ቅደም ተከተል
- ያገቡ ልጆች እና እዚሁ ቤት አብረው የሚኖሩ የቤተሰባቸው አባላት
- ሌሎች ዘመዶች
- ዘመድ ያልሆኑ አባላት

የቤተሰብ አባላትን መልስ ሰጭዎች ዘርዝረው በሚያስመዘግቡበት ጊዜ የአባላትንም ስም፣ ዝምድናና ጾታቸውን በአንድ ላይ ሊያስመዘግቡ ይችላሉ። በመጨረሻም የተመዘገቡትን የቤተሰብ አባላት ስም ለመልስ ሰ ጪው ማንበብና የተዘነጉ አባላት እንዳይኖሩ ማረጋገጥ ያስፈልጋል። እንዲሁም በምዝገባው ወቅት ሕጻናት፣ አ ዛውንቶችና ሠራተኞች እንዳይዘነጉ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

## ዓምድ 12 <u>ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና</u>፡-

የቤተሰብ አባላት አመዘጋገብ ቅደም ተከተል ሲዘረዘር ከላይ እንደተገለጸው ሁሉ የቤተሰቡ ኃላፊ ሁልጊዜ በመጀመሪያው መሥመር ላይ ይመዘገባል /ትመዘገባለች/። አንድ ሰው ብቻ በሚኖርበ ት ቤተሰብ ግለሰቡ ኃላፊ ተብሎ ይጠቀሳል። ከአንድ በላይ የሆኑ አባላት በሚኖሩበት ቤተሰብ ውስጥ በኃላፊነት የሚጠቀሰው/የምትጠቀሰው የቤተሰቡ አባላት ቤተሰቡን በኃላፊነት ይመራል/ትመራለች/ ብለው የሚያምኑበት/የሚያምኑባት/ ግለሰብ ነው/ናት/። የሌሎቹ የቤተሰብ አባላት ዝምድና ከኃላፊ ው/ከኃላፊዋ/ወይም ከሚስተየዋ ወይም ከባልየው ጋር ባላቸው ዝምድና መሠረት በካርድ ኮለሙ ይ ሞላል።

0 = ኃላፊ
1 = የኃላፊ ሚስት/ባል
2 = የኃላፊና የባለቤት ልጅ
3 = የኃላፊ ልጅ
4 = የባለቤት ልጅ
5 = የኃላፊ/የባለቤት አባት/እናት
6 = የኃላፊ/የባለቤት ወንድም/እህት
7 = ሌሎች ዘመዶች /የማደጎ ልጅ፣ የክርስትና ልጅ/
8 = ዝምድና የሌላቸው (ከኃላፊው ጋር ምንም የሥጋም ሆነ የጋብቻ ዝምድና የሌላቸው)

## ዓምድ 13፡ <u>ጾታ</u>፡-

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ የእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ጾታውን በመጠየቅ የሚሞላ ሲሆን በካርድ ኮ ለሙ ደግሞ ጾታው ወንድ ከሆነ ኮድ 1፣ ሴት ከሆነች ኮድ 2 ይሞላል። በስም ብቻ ጾታው ምን እንደሆነ ማወ

ቅ ስለማይቻል የእያንዳንዱን አባል ጾታ ጠይቆ መመዝገብ ያስፈልጋል። የአንዳንድ ሰዎች ስም ለሁለቱም ጾታ ዎች ሊያገለግል ስለሚችል የአባላቱን ስም ብቻ መሠረት በማድረግ ጾታቸውን በግምት መሙላት ስህተት ያስከ ትላል። በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች ወንዶች በሴት ስም እንዲሁም ሴቶች በወንድ ስም ስለሚጠሩ ጾታ በሚሞላበት ጊዜ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

**ዓምድ 14፡ <u>ዕድሜ፡-</u>**

___ እድሜዎ ስንት ዓመት ነው? ብሎ በመጠየቅ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ይህ ጥናት በሚካሄድበት ጊዜ ያ ለው ትክክለኛ ዕድሜ ተጠይቆ በሙሉ ዓመት (በጨረሱት ዓመት) በዚህ ዓምድ ካርድ ኮለሞች ይመዘገባል። ዕ ድሜ በሙሉ ዓመት ማለት ከሙሉ ዓመት በተጨማሪ ያሉትን ወሮችንና ቀኖችን በመተው ዓመቱን ብቻ በመ ውሰድ ዕድሜውን መመዝገብ ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው ዕድሜ 15 ዓመት ከ11 ወር ከ10 ቀን ቢሆን መመዝ ገብ ያለበት 15 ዓመት ብቻ ይሆናል እንጂ 16 ዓመት ሊሞላው 20 ቀን ስለቀረው 16 ዓመት ተብሎ መሞላ ት የለበትም። የአንድ ህፃን ዕድሜ ከአንድ ዓመት በታች ከሆነ በዓምድ 14 ኮድ «00» ይመዘገባል። እንዲሁም የአንድ ሰው ዕድሜ 97 ዓመት እና ከዚያ በላይ ከሆነ ኮድ «97» ብቻ በካርድ ኮለሙ ይመዘገባል።

ዕድሜያቸውን በትክክል የማያውቁ ወይም ዕድሜያቸውን ለመናገር ፈቃደኛ ያልሆኑ ሰዎች እንደሚያ ጋጥሙ ይገመታል። ስለዚህ የእያንዳንዱን የቤተሰብ አባል ትክክለኛ ዕድሜ በተቻለ መጠን ለማግኘት ባለመሰል ቸት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ከሚያስችሉት ዘዴዎች መካከል ቀጥሎ የተመለከቱትን ማጤን ይገባል።

ሀ.

መልስ ሰጪው በተወለደበት ጊዜ/አካባቢ በብሄራዊ ደረጃ ወይም በሚኖርበት አካባቢ የተፈፀ መ ታሪካዊ ድርጊት እንዳለና ቀጥሎም መልስ ሰጪው ድርጊቱ በተፈፀመ ጊዜ ዕድሜው ምን ያህል እንደነበረ ወይም ከድርጊቱ በኋላ ምን ያህል ጊዜ ቆይቶ እንደተወለደ በመጠየቅና ከዚያም ይህንን መ ረጃ መሠረት በማድረግ የግለሰቡን ዕድሜ ለመገመት መሞከር ያስፈልጋል።

<u>**ለምሳሌ፣**</u> ግለሰቡ የ1966 አብዮት ከመፈንዳቱ 10 ዓመት ቀድሞ የተወለደ እንደሆነ የግለሰቡ ዕድሜ በ1991 ዓ.ም. ከሞላ ጎደል (1991-1966)+10=
35 ዓመት ይሆናል። ስለዚህ የአንድን ግለሰብ የተወለደበት ዓመት ታሪካዊ ድርጊቶች ከተፈፀሙበት ዓ መተ ምሕረት ጋር በማዛመድ ዕድሜውን ለመገመት ስለሚቻል ዋና ዋና ታሪካዊ ድርጊቶች የተፈፀመ ብት ዓመተ ምሕረት ዝርዝር በዚህ መመሪያ መጨረሻ ገጽ በአዝል 1 ተያይዞ ይገኛል።

ለ.

አንዳንድ የቤተሰብ አባላት ወይም በአካባቢው የሚኖሩ ግለሰቦች ዕድሜያቸውን በትክክል ሊ ያውቁና ሊናገሩ ይችሉ ይሆናል። በዚህ ጊዜ ዕድሜያቸውን የማያውቁትን ሰዎች ዕድሜ ከነዚህ ዕድማ ያቸውን ከሚያውቁ ሰዎች ጋር በማነፃፀር ለመገመት ይቻላል።

ከቤተሰቡ አባላት መካከል የአንዱ ዕድሜ በትክክል ከታወቀ፣ የሌሎችን ዕድሜ ለመገመት ይቻል ይ ሆናል። ለምሳሌ የአንድ ቤተሰብ የመጀመሪያው ልጅ ዕድሜው 13 ዓመት መሆኑ ከታወቀና የእናቱን ዕድሜ ለማወቅ ቢፈለግ የእናቱ
ዕድሜ ቢያንስ 29 ዓመት ብሎ ለመገመት ይቻላል። ይህም ሊገኝ የሚቻለው እናቶች አብዛኛ ውን ጊዜ በ16 ዓመት የመጀመሪያውን ልጅ ይወልዳሉ ተብሎ
ስለሚገመት የእናትየዋ ዕድሜ 16+13 =
29 ይሆናል። የሥጋ ዝምድና ባላቸው ሰዎች መካከል የአንዱን ዕድሜ ከሌላው በማነፃፀር ዕድሜያቸው ን ለመገመት ይቻላል። ለምሳሌ አብዛኛውን ጊዜ እናቶች በየሁለት ዓመት ይወልዳሉ። የትንሹ ልጅ ዕ ድሜ 7 ዓመት መሆኑ ከተረጋገጠ፣ የታላቁ ልጅ ዕድሜ 9 ዓመት ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም አን ድ አባል ባገባበት ጊዜ ዕድሜው ስንት እንደነበረና በጋብቻ ስንት ዓመት እንደቆየ ከታወቀ ዕድሜውን ለመገመት ይቻላል። ዕድሜያቸው የገፉ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ዕድሜያቸውን በጣም ከፍ ያደርጉታል። የነኚህን ሰዎች ዕድሜ ከመጀመሪያው ልጃቸውና ከልጅ ልጆቻቸው ጋር በማነፃፀር ለመገመት ይቻላል። ስለዚህ የአንዱ ቤተሰብ አባል ዕድሜ ከታወቀ ከሌላው አባል ጋር በማዛመድ በተቻለ መጠን ትክክለ ኛ የሆነውን ገምቶ መፃፍ ያስፈልጋል።

ሐ.

አንዳንድ ሰዎች ዕድሜያቸውን በዜሮ ወይም በአምስት በሚያልቁ አሃዞች ለመናገር ይፈልጋሉ ወይም ይቀላቸዋል፡፡ ስለዚህ ዕድሜያቸውን መግለፅ የሚገባቸው ለመናገር በሚቀላቸው ወይም በሚፈልጉት ሳይሆን፣ ትክክለኛውን ዕድሜ ለማግኘት መሞከር ያስፈልጋል፡፡ አንዳንድ ሰዎች በእርግጥ ዕድሜያቸው 10፣ 15፣ 20፣ 25፣ … ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡

መ.

ዕድሜያቸው ከ10 ዓመት ያላለፉ ሕፃናት ልጆች የተወለዱበትን ጊዜ ወላጆቹ ሊያስታውሱት ስለሚችሉ የሕፃናትና ትናንሽ ልጆች ዕድሜ በሙሉ ዓመት በትክክል መፃፍ አለበት፡፡ አልፎ አልፎ የሕፃናትን ትክክለኛ ዕድሜ ለማግኘት ቀላል የማይሆንበት ሁኔታ ካጋጠመም ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ትክክለኛውን ዕድሜ መመዝገብ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ በላይ የተሰጡትን መመሪያዎች መሠረት በማድረግ የእያንዳንዱን የቤተሰብ አባል ዕድሜ ለማግኘት ትክክለኛ መልሶችን ሊያስገኙ የሚችሉ ጥያቄዎችን በማቅረብና በማስላት በቂ ጥረት ከተደረገ በኋላ ትክክለኛው ዕድሜ በሙሉ ዓመት ይፃፋል፡፡

## ዓምድ 15 <u>ሃይማኖት፣ …… ሃይማኖትዎ ምንድን ነው?</u>

ሃይማኖት አንድ ግለሰብ የሚከተለው እምነት ወይም የመንፈሳዊ ድርጅት አባልነት ነው፡፡ የሃይማኖትን ዓይነት የሚመለከት ጥያቄ ለቤተሰቡ አባላት በሙሉ በማቅረብ ይህን ዓምድ መሙላት ያስፈልጋል፡፡ ሃይማኖት በሚጠየቅበት ጊዜ ክርስቲያን የሚል መልስ ከተገኘ በዚህ ዓምድ ከኮድ 1-3 ከተሰጣቸው ውስጥ የትኛው መሆኑ ተጣርቶ ይሞላል፡፡ ለምሳሌ ከክርስቲያን ወላጆች የተወለደና በጥናቱ ወቅት ክርስትና ለመነሳት ዕድሜው ገና ያልደረሰ ሕፃን ሃይማኖት ክርስቲያን ተብሎ ተገቢው ኮድ ይመዘገብለታል፡፡

1= ኦርቶዶክስ (ተዋህዶ፣ ቅባት፣ ፀጋ)

2= ፕሮቴስታንት (ሰባት ቀን አድቬንቲስት፣ ጴንጤቆስጤ፣ ሉተሪያን መካነየሱስ፣ ባፕቲስት፣ መነናይት፣ እንግሊካን፣ ፕረስፒተርያን፣ መሰረተ ክርስቶስ፣ ሙሉ ወንጌል፣ ቃለ ሕይወት፣ …)

3= ካቶሊክ

4= እስላም (ሙስሊም ነኝ ካሉም «እስላም» መሆኑ ይታወቅ)

5= ባህላዊ አምልኮ

6= ሌላ (ለምሳሌ:- ሂንዱ፣ ይሁዲ፣ ብሃይ፣ ጆሆቫ፣ ኤቲስት፣ …. ወዘተ)

አንዳንድ ጊዜ የቤተሰቡን ኃላፊ ሃይማኖት በመውሰድ የሌሎችን የቤተሰቡን አባላት ሃይማኖት ለመገመት ይሞከር ይሆናል፡፡ ይህ ትክክል ሊሆን ስለማይችል የእያንዳንዱን የቤተሰብ አባል ሃይማኖት በመጠየቅ የተገኘውን መልስ መሠረት በማድረግ የግለሰቡ ሃይማኖት ዓይነት በዓምዱ ተመዝግቦ በካርድ ኮለሙ ትክክለኛው ኮድ መሞላት አለበት፡፡ ባልና ሚስት የተለያየ ሃይማኖት ሊኖራቸው ይችላል፡፡

ለሕፃናት የሚሞላው የሃይማኖት ዓይነት ወላጆቻቸው የሚከተሉት ሃይማኖት ይሆናል፡፡ የተለያዩ ሃይማኖት ከሚከተሉ ወላጆች ለተወለደ ሕፃን ወደፊት ሊከተለው ይችላል ብለው ወላጆቹ የሚያስቡትን ሃይማኖት በመውሰድ በዓምዱ ይሞላል፡፡

## ዓምድ 16 <u>ብሄረሰብ …….. ብሄረሰብዎ ምንድን ነው?</u>

የእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ብሄረሰብ ምን እንደሆነ ተጠይቆ በዓምድ 16 በተሰጠው ክፍት ቦታ ተፅፎ ትክክለኛው ኮድ በካርድ ኮለሞቹ ይመዘገባል፡፡ ግለሰቡ ብሄረሰብህ ምንድነው ተብሎ ሲጠየቅ ትርጉሙን ባለመረዳት ጥያቄውን በትክክል ለመመለስ ከተቸገረ ዘርህ፣ ትውልድህ፣ ነገድህ፣ ጎሳህ፣ በማለት በማብራራት ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡ የብሄረሰቦችን ስምና ኮድ በቀላሉ ለማግኘት እንዲያመች ሁለት ዝርዝሮች ማለትም የዋና ዋና ብሄረሰቦች ስምና ኮድ ዝርዝር እና የቅርንጫፍ ብሄረሰቦች ሥምና ኮድ ዝርዝር በሚከተሉት ገፆች ቀርበዋል፡፡ ይኸን በመገንዘብ የብሄረሰብ ስምና ኮድ አመዘጋገብ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

1.

ለብሄረሰብ መፃፊያ በተሰጠው ቦታ መልስ ሰጪው የሰጠው የብሄረሰብ ስም ይመዘገባል፡፡ የብ

ሂረሰባቸውን ስም ለመናገር ፈቃደኛ ያልሆኑ ግለሰቦች ካጋጠሙ በተቻለ መጠን አግባብቶ ትክክለኛ ውን መልስ ማግኘት ያስፈልጋል።

2.

መልስ ሰጭው ላስመዘገበው ብሄረሰብ የተሰጠው ትክክለኛ ኮድ የዋና ዋና ብሄረሰቦች ስምና ኮድ ዝርዝር በመመልከት በካርድ ኮለሞች ይመዘገባል። በዚህ ዝርዝር ውስጥ ብሄረሰቡን ለማግኘት አ ስቸጋሪ ከሆነ የቅርንጫፍ ብሄረሰቦች ስምና ኮድ ዝርዝር በመመልከት ለማግኘት ይቻላል።

3.

መልስ ሰጪው የሰጠው መልስ ዋናው/ግንድ ብሄረሰብ ወይም የግንድ ቅርንጫፍ ብሄረሰብ ሊ ሆን ይችላል። የተሰጠው መልስ ቅርንጫፍ ብሄረሰብ ከሆነ ቅርንጫፍ ብሄረሰቡ የየትኛው ዋና ወይም ግንድ ብሄረሰብ አካል እንደሆነ በመለየት የሚሰጠው ኮድ የዋናው ወይም የግንድ ብሄረሰብ ኮድ ይሆ ናል። ለምሳሌ በዓምዱ የተመዘገበው ብሄረሰብ ስም ጋይንቴ ቢሆን ግንዱ አማራ ስለሆነ በካርድ ኮለ ሙ የሚሞላው «04» ነው። ይኸውም የአማራ ብሄረሰብ መለያ ኮድ ነው። በዓምዱ የተመዘገበው የ ብሄረሰብ ስም እነቀር ቢሆን ግንዱ ጉራጌ ስለሆነ በካርድ ኮለሙ «25» ... ወዘተ ይሞላል።

## ሀ. <u>የዋና ዋና ብሄረሰቦች ስምና ኮድ ዝርዝር</u>

በዚህ ዝርዝር ውስጥ ሁሉም ብሄረሰቦች የቀረቡ ሲሆን አቀማመጣቸውም ዋና ዋና ብሄረሰቦችን በመ ጠቀም ነው። የዋናው ብሔረሰብ ሞክሼ ስሞችና ቅርንጫፍ ብሄረሰቦች ከዋናው ብሄረሰብ ጋር ተመሣ ሣይ ኮድ ስለሚሰጣቸው በቅንፍ ውስጥ ቀርበዋል። ለምሳሌ አዳል፣ ደናኪል፣ ደንከል፣ ጠልጣል የሚባለ - ቅርንጫፍ ብሔረሰቦች ሁሉ አፋር በሚባል ዋና ብሔረሰብ ስር የሚጠቃለሉ በመሆናቸው በዝርዝሩ ም ውስጥ አፋር እንደ ዋና ብሄረሰብ ተፅፎ ሌሎቹ በቅንፍ ውስጥ ቀርበዋል። የብሄረሰብን መረጃ በት ክክል ለመመዝገብ እንዲያመች ተመሣሣይነት ያላቸው ብሄረሰቦች ሁሉ ዋነኛውን ብሄረሰብ ተከትለው በዝርዝሩ ላይ ትንሽ ገባ እየተደረጉ የቀረቡ ሲሆን ለነዚህም የራሳቸው የተለየ ኮድ ተሰጥቷቸዋል። ለምሳሌ ዶርዜ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ኮንታ፣ ኩሎ፣ መሎ የሚባሉ ብሔረሰቦች ከወላይታ ብሔረሰብ ጋር በጣም ስለሚቀራረቡ በዝርዝሩም ውስጥ ከወላይታ ቀጥሎ በተከታታይ ቀርበዋል ነገር ግን እነዚህ ብሔረሰቦ ች ሁሉ ራሳቸውን የቻሉ የተለያየዩ ብሄረሰቦች ስለሆኑ የየራሳቸው ኮድ ተሰጥቷቸዋል። ዋና ዋና ብሔ ረሰቦችን በቀላሉ ከዝርዝሩ ለማግኘት እንዲቻል አቀማመጣቸው የተዘጋጀው የእንግሊዘኛውን ፊደል ቅደም ተከተል መሠረት በማድረግ ነው።

## ለ. <u>የቅርንጫፍ ብሄረሰቦች ስምና ኮድ ዝርዝር፤</u>

ይህ ዝርዝር የተዘጋጀው በዋና ዋና ብሄረሰቦች ሥምና ኮድ ዝርዝር ውስጥ በቅንፍ ውስጥ የቀረቡትን ሞክሼ ስሞች ወይም ቅርንጫፍ ብሄረሰቦችን (ለምሳሌ፣ ኤወሬ፣ አልደ፣ ሙርሲ፣ ) እንዲሁም በዝር ዝሩ ላይ ትንሽ ገባ ብለው የቀረቡትን ብሔረሰቦች (ለምሳሌ ዶርዜ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ኮንታ፣ ኩሎ፣ መሎ) በእንግሊዘኛ ፊደል ቅደም ተከተል መሠረት በማቅረብ ነው። በዋና ዋና ብሄረሰብ ሥምና ኮድ ዝርዝ ር ውስጥ ትንሽ ወጣ ብለው በእንግሊዝኛ ፊደል ቅደም ተከተል መሠረት የቀረቡት ዋና ዋና ብሔረ ሰቦች ግን (ለምሳሌ፣ ኤርቦሬ፣ ወላይታ) በዚህኛው ዝርዝር ውስጥ በድጋሚ አልቀረቡም።

4.

ከተጠቀሱት ዋና ዋና ብሄረሰቦችና ቅርንጫፍ ማህበረሰቦች ውጭ ካጋጠሙ የብሄረሰቡ ስም በ ዓምዱ ተጽፎ የሚሰጠው ኮድ ግን ለሌሎች የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች የሚሰጥ ኮድ «90» ይሆናል።

5.

ከሁለት የተለያዩ ኢትዮጵያውያን ብሔረሰቦች ወይም ከኢትዮጵያዊያንና ከውጭ አገር ዜጎች የተወለዱ ግለሰቦች ዕድሜያቸው 18 ዓመትና በላይ ከሆነ እነሱ የመረጡት የብሄረሰብ ስም በዓምዱ ይመዘገባል። ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ከሆነ ግን ወላጅ ወይም አሳዳጊ የወሰነው የብሄረሰብ ስ ም በዓምዱ እንዲፃፍ ያስፈልጋል።

6.

ከተለያዩ የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ለተወለደና ከአባቱና ከእናቱ ብሄረሰብ አንዱን ለይቶ ለመና

ገር ለማይፈልግ የሁለት ብሄረሰቦች ስም ተጽፎ ከተለያዩ ብሄረሰቦች የተወለዱ የሚለው ኮድ «91» ይሞላል፡፡ ከእናታቸው ወይም ከአባታቸው ብሄረሰብ አንዱን መርጠው ለመናገር ፈቃደኛ ለሆኑ ግን የመረጡት ብሄረሰብ ስም ተመዝግቦ የብሄረሰቡ ኮድ ይሞላላቸዋል፡፡

7.

ኤርትራዊያን ለሆኑ ሁሉ በዓምዱ «ኤርትራዊ» ተብሎ ተመዝግቦ ኮድ «93» በካርድ ኮለሞ ቹ ይመዘገባል፡፡ እንዲሁም ለጅቡቲያውያን ኮድ «94» ይሰጣቸዋል፡፡ ለሱማሊያ አገር ዜጎች «ሶማሊያ ዊ» ተብሎ ተመዝግቦ ኮድ «95» በካርድ ኮለሞቹ ይመዘገባል፡፡ ይህ ኮድ ግን የሚመዘገበው ኢትዮጵ ያውያን ሳልሆኑ ብቻ እንደሆነ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ለኢትዮጵያዊያን ሶማሌዎች የሚመዘገበው «ሶ ማሌ» የሚል መልስ ሲሆን የሚሰጣቸውም ኮድ «68» ነው፡፡ ለኬንያውያን ኮድ 96 ለሱዳናዊያን ኮ ድ 97 የሚመዘገብ ሲሆን ለሌሎች የውጭ አገር ዜጎች ሁሉ የአገራቸው ስም ተመዝግቦ ኮድ 98 ይሰ ጣቸዋል፡፡

ዓምድ 17-21 <u>የፍልሰት ሁኔታ</u>

ዓምድ 17 <u>ለከተማ፡ እዚህ ____ ከተማ ውስጥ ያለማቋረጥ ስንት ዓመት ኖረዋል?</u>
<u>ለገጠር፡ እዚህ _____ ወረዳ ገጠር ውስጥ ያለማቋረጥ ስንት ዓመት ኖረዋል?</u>

በዚህ ዓምድ በጥናቱ የሚሸፈኑ የቤተሰብ አባላት ሁሉ ጥናቱ በሚካሄድበት ከተማ (ወረዳ ገጠር ክፍል) ክፍል ከመቼ ጀምረው በመኖር ላይ እንደሚገኙ ተጠይቀው መልሱ ይመዘገባል:: በገጠር እና በከተማ ቆጠራ ቦታ ዎች ይህ ጥያቄ ሲቀርብ እንደሁኔታው «እዚህ__ ከተማ ... » «እዚህ ወረዳ ገጠር ...» እየተባለ ተለይቶ መ ሆን አለበት እንጂ መጠይቁ ላይ ያለውን ጥያቄ እንዳለ ማንበብ አያስፈልግም:: ግለሰቡ በከተማው (ወረዳው ገጠር ክፍል) ውስጥ ተወልደው እስከጥናቱ ቀን ድረስ ከከተማው (ወረዳው ገጠር) ውጭ ኑረው የማያውቁ ከ ሆነ «ከልደት ጀምሮ» የኖሩ በመሆኑ በካርድ ኮለሙ ኮድ "8" ይሞላል:: አንዳንድ ግለሰቦች ከከተማው (ወረዳ ው ገጠር ክፍል) ውጭ በሚገኝ ሆስፒታል ቢወለዱም የተወለዱበት ሥፍራ ተብሎ የሚቆጠረው የመኖሪያ ሥ ፍራቸው እንጂ ሆስፒታሉ የሚገኝበት ሥፍራ አይደለም:: በተመሳሳይ መልክም እናትየው ዘመዶቿ በሚኖሩበ ት አካባቢ ልጅ ወልዳና ታርሳ ብትመለስ ልጁ የተወለደበት ሥፍራ ተብሎ የሚቆጠረው የቤተሰቡ መደበኛ መኖሪያ ሥፍራ እንጂ የእናትየው ዘመዶች የሚገኙበት ሥፍራ አይደለም::

ከተወለዱ ጀምሮ በከተማው (በወረዳው ገጠር ክፍል) ውስጥ ላልኖሩ ግለሰቦች በከተማው (በወረዳው ገጠር ክፍል) ውስጥ ያለማቋረጥ መኖር ከጀመሩ ምን ያህል ዓመታት እንደሆናቸው ተጠይቀው ተገቢው ኮድ በተሰጠው ካርድ ኮለም ይመዘገባል:: ያለማቋረጥ የኖሩት ዓመት የሚሰላው በጨረሱት ሙሉ ዓመት ነው:: ለ ምሳሌ ሶስት ዓመት ከአስራ አንድ ወር ለሆናቸው ያለማቋረጥ ኖሩ የሚባለው ሶስት ዓመት ሲሆን የሚሰጠው ም ኮድ 3 ይሆናል:: በዚህ ዓምድ በካርድ ኮለሙ የሚመዘገበው የጨረሱት ሙሉ ዓመት የሚያሳየው ኮድ ነው :: ከተወለዱ ጀምሮ ያለማቋረጥ በከተማው (ወረዳ ገጠር ክፍል) ውስጥ ያልኖሩ የሚባሉት ግለሰቦች በሁለት መልክ ይከፈላሉ:: እነዚህም፡-

1ኛ/ ከከተማው (ከወረዳው ገጠር ክፍል) ውጭ የተወለዱ እና

2ኛ/

ለገጠር ቆጠራ ቦታዎች በወረዳው የገጠር ክፍል ውስጥ ተወልደው በመሀሉ ከወረዳው ገጠር ክፍል ውጪ ወይም በወረዳው ውስጥ በሚገኙ ከተማዎች ወይም ሌላ ወረዳ ሲኖሩ ቆይተው የተመለ ሱ ናቸው:: ለከተማ ቆጠራ ቦታዎች በከተማው ውስጥ ተወልደው በመሀሉ በወረዳው ገጠር ክፍል ወይም በሌላ ወረዳ ሲኖሩ ቆይተው የተመለሱ ናቸው:: ይህም ማለት ለጥቂት ጊዜ ብቻ ወጥተው የተ መለሱ ግለሰቦች ሳይሆኑ ለስድስት ወርና በላይ ለሆነ ጊዜ ሌላ ሥፍራ ቆይተው የተመለሱ ናቸው::

በአንደኛ ተራ ቁጥር ለተጠቀሱት ግለሰቦች ያለማቋረጥ የኖሩበት ጊዜ የሚገለፀው ወደ ከተማው (ወረ ዳው የገጠር ክፍል) ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ጥናቱ ቀን የጨረሱትን ሙሉ ዓመት በማስላት ይሆናል:: በሁ ለተኛ ተራ ቁጥር ለተጠቀሱት ደግሞ የሚገለጸው ወደ ከተማው (ወረዳው የገጠር ክፍል) ተመልሰው ከመጡ በኋላ እስከ ጥናቱ ዕለት ያለማቋረጥ ያጠናቀቁትን ሙሉ ዓመት በማስላትና ከተሰጡት ኮዶች ጋር በማገናዘብ ይሆናል:: ለገጠር ይህ ጥያቄ የሚመለከተው በወረዳው የገጠሩ ክፍል የኖሩበትን ጊዜ ስለሆነ በወረዳው ውስጥ ከሚገኝ ከተማ የመጡ አባላት ቢያጋጥሙ ከልደት ጀምረው በወረዳው የገጠር ክፍል እንደኖሩ አይቆጠርላቸ ውም:: በተመሣሣይ መልክም በወረዳው የገጠር ክፍል ተወልደውና እዝያው ሲኖሩ ቆይተው በመሐሉ በወረ ዳው ውስጥ በሚገኝ ከተማ ኑሮአቸውን መስርተው የነበሩ ግለሰቦች ወደ ወረዳው ገጠር ክፍል ቢመለሱ ከልደ ት ጀምሮ በወረዳው የገጠር ክፍል እንደኖሩ አይቆጠርላቸውም:: በዚህ ዓምድ ያለማቋረጥ በከተማው (በወረዳ ው የገጠር ክፍል) የኖሩበት ዓመታት ብዛት ተጠይቆ ሲመዘገብ አንድ መታወስ ያለበት ጉዳይ አለ:: ይህም አ ንዳንድ አባላት ጥናቱ በሚካሄድበት ከተማ (ወረዳ ገጠር ክፍል) መኖር ከጀመሩ በኋላ አንድ ጊዜ ወይም ከአ ንድ ጊዜ በላይ ሥፍራውን ትተው በሌላ ቦታ ኑሮ መስርተው ከቆዩ በኋላ ተመልሰው ወደ ከተማው (ወረዳው ገጠር ክፍል) ይመጣሉ:: ለነዚህ አባላት የሚመዘገብላቸው ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ከተማው (ወረዳው የገጠር ክ ፍል) ውስጥ እስከ ጥናቱ ዕለት የኖሩበት ዓመታት ብዛት እንጂ በተለያዩ ጊዜያት የኖሩባቸው ዓመታት ተደም ረው አይደለም:: በዓምዱ ለሚገኙ መልሶች የሚሰጣቸው ኮዶች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል::

<u>ኮድ</u>

0= ከአንድ ዓመት በታች በከተማው (በወረዳው የገጠር ክፍል) ያለማቋረጥ የኖሩ (አን ድ ዓመት ያልሞላቸው)

1= ለአንድ ዓመት በከተማው (በወረዳው የገጠር ክፍል) ያለማቋረጥ የኖሩ

2= ለሁለት ዓመት በከተማው (በወረዳው የገጠር ክፍል) ያለማቋረጥ የኖሩ
3= ለሶስት ዓመት በከተማው (በወረዳው የገጠር ክፍል) ያለማቋረጥ የኖሩ
4= ለአራት ዓመት በከተማው (በወረዳው የገጠር ክፍል) ያለማቋረጥ የኖሩ
5= ከአምስት እስከ ስድስት ዓመት በከተማው (በወረዳው የገጠር ክፍል ) ያለማቋረጥ የኖሩ
6= ከሰባት ዓመት እስከ ዘጠኝ ዓመት በከተማው (በወረዳው የገጠር ክፍል ) ያለማቋረጥ የኖሩ
7= ለአሥር ዓመትና ከዚያ በላይ በከተማው (በወረዳው የገጠር ክፍል ) ያለማቋረጥ የኖሩ
8= ከተወለዱ ጀምሮ በከተማው (በወረዳው የገጠር ክፍል) ያለሚቋረጥ የኖሩ

ከመልስ ሰጭዎች የሚገኘው መረጃ የሚመዘገበው ከላይ በተዘረዘሩት ኮዶች አማካኝነት በዓምዱ ስር በሚገኘው ካርድ ኮለም ነው። ያለማቋረጥ የኖሩት ከአንድ ዓመት በታች ከሆነ ለኮዱ መመዝገቢያ በተሰጠው ቦታ «0» ይመዘገባል። ከአምስት እስከ ስድስት ዓመት ለቆዩ የሚሞላላቸው ኮድ «5» ሲሆን ሰባት ዓመት፣ ስ ምንት ዓመትና ዘጠኝ ዓመት ለቆዩ ኮድ «6» ይመዘገባል። አሥር ዓመት ለቆዩና ከዚያ በላይ ለሆናቸው ሁሉ ኮድ «7» ይመዘገባል። ከልደት ጀምረው ለኖሩ ሁሉ ኮዱን ለመጻፍ በተሰጠው ቦታ ኮድ "8" ይመዘገባል።

## ዓምድ 18-21 በዓምድ 17 ከኮድ 0-4 ለተሞላላቸው ብቻ

በነዚህ ዓምዶች በዓምድ 17 ከኮድ 0-4 የተሞላላቸው (ከ5 በታች በከተማው (በወረዳው የገጠር ክፍል) ያለ ማቋረጥ ለኖሩ) የሚቀጥሉትን የፍልሰት ሁኔታ የሚያመለክቱ ጥያቄዎች ሲጠየቁ ከኮድ 5-8 የተሞላላቸው ግን የፍልሰት ሁኔታን ሳይጠይቁ ወደ ዓምድ 22 በቀጥታ ይሻገራሉ።

## ዓምድ 18 **ለከተማ: <u>እዚህ___ ከተማ ከመምጣትዎ በፊት የትኛው ክልል ነዋሪ ነበሩ?</u>**

**ለገጠር: <u>እዚህ___ ወረዳ ገጠር ክፍል ከመምጣትዎ በፊት የትኛው ክልል ነዋሪ ነበሩ?</u>**

ከዚህ ከተማ (ወረዳው ገጠር ክፍል) ያለማቋረጥ መኖር ከመጀመሩ 5 ዓመት ላልሞላቸው (በዓምድ 1 7 ከኮድ 1-4 ለተሞላላቸው) እዚህ ከተማ (ወረዳ ገጠር ክፍል) ከመምጣታቸው በፊት ይኖሩበት የነበ ረው ክልል ተጠይቆ በሚከተሉት ኮዶች አማካይነት ይሞላል።

| | |
|---|---|
| *01= ትግራይ ክልል* | *07= ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል* |
| *02= አፋር ክልል* | *12= ጋምቤላ ክልል* |
| *03= አማራ ክልል* | *13= ሐረሪ ክልል* |
| *04= ኦሮሚያ ክልል* | *14= አዲስ አበባ* |
| *05= ሶማሌ ክልል* | *15= ድሬዳዋ* |
| *06= ቤንሻንጉል-ጉምዝ ክልል* | *16= ከኢትዮጵያ ውጭ* |

## ዓምድ 19 **ለከተማ<u>: እዚህ___ ከተማ ከመምጣትዎ በፊት የትኛው ዞን ነዋሪ ነበሩ?</u>**

**ለገጠር<u>: እዚህ ወረዳ ገጠር ክፍል ከመምጣትዎ በፊት የትኛው ዞን ነዋሪ ነበሩ?</u>**

በዚህ ዓምድ በከተማው (በወረዳው ገጠር ክፍል) ከተወለዱ ጀምሮ ያለማቋረጥ ላልኖሩ እና ከዚህ ከተማ (ወ ረዳው ገጠር ክፍል) ያለማቋረጥ መኖር ከመጀመሩ 5 ዓመት ላልሞላቸው (በዓምድ 17 ከኮድ 1-4 ለተሞላላቸ ው) እዚህ (ወረዳው ገጠር ክፍል) ከተማ ከመምጣታቸው በፊት ይኖሩበት የነበረው ዞን ተጠይቆ በዓምዱ ክፍ ት ቦታ ይሞላል። የዞኖች ዝርዝርና ኮድ በዚህ መመሪያ በአዝል - 2 ተያይዟል።

## ዓምድ 20 *<u>ቀድሞ ይኖሩበት የነበረው ሥፍራ ከተማ ነበር ወይስ ገጠር</u>* ?

በዚህ ዓምድ ከተወለዱ ጀምሮ በከተማው (በወረዳው የገጠር ክፍል) ይኖሩ ካልነበሩት ውስጥ በከተማ ው (በወረዳው ገጠር ክፍል) መኖር ከጀመሩ 5 ዓመት ላልሞላቸው የቤተሰብ አባላት ሁሉ በመጨረሻ ይኖሩበት የነበረው ሥፍራ ተጠይቆ ከተማ ከነበረ የከተማው ስም በዓምዱ ክፍት ቦታ ይጻፋል። ሥ ፍራው ገጠር ከነበረ ግን «ገጠር» የሚለው ቃል ይፃፋል። በሁለትና ከሁለት በላይ በሆኑ ሥፍራዎ ች ሲኖሩ ቆይተው ጥናቱ ወደሚካሄድበት ወረዳ ለመጡ አባላት የሚመዘገብላቸው ለመጨረሻ ጊዜ በ መደበኛነት ይኖሩበት የነበረው ሥፍራ ነው። በውጭ አገር ይኖሩ ለነበሩ ሥፍራው ገጠር ከነበረ «ገ

ጠር» ሲፃፍ ሥፍራው ከተማ ከነበረ «ከተማ» የሚለው ቃል ይፃፋል:: በተጨማሪ በሀገር ውስጥ ይኖ ሩ ለነበሩና ይኖሩበት የነበረውን ከተማ ስም በትክክል ለመናገር ላልቻሉ «ከተማ» የሚለው ቃል ተ መዝግቦ በመጠይቁ ግርጌ ማብራሪያ ይፃፋል::

**ዓምድ 21** ***<u>የቀድሞ መኖሪያዎን ለመልቀቅ ያበቃዎት ምክንያት ምንድነው?</u>***

በዚህ ዓምድ ከተወለዱ ጀምሮ በከተማው (በወረዳው የገጠሩ ክፍል) ይኖሩ ካልነበሩት የቤተሰብ አባላ ት ውስጥ በከተማው (በወረዳው ገጠር ክፍል) ያለማቋረጥ የኖሩት ከ5 ዓመት በታች የሆናቸው (በዓ ምድ 17 ከኮድ 1-4 ለተሞላላቸው) የቀድሞ መኖሪያ ቦታቸውን የለቀቁበት ምክንያት ተጠይቆ በሚከ ተሉት ኮዶች አማካኝነት ይመዘገባል::

01= <u>በትምህርት:-</u> ትምህርት ለመማር ብለው የቀድሞ መኖሪያቸው የለቀቁ፣

02= <u>በጋብቻ መመሥረት:-</u> ጋብቻ በመመስረታቸው ምክንያት ከባለቤታቸው ጋር ለመኖር ሲሉ

የቀድሞ መኖሪያቸውን የለቀቁ፣

03= <u>በጋብቻዬ መፍረስ:-</u> ጋብቻቸው በፍቺ ወይም በሞት ምክንያት በመፍረሱ ምክንያት የቀድሞ መኖሪያቸውን የለቀቁ፣

04= <u>ሥራ ፍለጋ:-</u> ሥራ ለመፈለግ ብለው ከቀድሞ መኖሪያቸውን የለቀቁ፣

05= <u>ሥራ ዝውውር/ በማግኘት:-</u> የሥራ ቦታቸውን ቀይረው ወይም ሥራ በማግኘታቸው የቀድሞ

መኖሪያቸውን የለቀቁ፣

06= <u>በመፈናቀል:- በጦርነት፣ ድርቅ ...ወዘተ</u> ተፈጥሮአዊ ወይም ሰውሰራሽ በሆነ ምክንያት የቀድሞ መኖሪያቸውን የለቀቁ፣

07= <u>ከቤተሰብ ጋር:-</u> ቤተሰባቸው ከቀድሞ መኖሪያ በመልቀቅ አብረው የመጡ፣

08= <u>ወደ ቤተሰብ /ቤት መመለስ:-</u> ከሄዱበት ቦታ በተለያዩ መንስኤዎች ወደ ቤታቸው /ቤተሰባቸው የተመለሱ፣

09= <u>የመሬት ችግር:-</u> የቀድሞ መኖሪያቸው የመሬት እጦት ያለባቸው ወይም መሬቱ ምርት አልሠጥም ስላለ ወይም ከመሬት ጋር በተያያዘ ምክንያት የለቀቁ፣

10= <u>ሌላ /ይገለፅ):-</u> ከላይ ከተዘረዘሩት ምክንያቶች በተለየ ምክንያት የቀድሞ ቦታቸውን የለቀቁ፣

**ዓምድ 22-23** ***<u>የትምህርት ሁኔታ</u>*** (ዕድሜአቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆናቸው አባላት ብቻ የሚጠየቅ)

**ዓምድ 22** ***<u>ማንበብና መፃፍ ይችላሉ?</u>***

በዚህ ዓምድ ዕድሜአቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆናቸው የቤተሰቡ አባላት ማንበብና መፃፍ መቻላቸው ን ይጠየቃሉ:: መልስ ሰጪው ማንበብና መፃፍ እችላለሁ (አዎን) ካሉ ኮድ «1» ይመዘገባል:: አንድ ግለሰብ የ ማንበብና የመፃፍ ችሎታ አለው የሚባለው ቢያንስ በአንድ ቋንቋ አንብቦ መረዳትና እንዲሁም መፃፍ ሲችል ነ ው:: የራሳቸውን ስም ወይም ቁጥሮችን ብቻ ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ግለሰቦች የትምህርት ችሎታ እንዳላቸ ው አይቆጠሩም:: እንዲሁም ሃይማኖት ነክ የሆኑና ቀደም ብለው በቃል የተጠኑ ዓረፍተ ነገሮች ብቻ መድገም የሚችሉ የማንበብና የመፃፍ ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም:: መልስ ሰጪው ማንበብና መፃፍ «አልችልም» ካሉ ኮድ «2» ይመዘገባል::

## ዓምድ 23 የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል ስንተኛ ነው?

ዕድሜያቸው 5 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑ የቤተሰቡ አባላት (በዓምድ 22 ኮድ 1 ለተሞላላቸው) በ መጀመሪያ የፈፀሙት ከፍተኛ ክፍል ተጠይቆ መልሱ በዓምዱ ውስጥ ተመዝግቦ በካርድ ኮለሞቹ ከታች በተገለ ፀው መሠረት ተስማሚው ኮድ ይሞላል።

የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል ሲባል ግለሰቡ ባለው የትምህርት ሥርዓት በመደበኛ ትምህርት በዩኒቨርስቲ በማሰልጠኛ ተቋምና በመሳሰሉት በመማር ላይ ያሉትን ወይም ከዚህ በፊት ተምረው ያጠናቀቁትን ከፍተኛ የ ትምህርት ክፍል የሚያመለክት ነው።

## የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል

| | ኮድ በፊደል | የክፍል ደረጃ |
|---|---|---|
| 01 = | አንደኛ | የአንደኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁና ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሁሉ፧ |
| 02 = | ሁለተኛ | የሁለተኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁና ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሁሉ፧ |
| 03 = | ሶስተኛ | የሶስተኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁና ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሁሉ፧ |
| 04 = | አራተኛ | የአራተኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁና ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሁሉ፧ |
| 05 = | አምስተኛ | የአምስተኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁና ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሁሉ፧ |
| 06 = | ስድስተኛ | የስድስተኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁ፧ |
| 07 = | ሰባተኛ | የሰባተኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁ፧ |
| 08 = | ስምንተኛ | የስምንተኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁ፧ |
| 09 = | ዘጠነኛ | የዘጠነኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁ፧ |
| 10 = | አሥረኛ | የአስረኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁ፧ |
| 11 = | አሥራ አንደኛ | የአስራ አንደኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁ፧ |
| 12 = | አሥራ ሁለተኛ | የአሥራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁ፧ |

20 =

<u>ሰርተፊኬት፧</u> ከ12ኛ ክፍል በላይ ከመደበኛ ትምህርት ቤቶች ወይም በከፍተኛ ትምህርት መስጫ ከታ ወቀ ተቋሞች (ኮሌጆች) ዩኒቨርስቲዎች ወይም ከተመሳሳይ ትምህርት መስጫ ተቋም ዲፕሎም ወይም ዲግሪ ለ ማስገኘት ባልታቀደ ፕሮግራም ቢያንስ የአንድ ዓመትና ከዚያ በላይ ትምህርት ለፈፀሙ ሁሉ ፕሮግራሙን አ ጠናቀው ሰርተፊኬት የተቀበሉ ሁሉ በዚህ ኮድ ይጠቃለላሉ። ከታች ከሀ-ደ ከተዘረዘሩት ውጭ የተከታተሉት ትምህርት ወይም ያገኙት ሰርተፊኬት በዚህ ዓምድ በኮድ 20 ይመዘገባል።

21 =

<u>ዲፕሎም ያልጨረሱ፧</u> ከአሥራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርት በላይ በከፍተኛ ትምህርት መስጫ ከታወቀ ተ ቋም ወይም ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርስቲ ወይም ከተመሳሳይ ትምህርት መስጫ ተቋም ዲፕሎም ለማስገኘት በታ ቀደ የትምህርት ፕሮግራም የአንድ ዓመትና ከዚያ በላይ ትምህርት ያጠናቀቁ ግን ዲፕሎም ላላገኙ ሁሉ።

22 =

<u>ዲግሪ ያልጨረሱ፧</u> ከአሥራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርት በላይ የመጀመሪያ ዲግሪ (ቢ.ኤ፧ ቢ.ኤስ.ሲ) ያስ ገኛል ተብሎ በታቀደ የትምህርት ፕሮግራም በኮሌጅ ወይም በዩኒቨርስቲ (በሚቀጥለው ከገጽ ከ«ሀ-ደ» በተዘረ ዘሩት ውስጥ) የአንድ ዓመት ወይም የበለጠ ትምህርት ላጠናቀቁ ግን ዲግሪ ላላገኙ ሁሉ፧

23 =

<u>ዲፕሎም፧</u> በከፍተኛ ትምህርት መስጫ ተቋም (ኮሌጅ) ዩኒቨርስቲ ወይም ተመሳሳይ ትምህርት መስጫ ተቋም ከታች ከ«ሀ-ደ» በተዘረዘሩት ውስጥ) ዲፕሎም ላገኙና ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ ላላቸው ሁሉ፧

24 = ***ዲግሪ፡***

*የመጀመሪያ ዲግሪ (የሕክምና ዲግሪ ቢ.ኤ፣ ቢ.ኤስ.ሲ፤ ኤል.ኤል.ቢ.) ላገኙና ተመሳሳይ የትምህርት ደ ረጃ ላላቸው ሁሉ።*

25 =

***ከዲግሪ በላይ፡*** *በዩኒቨርስቲ የመጀመሪያ ዲግሪ ካገኙ በኋላ በድህረ ምረቃ ፕሮግራም የማስተርስ ወይ ም የዶክትሬት ዲግሪ ላገኙ በድህረ ምረቃ ፕሮግራም ቢያንስ የአንድ ዓመት ትምህርት ላጠናቀቁ፣*

95 =

***መሠረተ ትምህርት፡*** *በመሠረተ ትምህርት ፕሮግራም ማንበብና መፃፍ ችለው በሌላ ቦታ ትምህርት ላ ልቀጠሉ ሁሉ፣*

96 =

***መደበኛ ያልሆኑ፡*** *የቄስ፣ የቁርዓንና የመሳሰሉት ትምህርት ቤቶች በመማር ማንበብና መፃፍ የሚችሉ (ትምህርታቸው ወደ መደበኛ የትምህርት ደረጃ አመዳደብ ሊተረጎም የማይችል)። እንደዚሁም በራሳቸው ጥ ረት የግለሰቦችን ዕርዳታ እየጠየቁ ማንበብና መፃፍ የቻሉ ምንም እንኳን በዓምድ 22 ኮድ 1 ቢሞላላቸውም እ ዚህ ይመደባሉ። በተጨማሪም በመደበኛ ት/ቤት አንደኛ ክፍል ያላጠናቀቁ ሆነው ነገር ግን ማንበብና መፃፍ የሚችሉ በዚህ ክፍል ይካተታሉ። እንዲሁም የመሠረተ ትምህርት በመከታተል ላይ የሚገኙ (ፕሮግራሙን ያላ ጠናቀቁ) ሆነው ማንበብና መፃፍ የሚችሉትንም ያጠቃልላል።*

***ማስታወሻ፡*** *በሀገሪቱ የታወቁ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም (ኮሌጅ) ዩኒቨርስቲ የሚባሉት፡-*

*ሀ/ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ሳይንስ ፋኩልቲ፣ የቋንቋ ጥናት ኢንስቲተዩት፣ ሶሻል ሳይንስ ኮሌጅ፥ ቴክኖሎጂ ፋኩልቲ፣ ፋርማሲ፣ የትምህርት ፋኩልቲ፣ ሕግ ፋኩልቲ፣ የከብት ሕክም ና ፋኩልቲ፣ የሕክምና ፋኩልቲ፣ ላይብረሪ ሳይንስ፣ ድህረ ምረቃ፣ ...ወዘተ)*
*ለ/ ጎንደር ሕክምና ኮሌጅ፣*
*ሐ/ ባህር ዳር መምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጅ፣*
*መ/ አዋሳ እርሻ ኮሌጅ*
*ሠ/ አለማያ ዩንቨርስቲ (የእርሻ ፋኩልቲ፣ የደን ጥናት ፋኩልቲ እና የግብርና ሳይንስ የ ድህረ ምረቃ ፕሮግራም)*
*ረ/ አምቦ እርሻ ኮሌጅ*
*ሰ/ አዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ*
*ሸ/ ጅማ እርሻ ኮሌጅ*
*ቀ/ ባህር ዳር ፖሊቴክኒክ ኢንስቲትዩት፣*
*በ/ ኮተቤ መምህራን ማሰልጠኛ፣*
*ተ/ ወንዶ ገነት ደን ጥናት ኮሌጅ፣*
*ቸ/ አርባ ምንጭ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስትትዩት፣*
*ኀ/ መቀሌ ቢዝነስ ኮሌጅ፣*
*ነ/ ኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ፣*
*ኘ/ ጅማ ጤና ሳይንስ ኢንስትቲዩት፣*
*አ/ ናዝሬት ቴክኒክ ኮሌጅ፣*
*ወ/ መቀሌ ዩንቨርስቲ ኮሌጅ፣*
*ገ/ ዲላ ጤናና ትምህርት ኮሌጅ፣*
*ደ/ ጎንደር መምህራን ኮሌጅ?*

*ከነዚህ ተቋሞች ውጭ የሚሰጡ ዲፕሎሞች (የምስክር ወረቀቶች) በኮድ «20» ይመዘገባሉ። (ለምሳሌ*

የካቲት 66 ፖለቲካ ት/ቤት፣ ዩኒቲ ኮሌጅ፣
ተግባረዕድ፣ መምህራን ማሰልጠኛ ተቋም፣ እንጦጦ አጠቃላይ ት/ቤት … ወዘተ)

**ዓምድ 24-26** <u>**የስልጠና ሁኔታ (ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆኑ ብቻ)፡-**</u>

እነዚህ ዓምዶች የሚመለከቱት ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ የሆናቸው የቤተሰብ አባላትን ብቻ ሲ ሆን በዓምዶቹም አማካይነት በጥናቱ ወቅት የሙያ /ቮኬሽናል (ቴክኒካል) ስልጠና አግኝተው እንደሆነ ካገኙ ደግሞ ከየት እንዳገኙት በእነዚህ ዓምዶች ይጠየቃሉ። ዕድሜያቸው 10 ዓመት ላልሞላቸው የቤተሰብ አባላት በዓምዶቹ ላይ «-» ይደረጋል።

**ዓምድ 24**

<u>**የሙያ (ቮኬሽናል/ቴክኒካል) ስልጠና ወስደውና አጠናቀው የምስክር ወረቀት ወይ ም ከዚያ በላይ አግኝተዋል?**</u>

-

በዚህ ዓምድ ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ የሆናቸው የቤተሰብ አባላት በሙሉ የሙያ ወ ይም ቮኬሽናል/ቴክኒካል ስልጠና ወስደው አጠናቀው እንደሆነ ይጠየቃሉ።

-

ለዚህ ጥናት ስልጠና ማለት በአሰልጣኙ ድርጅት ስልጠናውን ለመስጠት ጊዜ ተመድቦለት በ ክፍል ውስጥ ወይም ከክፍል ውጭ /PRACTICE/ ወይም ሁለቱን በማጣመር የተሰጠ እንደ ሆነ ነው። በዚህ ጥናት ስልጠና ሲባል መነሻ የመደበኛ ትምህርት ደረጃ የማይጠይቁትን ሁሉ ያጠቃልላል። ማለትም አንድ ሰው ትምህርት ሳይኖረውም በአንድ ሙያ ቢሰለጥን በሙያ እንዳ ሰለጠነ ይቆጠራል። የስልጠናው መስክም በማናቸውም ትምህርት በሚጠይቅ ወይም በማይጠ ይቅ የሙያ መስክ ሊሆን ይችላል ለምሳሌ አናፂ፣ ሽክላ ሥራ፣ ሕክምና፣ ምህንድስና …ወዘተ። ለጥያቄው አዎን ለመለሱ በካርድ ኮለሙ ኮድ 1 ይሞላል። የለም ለመለሱ ኮድ 2 ተሞልቶ ወደ ዓምድ 27 ይታለፋል።

ስልጠናው የምስክር ወረቀት ያስገኘ መሆን ስላለበት ስልጠና ለመውሰድ ጀምረው ስልጠናው ን ያቋረጡ ወይም ለምስክር ወረቀት የሚያበቃ ውጤት ለማግኘታቸው ማረጋገጫ ላላገኙ የሚሞላላ ቸው ኮድ 2 ነው።

ይህ ዓምድ ሲሞላ ከታች የተመለከቱትን ነጥቦች መረዳት ያስፈልጋል።

- እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ የቀለም ትምህርት የተማሩ በሙያ እንደሰለጠኑ አይቆጠርም፣
- በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሙያ ትምህርት ተምረው ያጠናቀቁና የምስክር ወረቀት ያገኙ በሙያ እንደሰለጠኑ ይቆጠራል፣
- ከ12ኛ ክፍል በላይ ((በዩኒቨርስቲ/ኮሌጅ/ተቋም …ወዘተ) በቀንም ሆነ በማታ ትምህርት ተምረው

  ያጠናቀቁና የምስክር ወረቀት ያገኙ በሙያ ትምህርት እንደሰለጠኑ ይቆጠራል
- የምስክር ወረቀት እስካገኙ ድረስ በመንግስታዊም ሆነ በግል ድርጅቶች የሚሰጡ ማናቸውም የአጭርም ሆነ የረጅም ጊዜ ስልጠናዎች እንደሙያ ስልጠና ይቆጠራሉ።

**ዓምድ 25** <u>**የሰለጠኑበት የሙያ (ቮኬሽናል/ቴክኒካል) ዓይነት ምንድነው?**</u>

በዓምድ 24 ላይ ስልጠና እንዳላቸው የገለፁ /ኮድ 1 የተሞላላቸው/ ሰዎች በዚህ ዓምድ የሰለጠኑበት ሙያ (ቮኬሽናል/ቴክኒካል) ዓይነት ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል:: በካርድ ኮለሞቹም ከታች ከተዘረዘሩት ውስጥ ተገቢው /ተቀራራቢው/ ኮድ ይሞላል::

01= ሸክላ ስራ
02= ሽመና
03= እንጨት ሥራ (የአናጢነት ስልጠናን ይጨምራል)
04= ኤሌክትሪክ ሥራ
05= ብረታ ብረት
06= መካኒክ (የመኪና፣ የሞተር ሳይክል፣ የአውሮፕላን ጥገናን ይጨምራል)
07= ግንበኝነት
08= ታይፕ
09= ልብስ ስፌት
10= ሹፌርነት
11= የልማት ተጠሪ /DA/
12= ልምድ አዋላጅ
13= ሕክምና - የሰው (ሕክምና-የሰው/ ድሬሰር፣ ነርስና ሜዲካል ዶክተሮችን ይይዛል)
14= ሕክምና - የእንስሳት (ሕክምና-የእንስሳት/ ረዳቶችንና ዶክተሮችን ይይዛል)
15=
ምሕንድስና የውሀ ጭምር (ምህንድስና/ ከሕንፃ ኮሌጅ፣ ከከተማፕላን ኮሌጅ ከአርባ ምንጭ ውሃ ቴክኖሎጂ እና ከዩኒቨርሲቲ በምህንድስና የተመረቁትን ይይዛል)
16= ኮምፒውተር ሳይንስ (ፕሮግራመር)
17= ኮምፒውተር አጠቃቀም
18= ማህበራዊ ሳይንስ (በትምህርት እና ትምህርት አስተዳደር፣ ዲሞግራፊ ጭምር)
19= ተፈጥሮ ሳይንስ (የሂሳብ እና ስታትስቲክስ ጭምር)
20=
ቢዝነስ ኢኮኖሚክስ፣ ባንኪንግ፣ ሒሳብ መዝገብ አያያዝ እና ሥራ አመራር (ንግድ ሥራ ኮሌጅ ከ መቀሌ ቢዝነስ ኮሌጅ የተመረቁትን ይጨምራል)
21= በግብርና ሳይንስ (ደን ጭምር)
22= በግብርና አነስተኛ ስልጠና ሙያ (ከአጋርፋ፣ አርዳይታ ባኮ፣ ወዘተ)
23= ሆቴልና ቱሪዝም
24= ሕግ
25= ፖሊስ
26= ውትድርና
27=
መምህርነት (ከመምህራን ማሰልጠኛ ፣ ከቴክኒክ መምህር ማሰልጠኛ ኮሌጅ፣ ከመምህራን ማሰልጠኛ ተቋም፣)
28= ሌላ (ይገለጽ)

ዓምድ 26 <u>*የሙያ ሥልጠናውን ከየት ነው ያገኙት?*</u>

*1 = ከዩኒቨርስቲ/ከኮሌጅ/ከተቋም**

2 =

ከቴክኒክና ሙያ ት/ቤት /ተግባረዕድ፣ዊንጌት፣ተፈሪመኮንን፣ጳበና እና በቅርብ የተከፈቱ የመንግስትና የግል የቴክኒክ ት/ቤቶች/

3 = ከአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

4 = ከአሠሪ ድርጅት ወይም መ/ቤት

5 = ከግብረሰናይ ድርጅት

6 = ከግል ማሰልጠኛ ድርጅት

7 = ሌላ '_ይገለፅ'

*_ተቋም ሲባል የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋሞች፣ አርዳይታና አጋርፋ ማሰልጠኛዎችን ይይዛል፡፡

-

ዋነኛ የሙያ ዓይነት ከፍተኛውን ማለት ሲሆን በእኩል ደረጃ ላሉ ስልጠናዎች ረጅም ጊዜ የወሰደው ይመረጣል፡፡ ለምሣሌ አንድ ሰው ከዩኒቨርስቲ በአካውንቲንግ ቢመረቅና በሌላ በኩል ደግሞ የኮምፒውተር አጠቃቀም ስልጠና ቢወስድ የሚያዝለት ከዩኒቨርስቲ የተመረቀበት ቢዝነስ ኢኮኖሚክስ የሚለው ኮድ 20 ነው፡፡

## ዓምድ 27 <u>የጋብቻ ሁኔታ</u>፡-

ይህ ዓምድ ዕድሜያቸው 10 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆናቸው የቤተሰብ አባላት ሁሉ መሞላት አለበት፡፡ ጋብቻ ማለት አንድ ወንድና ሴት በሕጋዊ ወይም በባሕላዊ መንገድ የጋብቻ ስነ ስርዓት ፈፅመው እንደ ባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ ነው፡፡

የጋብቻውን ሁኔታ ለማመልከት ከዚህ በታች የተመለከቱት የጋብቻ ዓይነቶችና ኮዶቻቸው ተሰጥተዋል፡፡

1= አግብተው የማያውቁ

ፈፅሞ ያላገባ ወይም ያላገባች እስከ ጥናቱ ቀን ድረስ አግብቶ ወይም አግብታ የማታውቅ ወይም የማያውቅ፣

2 = ባለትዳር

በጥናቱ ቀን በጋብቻ ላይ ያለ ወይም ያለች፣

3 = የተፋቱ

ከጥናቱ ቀን በፊት አግብቶ ወይም አግብታ የነበረ ነገር ግን ከጥናቱ ቀን በፊት በሕጋዊ ወይም በባሕላዊ መንገድ የተፋታ ወይም የተፋታች፣

4 = የሞቱባቸው

ባል የሞተባት ወይም ሚስት የሞተችበት ሆነው ከሞተባቸው በኋላ እስከ ጥናቱ ቀን ላገቡ፣

5 = የተለያዩ

ባልና ሚስት ባለመግባባት ምክንያት ጉዳያቸው በሽማግሌዎች በመታየት ላይ ያለ ወይም ፍርድ ቤት በቀጠሮ ላይ የሚገኙ፣

# ምዕራፍ 4 የክፍል 3፣ 4 እና 5 አሞላል መምሪያ

## ክፍል 3 ያለፉት 12 ወራት እና ያለፉት 7 ቀናት የሥራ ሁኔታ (ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው አባላት ብቻ)

*ማስታወሻ፡- የዚህ ክፍል መረጃዎች ከመሞላታቸው አስቀድሞ በመጠይቁ ራስጌ ላይ በተዘጋጀው ሥፍራ የተመረጠውን ቤተሰብ አድራሻና የአካባቢ መለያ ከገፅ 1 ክፍል 1 ማወራረስ ያስፈልጋል።*

በዚህ ክፍል የሚሰበሰቡ መረጃዎች ከጥናቱ ቀን በፊት በነበሩበት 12 ወራትና ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው የቤተሰቡ አባላት የተከናወኑ የኢኮኖሚ ተግባሮችን የሚመለከቱ ይሆናሉ።

### ዓምድ 11 እና 10፡-

ዓምድ 11 "ሙሉ ስም" እና ዓምድ 10 "የመስመር ቁጥር" የሚለው ከገፅ 1 ዓምድ 11 እና 10 ሁሉም የቤተሰብ አባላት ቀደም ተከተላቸውን እና የመስመር ቁጥራቸውን እንደጠበቁ የሚዛወሩበት ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ በሚቀጥሉት ክፍሎችም ዓምድ 11 እና ዓምድ 10 ላይ የሁሉም ቤተሰቦች አባላት ስምና የመስመር ቁጥር ከገጽ 1 ዓምድ 11 እና 10 ይገለበጣል። በክፍል 3፣ 4 እና 5 የሚቀርቡት ጥያቄዎች 10 ዓመትና በላይ የሆናቸው የቤተሰብን አባላት ብቻ ስለሚመለከቱ ዕድሜአቸው ከ10 ዓመት በታች ለሆናቸው የቤተሰብ አባላት ከስምና መስመር ቁጥር በስተቀር ከዓምድ 28-57 ያሉት ዓምዶች በ "__" ይታለፋሉ። ከገጽ 1 ዓምድ 14 ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ የሆናቸው የቤተሰብ አባላት በመለየት ሁሉም በእነዚህ ክፍሎች ሳይጠይቁ እንዳይዘለሉ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

## ክፍል 3ሀ - ያለፉት 12 ወራት የሥራ ሁኔታ

### ዓምድ 28

**ባለፉት 12 ወራት አብዛኛውን ጊዜ ለክፍያ ወይም ለትርፍ ወይም ለቤተሰብ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ተሰማርተዋል?**

በዚህ ዓምድ ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ የሆናቸው የቤተሰብ አባላት ያለፈውን 12 ወራት (የጥናቱ ዓመት ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል) ማለትም ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ለክፍያ ወይም ለትርፍ ወይም ለቤተሰብ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ተሰማርተው እንደነበር ይጠየቃሉ። በዚህ ጥያቄ አማካይነት ባለፉት 12 ወራት አብዛኛውን ጊዜ በምርታማ ተግባር የተሳተፉትንና ያልተሳተፉትን እንለያለን። ባለፉት 12 ወራት አብዛኛውን ጊዜ በምርታማ ተግባር ለተሳተፉት በዓምዱ በተሰጠው ክፍት ቦታ "ሠርቻለሁ" ይመዘገባል። በካርድ ኮለሙም ኮድ 1 ተሞልቶ ወደ ዓምድ 30 ይታለፋል። አብዛኛውን ጊዜ በምርታማ ተግባር ያልተሳተፉ ከሆነ "አልሠራሁም" ተመዝግቦ ኮድ 2 ይሞላላቸዋል።

የሥራ ሁኔታ መረጃን ለመሙላት ቀጥሎ የተሰጠውን የምርታማ ሥራን ትርጉምና ማብራሪያ እንዲሁም "ባለፉት 12 ወራት ውስጥ **አብዛኛውን ጊዜ**" ምን ማለት እንደሆነ ጠንቅቆ መረዳት ያስፈልጋል።

***ምርታማ ሥራ*** ማለት የሥራው ውጤት የሆነውን ሸቀጣ ሸቀጥ ወይም አገልግሎት በክፊል ወይም በጠቅላላ በገንዘብም ሆነ በዓይነት (በዕቃ) በመለወጥ ገቢ ለማግኘት ለገበያ ለማቅረብ ሲቻል ነው። በራስ፥ በቤተሰብ ይዞታ፥ በመንግሥታዊ፥ በሕዝባዊ ወይም በግለሰብ ቤት ወይም ድርጅት በቀን፥ በሳምንት፥ በወር ወይም በሥሩት መጠን ክፍያ ወይም ገቢ ለማግኘት ሥራ ከሠሩ እንደ ምርታማ ሥራ ይቆጠራል። በሌላ አገላለጽ ምርታማ ሥራ ለግል ወይም ለመንግስት ተቀጥሮ ወይም የግል ሥራ መስራት፣ መነገድ፣ የግብርና ሥራ፣ ለሽያጭ የሚሆኑ ዕቃዎችን ማምረት በቤተሰብ ድርጅት/እርሻ ውስጥ ያለክፍያ መስራት ተለማማጅነትን ያጠቃልላል ።

በምርታማ ሥራ ውስጥ የሚጠቃለሉ የማምረት ወይም አገልግሎት የመስጠት ተግባራት እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

ሀ.

ለሽያጭ የሚሆኑ ዕቃዎችን ማምረት ለምሳሌ፥ የፋብሪካ ውጤቶች፥ ሸክላ ማምረት ... ወዘተ ወይም በክፍያ አገልግሎቶችን ማቅረብ ለምሳሌ፥ ፀጉር ማስተካከል፣ የሽመና ሥራ፥ የጠላና የአረቄ ንግድ፥ ድለላ ...ወዘተ

ለ.

ለመንግሥት፥ ለሌላ ድርጅት ወይም ለግለሰብ በክፍያ የሚሠሩ ሥራዎች (ለምሳሌ ሐኪም፥ መምህር፥ ተቀጣሪ ገበሬ፥ እረኛ፥ ...ወዘተ)፥ በተጨማሪ ያለክፍያ ለመረዳዳት ወይም በዘመቻ የሚሠሩ (ለምሳሌ ምግብ ለሥራ፥ የደን ተከላ፥ የደቦ ሥራ፥ ... ወዘተ)

ሐ.

ለራስ የምግብ ፍጆታ ወይም ለሽያጭ ወይም ቋሚ ንብረት ለማከማቸት ሲባል የማምረት ተግባር፤ እነርሱም፡-

1. ለራስ መሠረታዊ ፍላጎት ፍጆታ ሲባል የምርት ቀዳሚ ውጤቶችን (Primary Products) የማምረት ተግባር፤ ለምሳሌ የተለያዩ ሰብሎች/ጥራጥሬ፥ ፍራፍሬ፥ ጥጥ፥ ወተት፥ ...ወዘተ/ማምረት፥ ዓሣ ማጥመድ፣ የማገዶ እንጨት መቁረጥና መልቀም፣

2. ከላይ በተራ ቁጥር 1 ያመረቱትን ምርት ለራስ ፍጆታ በማሰብ ወደ ሌላ ዓይነት ምርት የመለወጥ ተግባር፥ ለምሳሌ ፈትል መፍተል፣ ቅቤ/አይብ ማውጣት፣ በቆሎ መፈልፈል፣ እህል መፍጨት፣ የቤት ቁሳቁስ እንደ ወንበር፣ ጠረጴዛ ማዘጋጀት ወዘተ...፡፡ ያመረቱትን ቀዳሚ ምርት ለራስ ፍጆታ በማሰብ ወደ ሌላ ዓይነት ምርት መቀየር ምርታማ ተግባር ቢሆንም ይህን የተቀየረውን ምርት ለራስ ፍጆታ በማለት እንደገና ወደ ሌላ ዓይነት ምርት መቀየር ምርታማ አይደለም፡፡ በዚህ ዓይነት በቤተሰቡ አባላት የተመረተን ጤፍ ለራስ ፍጆታ በማለት ፈጭቶ ወደ ዱቄት መቀየር እንደምርታማ ተግባር ይቆጠራል፡፡ ነገር ግን ይህን የተፈጨውን ዱቄት ለራስ ፍጆታ በማለት ወደ እንጀራ መቀየር ምርታማ ተግባር አይደለም፡፡ በአንጻሩም ለራስ ፍጆታ ለማዋል በሌላ ሰው የተመረተን ምርት ለምሳሌ ጤፍ ወደ ዱቄትም ሆነ እንጀራ ቢቀየር እንደምርታማ ተግባር አይቆጠርም፡፡

3. ለራስ የምግብ ፍጆታ የሚመረቱ ዕቃዎችና ግልጋሎቶች ለሽያጭም ጭምር በቤተሰብ ሲመረቱ፥ ለምሳሌ ጠላ ጠምቀው (ከፊሉን ቢጠጡም) የሚሸጡ፥

4. ቋሚ ንብረቶችን (ቢያንስ ለአንድ ዓመት ያህል ግልጋሎት መስጠት የሚችሉ) ለራስ ጥቅም ሲባል ማምረት፥ ለምሳሌ የራስን ግቢ ወይም አካባቢ ግንባታ፥ የእርሻ ውጤት ማከማቻ መጋዘኖችንና የእርሻ መሣሪያዎችን መሥራት፥ ሌሎች መሣሪያዎችን ማምረት ናቸው፡

ባለፉት 12 ወራት ውስጥ <u>አብዛኛውን ጊዜ</u> (<u>አብዛኛውን ጊዜ ምን ማለት እንደሆነ ከታች ይብራራል</u>) ከላይ የተገለፁትን ምርቶች በማምረትና ግልጋሎቶችን በማቅረብ ተግባር ላይ የተሠማሩ ሰዎች በምርታማ ሥራ ላይ እንደተሠማሩ ይቆጠራሉ፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት የማምረት ወይም ግልጋሎት የመስጠት ተግባሮች ውስጥ ሊጠቃለሉ የማይችሉ ሥራዎች በጠቅላላ ምርታማ ያልሆኑ ሥራዎች በመባል ይታወቃሉ፡፡ ያለ ክፍያ ለቤተሰብ ግልጋሎት

የሚውሉ ሥራዎችን ለምሳሌ ልጆችን ማስተማር፥ ማሳደግ፥ ቤተሰቡ የሚመገበውን ምግብና መጠጥ ማዘጋጀት ፥ የራሳቸውን አጥር፥ ቤት፥ ... ወዘተ አነስተኛ የጥገና ተግባር ማከናወን፥ በበጎ ፈቃደኝነት ለአካባቢው ሕብረተሰብ በተለያዩ ማህበራት አነስተኛ ግልጋሎት መስጠት፥ ...ወዘተ እንደምርታማ ሥራ አይቆጠሩም። ሆኖም ከላይ የተገለፁት የቤት ውስጥ ሥራዎች ለክፍያ እስከተከናወኑ ድረስ በምርታማ ሥራ ክፍል ይመደባሉ። በልመና፥ በሴተኛ አዳሪነት (መጠጥ ደርድረውም ሆነ ሳይደረድሩ) የሚተዳደሩ ምርታማ ሥራ እንደሚሠሩ አይቆጠሩም። የቡና ቤት አሻሻጮች አብዛኛውን ጊዜ በሴተኛ አዳሪነት ተግባር ከተሠማሩ እንደሴተኛ አዳሪዎች ተቆጥረው ምርታማ ሥራ እንደሠሩ አይቆጠሩም። ነገር ግን በቡና ቤት ውስጥ ተቀጥረው የሚያገለግሉ ሌሎች ሠራተኞች /ለምሳሌ አልጋ አንጣፊ፥ ገንዘብ ተቀባይ፥ ቡናና ሻይ የሚያፈሉ (ባሬስታ)፥ ወጥ ቤት፥ የቡና ቤት ባለቤቶች፥ በትላልቅ ሆቴሎች በአስተናጋጅነት ሥራ የተሰማሩ፥ ...ወዘተ/ ምርታማ ሥራ እንደሠሩ ይቆጠራሉ። ለምሳሌ በመንግሥትና መሰል የግል ሆቴሎች ከማስተናገዱ ሥራ በተጨማሪ በሥራቸው ወቅት ሌላ የሴተኛ አዳሪነት ተግባር የሚከለክል ሕግ ባላቸው ሆቴሎች ውስጥ በአስተናጋጅነት ተቀጥረው የሚሰሩትን ያጠቃልላል። በተጨማሪም ሳይከፈላቸውም ሆነ እየተከፈላቸው የሥራ ልምምድ የሚያደርጉ (በቢሮ፥ በጋራዥ፥ ...ወዘተ) የሚሠሩት ሥራ እንደ ምርታማ ሥራ ይቆጠራል። የድርጅት ባለቤቶች በሥራው ምንም ተሳትፎ ከሌላቸው ባለቤት በመሆናቸው ብቻ ምርታማ ሥራ እንደሠሩ አይቆጠሩም። በተጨማሪም ቤት በማከራየት ብቻ ወይም በጡረታ ብቻ የሚተዳደሩ ምንም እንኳ ገቢ ቢያገኙም ምርታማ ሥራ እንደሠሩ አይቆጠሩም።

## <u>ባለፉት 12 ወራት ውስጥ “አብዛኛውን ጊዜ” ምን ማለት ነው?</u>

አንድ ግለሰብ ባለፉት 12 ወራት ምርታማ ሥራ ሠርቷል የሚባለው በተሰማራበት የሥራ መስክ/ኮች ከስድስት ወራት (ማለትም ከ26 ሳምንታት) በላይ ምርታማ ሊያሰኝ የሚችል ሥራ ከሠራ ነው። ይህ አጠቃላይ ትርጉም ሲሆን ሰዎች ከተሰማሩባቸው የተለያዩ የሥራ መስኮች ፀባይና ከየአገሩ ነባራዊ ሁኔታ ጋር አዛምዶ ከመጠቀም አኳያ ከአጠቃላይ ትርጉሙ ጋር ሊጣጣም በሚችል መልኩ ዘርዘር ያሉ የአሠራር መመሪያዎችን ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ ዝርዝሩ ከዚህ በታች ተመልክቷል።

ሀ.

አንድ በእርሻ ሥራ ለተሠማራ ግለሰብ ባለፉት 12 ወራት አብዛኛውን ጊዜ ምርታማ ሥራ ሠርቷል የሚባለው በአካባቢው በአንድ የሰብል ዘመን አብዛኛውን ጊዜ ከሠራ ነው። ለምሳሌ የአካባቢው አንድ የሰብል ዘመን 8 ወር ከሆነና ግለሰቡ ለአራት ወርና ከዛ በላይ የግብርናውን ሥራ ከሠራ ምርታማ ሥራ እንደሠራ ይቆጠራል። አንድ የሰብል ዘመን የሚባለው የመኸሩንና የበልጉን ወቅቶች የሚያጠቃልል ሲሆን የሚከናወኑትም ሥራዎች የእርሻውን መሬት ከማዘጋጀት አንስቶ የዘሩን፥ የጉልጓሎውን፥ የማረሙን፥ የአጨዳውንና የመሰብሰቡን ጊዜ ያጠቃልላል።

ለ.

ሌላ ግብርና፡- በከብት እርባታ፥ ንብ እርባታ፥ ...ወዘተ የተሰማሩ ግለሰቦች በተሰማሩበት የሥራ መስክ/ኮች ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ከ6 ወራት በላይ ከሠሩ ምርታማ ሥራ እንደሰሩ ይቆጠራሉ።

ሐ.

በገጠርም ሆነ በከተማ በሌሎች የሥራ መስኮች ማለትም ንግድ፥ ሽመና፥ አንጥረኝነት፥ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፥ ... ወዘተ. የተሠማሩ ግለሰቦች በተሠማሩበት የሥራ መስክ/ኮች ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ከ6 ወራት በላይ ከሠሩ ምርታማ ሥራ እንደሠሩ ይቆጠራሉ።

## ዓምድ 29 <u>ባለፉት 12 ወራት ስራ ያልሰሩበት ምክንያት ምን ነበር</u>?

በዚህ ዓምድ ባለፉት 12 ወራት አብዛኛውን ጊዜ በምርታማ ተግባር ላልተሰማሩ/በዓምድ 28 ኮድ 2 የተሞላላቸው/ ስራ ያልሰሩበት ምክንያት ተጠይቆ ከሚከተሉት ኮዶች ውስጥ አንዱ ይሞላላቸዋል።

0 =

<u>ሥራ አጥ/ፈላጊ:-</u> ባለፉት 12 ወራት አብዛኛውን ጊዜ ሥራ ያልሰሩና ስራ በመፈለግ ላይ የነበሩ ወይም ሥራ ቢያገኙ ሊሠሩ ዝግጁ የነበሩ፣

1 = <u>ያለክፍያ የቤት ውስጥ ሥራ ብቻ:-</u>

እነዚህ ግለሰቦች የገንዘብ ወይም የዓይነት ክፍያ ሳያገኙ ምግብ ማብሰል፣ ልብስ ማጠብ የመሳሰሉትን በቤት ውስጥ የሚሠሩ ሥራዎችን በመስራት ያሳለፉ ናቸው። የቤት እመቤት ሴቶች በዚህ ኮድ ይጠቃለላሉ።

2 = <u>ተማሪ</u> :-

እነዚህ ግለሰቦች ቀን ቀን ትምህርት በመከታተላቸው የተነሳ ባለፉት 12 ወራት አብዛኛውን ጊዜያቸውን ምርታማ ሥራ ያልሰሩ፣

3 = <u>አካል ጉዳት:-</u>

የአካል ጉዳት ወይም የአዕምሮ በሽታ ደርሶባቸው በዚህ ምክንያት ባለፉት 12 ወራት አብዛኛውን ጊዜ ሥራ ያልሰሩ፣

4 = <u>ህመም:-</u>

ባለፉት 12 ወራት አብዛኛውን ጊዜ በሕመም ምክንያት ያልሰሩ፣

5 = <u>ልጅ (ለሥራ ያልደረሱ)</u>:-

እነዚህ ግለሰቦች ምንም እንኳን ዕድሜአቸው ከ10 ዓመት በላይ ቢሆንም ባለፉት 12 ወራት አብዛኛውን ጊዜ በምርታማ ሥራ ያልተሰማሩ ሲሆን ያልተሰማሩበትን ምክንያት ሲገልፁ "ልጅ" በመሆናቸው የሚል መልስ የሚሰጡ ናቸው። ዕድሜአቸው 15 ዓመትና በላይ የሆኑ ይህ ኮድ ሊሰጣቸው አይችልም። በመማር ላይ ያሉ ልጆች የሚሞላላቸው ኮድ 02 እንጂ ልጅ ተብሎ ኮድ 05 አይደለም።

6 = <u>ሴተኛ አዳሪ:-</u>

ባለፉት 12 ወራት አብዛኛውን ጊዜ በሴተኛ አዳሪነት ሲተዳደሩ የነበሩ፣

7 = <u>ጡረተኛ/እርጅና:-</u>

ባለፉት 12 ወራት አብዛኛውን ጊዜ ሳይሠሩ በቤት አበል፣ ባጠራቀሙት ገንዘብ፣ በቤት ኪራይ ገቢ ወይም በቤተሰብ እርዳታ የሚተዳደሩ ናቸው። በጡረታ ወይም በእርጅና ምክንያት ሥራ ያልሠሩ በዚህ ኮድ ይጠቃለላሉ።

8 =

<u>ሌላ</u> ከላይ ከተዘረዘሩት በተለየ ምክንያት ሥራ ያልሠሩ ለምሳሌ በቤት ሠራተኛነት፣ በተለማማጅነት ልመና፣ ...ወዘተ.

## <u>ክፍል 3ለ- ያለፉት 7 ቀናት የሥራ ሁኔታ (ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው አባላት ብቻ)</u>

በዚህ ንዑስ ክፍል የሚሰበሰቡት መረጃዎች ከጥናቱ ቀን በፊት በነበሩት 7 ቀናት ውስጥ ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ የሆኑ በቤተሰቡ አባላት የተከናወኑ የኢኮኖሚ ተግባሮችን የሚመለከቱ ይሆናሉ። በዚህ ንዑስ ክፍል እና በተከታዩ ክፍሎች ውስጥ "ባለፉት 7 ቀናት" መረጃ ሰብሳቢው መልስ ሰጪው ቤት ደርሶ መጠይቁን ከሞላበት ቀን በፊት ያሉትን ሰባት ቀናት ይመለከታል። መልስ ሰጪውም ይህን ሀሳብ መረዳት አለባቸው። መረጃ ሰብሳቢው ለመልስ ሰ

ጪው "ባለፉት 7 ቀናት ከ___ ቀን እስከ___ ቀን" መሆኑን ማሣወቅ እና የቀኖቹን ስም እየጠራ ጥያቄውን ማቅረብ ይኖርበታል።

ዕድሜያቸው 10 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆናቸው የቤተሰብ አባላት ሁሉ፣ ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በምርታማ ተግባር ላይ ስለነበራቸው ተሣትፎ በዚህ ንዑስ ክፍል ይጠየቃሉ። በዚህ ንዑስ ክፍል በሚቀርቡ ጥያቄዎች አማካይነትም፣ ባለፉት 7 ቀናት በምርታማ ተግባር የተሣተፉ ግለሰቦች ብዛት፣ እና የሰሩት የሥራ ሰዓት መጠን መረጃ ይሰበሰባል።

በዚህ ንዑስ ክፍል የሚሰበሰቡ መረጃዎች በንዑስ ክፍል 3ሀ /ዓምድ 28 እና 29/ ከተሰበሰቡት የአሥራ ሁለት ወራትን ሁኔታ ከሚያመለክቱ መረጃዎች በተለየ ሁኔታ ስለሆነ፣ በዓምድ 28 እና 29 የተሰጡት መልሶች ሳይታዩ፣ ዕድ ሜያቸው አሥርና ከዚያ በላይ የሆኑ አባላት በጠቅላላ እንደ አዲስ በዚህ ክፍል የሚፈለጉትን መረጃዎች ያስመዘግባሉ። ይህም የሆነበት ምክንያት ባለፉት አሥራ ሁለት ወራት በአብዛኛው ጊዜ በምርታማ ተግባር ተሠማርቶ የነበረ የቤተሰ ብ አባል ባለፉት ሰባት ቀናት ግን በምርታማ ተግባር ያልተሠማራ ሊሆን ስለሚችል ነው። በተጨማሪም ባለፉት አሥራ ሁለት ወራት አብዛኛውን ጊዜ በምርታማ ተግባር ሳይሰማራ ቀርቶ ባለፉት ሰባት ቀናት ግን በምርታማ ተግባር የተሠ ማራ የቤተሰብ አባልም ሊያጋጥም ይችላል። ስለሆነም ጥያቄው ለመልስ ሰጪው ሲቀርብ የጥያቄዎቹን የጊዜ ገደብ ለመ ልስ ሰጪው ማስረዳትና መልሶቹም በዚህ ግንዛቤ መመለሳቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

**ዓምድ** 30

<u>ለመረጃ ሰብሳቢ :- ለመልስ ሰጭው የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንድ በአንድ አቅርበህ ቢያንስ በአንዱ የሥራ ዓይነት ከተሰማሩ በካርድ ኮለሙ ኮድ «1» ይሞላል። በአንዳቸውም በአንዱም ሥ ራ እንኳን ካልተሰማሩ በካርድ ኮለሙ ኮድ «2» ይሞላል።</u>

በዚህ ዓምድ እያንዳንዱ ዕድሜው 10 ዓመትና በላይ የሆነ የቤተሰቡ አባል ከጥናቱ ቀን በፊት ባለፉት 7 ቀና ት ውስጥ በቅጥር/በክፍያ ወይም ነግዶ ለማትረፍ ወይም በግብርና ወይም በሌላ የማምረት ተግባር ወይም አገ ልግሎት በመስጠት ተግባር ተሰማርቶ እንደሆነ ይጠየቃል። በዚህ ጥያቄ ለማወቅ የተፈለገው አባሉ ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በምርታማ ተግባር ላይ መሠማራት አለመሠማራታቸውን ነው። ዓምዱ ሰዎች ሊሰማሩ የሚችሉ ባቸውን 8 ዋና ዋና የሥራ ዘርፎችን የያዘ ሲሆን እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል በነዚህ የሥራ ዘርፎች ተሰማርቶ እንደሆነ ለማወቅ ጥያቄዎች ከመጀመሪያው ጀምሮ አንድ በአንድ ይቀርቡለታል። ከተዘረዘሩት የሥራ ዘርፎች በአንዱ እንኳን ከተሳተፈ በምርታማ ተግባር እንደተሰማራ ተቆጥሮ በካርድ ኮለሙ ኮድ 1 ይሞላል። ነገር ግ ን ከተዘረዘሩት የሥራ ዘርፎች ውስጥ በአንዱም እንኳ አልተሰማራሁም ካለ ኮድ 2 ይሞላል። በመጠይቁ ላይ የሠፈረው ጥያቄ እንዳለ ለመልስ ሰጪው መነበብ ይኖርበታል። የሥራ ሁኔታ መረጃን ለመሙላት በዓምድ 28 የተሰጠውን የምርታማ ሥራን ትርጉምና ማብራሪያ ጠንቅቆ መረዳት ያስፈልጋል። ቀጥሎ ለእያንዳንዱ ጥያቄ መብራሪያ ተሰጥቷል።

<u>በመንግሥት ወይም በግል ድርጅት ተቀጥረው ሠርተዋል?</u>

ጥያቄው እንደሚያመለክተው መንግስት በሚያስተዳድራቸው መ/ቤቶች/ድርጅቶች፣ ወይም የግል /መንግስታዊ ያልሆኑ/ አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩ ሰዎችን ያጠቃልላል። የግ ል ድርጅት ተቀጣሪዎች ሲባል በግለሰብ ቤት በቤት ሠራተኝነት የተቀጠሩትን፣ በአነስተኛ የንግድ ወይም የአገ ልግሎት ሰጪ ድርጅት ለምሳሌ ሱቅ ውስጥ አሻሻጭ እንዲሁም በትላልቅ ድርጅቶች (ፋብሪካዎችና ኢንዱስትሪ ዎች) ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩትን ይጨምራል። ለትርፍ በማይሰሩ መንግሥታዊ ባልሆኑ ግብረሰናይ ድርጅቶ ች /NGO/ ውስጥ የሚሰሩትን በሕዝባዊ ማህበራት ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩ፣ በሕዝባዊ ማህበራት በክፍያ የ ሚያገለግሉ ተመራጮች ፣ ከቀበሌ እስከ ማዕከል ባሉት የአስተዳደር እርከኖች ውስጥ በክፊያ የሚሠሩ ተመራ ጮች ... ወዘተ ተቀጥረው እንደሚሠሩ እንቆጥራቸዋለን።

<u>በንግድ ሥራ ተሰማርተው ነበር?</u>

ንግድ ማለት ትርፍ ለማግኘት ዕቃዎችን ገዝቶ በጅምላም ይሁን በችርቻሮ መሸጥ ነው። የገዙትን ዕቃ ወደ ሌላ መልክ ቀይሮም ይሁን ሳይቀይሩ መሸጥ ንግድ ይባላል። ይህም ከትናንሽ ንግድ ማለትም ከቆሎ ሻጭነት እስከ ትላልቅ ንግድ ያለውን ያካትታል። የመነገጃው ቦታውም ጉልት፣ ገበያ ቦታ፣ ወይም በየቦታው እየተዟዟ ሩ ወይም በተወሰነ ቤት ውስጥ በቋሚነት ተቀምጦ ሊሆን ይችላል።

<u>በቅጥርም ሆነ በግል ለክፍያ አገልግሎት በመስጠት ተሰማርተው ነበር?</u>

በክፍያ የሚሠሩ ሥራዎችን ለሌሎች ሰዎች መሥራት /ማገልገል/ አገልግሎት መስጠት ይባላል። በምሳሌነት ከሚጠቀሱት ውስጥ ሊስትሮ፣ ፀጉር ማስተካከል፣ ልብስ መስፋት፣ ድለላ፣ በክፍያ ማስተማር፣ የጥገና አገልግሎት

፣ የፅዳት አገልግሎት፣ ጉዳይ ማስፈፀም፣ የታክሲ ወይም የትራንስፖርት አገልግሎት፣ የሆቴል አገልግሎት መስጠት ናቸው።

<u>በግብርና ስራ ተሰማርተው ነበር?</u>

*የግብርና ሥራ እርሻ፣ ከብት እርባታ፣ የአሳማ እርባታ፣ የዶሮ እርባታን የንብ እርባታን ... ወዘተ ያጠቃልላል። ያመረቱትን ቀዳሚ ምርት /እህል፣ ጣውላ የመሳሰሉት/ ለሽያጭም ሆነ ለራስ ፍጆታ ወደ ሌላ ዓይነት ምርት መቀየር በዚህ ስር ይጠቃለላል። የእርሻ ሥራ የሚባለው ከዝግጅት ጀምሮ ምርቱ ከደረሰ በሁዋላ ሰብስቦ እስከ ማከማቸት ያለው ተግባር ነው። ብቻቸውን ወይም ከቤተሰብ አባላት ጋር ወይም ለሌላ ሰው /ድርጅት/ ተቀጥረው ወይም በምግብ ለሥራ ፕሮግራም በግብርና ስራ ላይ የተሰማሩ ሁሉ ለዚህ ጥያቄ አዎን የሚል መልስ እንዲመልሱ ይጠበቃል።*

<u>ለሽያጭ የሚሆኑ ዕቃዎችን አምርተው ነበር?</u>

*ራሳቸው /ቤተሰቡ/ ያመረቱትን ምርት በመጠቀምም ሆነ በሌላ ሰው የተመረቱ ምርቶችን በመጠቀም ለገበያ እንዲቀርቡ በማድረግ ተግባር የተሰማሩ፣ ከፊሉን ተጠቅመው ቀሪውን በመሸጥ ተግባር የተሠማሩ ... ወዘተ ለሽያጭ የሚሆኑ ዕቃዎች እንዳመረቱ ይቆጠራል ለምሳሌ፣ አሽዋ፣ ደንጋይ፣ ጣውላ ማምረት ለሽያጭ እንጀራ፣ ጠላ፣ አረቄ፣ ወንበር የመሳሰሉ ቁሳቁሶችን መስራት፣ ጫማ መስራት፣ ጥጥ መፍተል፣ እንጨት ለቅሞ መሸጥ። ነገር ግን በሌላ ሰው የተመረተን ምርት ገዝቶ ለራስ ፍጆታ በማሰብ ወደ ሌላ መልክ በመቀየር መስራት እንደ ምርታማ ስራ አይቆጠርም። ሆኖም የተመረተው ለሽያጭ ከቀረበ ምርታማ ተግባር ነው።*

<u>ለቤተሰቡ ቋሚ ንብረት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን ሰርተው ነበር?</u>

*ቋሚ ንብረት ማለት ቢያንስ ለአንድ ዓመት ያህል ግልጋሎት መስጠት የሚችሉ ግንባታዎችን ይመለከታል። ለምሳሌ አጥር፣ ቤት መስራት፣ ለዚሁ መሥሪያ የሚሆኑ ቁሳቁሶችን መሰብሰብ፣ ማዘጋጀትና መሥራት፣ የእርሻ መሣሪያዎች መሥራት፣ እንዲሁም ሌሎች መሣሪያዎችን መሥራትን ያጠቃልላል።*

<u>ያለክፍያ ለቤተሰብዎ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ተሰማርተዋል ነበር?</u>

*በቤተሰባቸው ድርጅት ማለትም የንግድ፣ የአገልግሎት ሰጪ ወይም እርሻ ውስጥ ክፍያ ሳያገኙ የሠሩ ናቸው። የቤት ውስጥ ሥራ እንደምርታማ ሥራ ስለማይቆጠር ለቤተሰባቸው የቤት ውስጥ አገልግሎት የሰጡ በምርታማ ሥራ ከተሳተፉት ተለይተው መታየት አለባቸው። ያለክፍያ ከቤተሰባቸው ጋር በምርታማ ተግባር ሲሳተፉ የነበሩ ነገር ግን በጥናቱ ሳምንት ሳይሠሩ የቀሩ ሥራ እንዳላቸው አይቆጠሩም።*

<u>ከላይ ከተጠቀሱት ውጪ ሌላ ሥራ ሠርተዋል ለምሳሌ በተለማማጅነት?</u>

*በጥናቱ ወቅት ከላይ ከተዘረዘሩት የምርታማ ሥራ ዘርፎች ውጪ ሌላ ስራ እየሠሩ ያሉም በዚህ ዓምድ ኮድ 1 ይሞላላቸዋል፤ ለምሳሌ በቤት ሠራተኝነት፤ ሥራ በመለማመድ ላይ የሚገኙ ... ወዘተ። ሥራ ተለማማጅ ሰዎች በተለማማጅነት በሚሰሩበት ወቅት የተወሰነ ክፍያ ሊኖራቸውም ላይኖራቸውም ይችላል እንዲያውም እየከፈሉ የሚሠሩ ሊያጋጥሙ ይችላሉ። በተለማማጅነት ገብተው ነገር ግን በሥራው ሂደት ላይ ምንም ተሳትፎ /አስተዋፅኦ/ የሌላቸው ምርታማ ሥራ እንደሠሩ አይቆጠርም። እንዲሁም ከላይ ከተዘረዘሩት የሥራ ዘርፎች ውጭ ሌላ ምርታማ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሁሉ በዚህ ዓምድ ኮድ 1 ይሞላላቸዋል።*

**ዓምድ 31**

<u>**የምሣና የጉዞ ሰዓትን ሳይጨምር ባለፉት 7 ቀናት በ___ ቀን በሰሯቸው በሁሉም ስራዎችዎ ለስንት ሰዓት ሰርተዋል?**</u>

*በዚህ ዓምድ እያንዳንዱ በምርታማ ስራ ላይ ተሰማርቶ የነበረ ግለሰብ (በዓምድ 30 ኮድ 1 የተሞላላቸው) በጥናቱ ሳምንት ባሉት 7 ቀናት ውስጥ በየቀኑ ስንት ሰዓት እንደሠራ ይጠየቃል። ይህ ጥያቄ በተቻለ መጠን መረጃው ከሚመለከተው ሰው መሰብሰብ ይኖርበታል። ጥያቄው የሚቀርበው ከቅርቡ ቀን ጀምሮ ተራ በተራ ወደ ኋ-*

*ላ እያንዳንዱን ቀን በመጥቀስ ያለፉትን 7 ቀናት ነው። ካርድ ኮለሞቹም እንዲሁ ከቅርቡ ቀን ጀምሮ ወደኋላ ላሉት 7 ቀናት ነው የሚሞሉት። ይህ ጥያቄ የሚቀርበው የቀኑን ስም እየጠሩ ግለሰቡ ከጠዋት እስከ ምሽት በምን ተግባር ላይ እንደዋሉ በመጠየቅ መሆን ይገባዋል። ለምሳሌ መረጃ ሰብሳቢው መልስ ሰጪው ቤት ደርሶ የሚጠይቀው ረቡዕ ዕለት ከሆነ ከትላንት ማክሰኞ ጀምሮ ወደኋላ ላሉት ሰባት ቀናት እስከ ረቡዕ ድረስ ተራ*

በተራ በቀኖቹ አኳያ በመጠየቅ መረጃውን ይሞላል። የበዓላት፣ የስብሰባንና የገበያ ቀናትን በስም መጥራት በ ዛን ሰሞን የነበሩ ሁኔታዎችን በቶሎ እንዲያስታውሱ ይረዳል። ለአንድ የቤተሰብ አባል የተሞላ መረጃ ለሌላኛ ው በማነፃፀሪያነት ሊጠቅም ስለሚችል መረጃው ሲሞላ እያነጻጸሩ መጠየቅ ለመረጃ ሰጪው ሁኔታዎችን ለማስ ታወስ ይረዳል። እንዲሁም መረጃው በሚሰበሰብበት ቤተሰብ አካባቢ የተከናወኑ ድርጊቶች (ለምሳሌ ለቅሶ፣ ስብ ሰባ፣ ሰርግ፣ ...ወዘተ) መኖራቸው ከታወቀ ይህንን በማነፃፀሪያነት መጠቀም ጥሩ ነው። አንዳንድ ሰዎች በየዕለቱ /በየቀኑ ከአንድ በላይ ሥራ ሊሠሩ እንደሚችሉ በመገንዘብ የሥራ ሰዓት አጠያየቁ በሁሉም ሥራዎች የዋለው ን የሥራ ሰዓት ብዛት መሆን መረጋገጥ ይኖርበታል። በተጨማሪም በፈረቃም ሆነ በሥራ ባሕሪያቸው የተነሣ በ ቀንና በምሽት ወይም በምሽት ብቻ የሚሠሩ ሰዎች ስላሉ ይኸም ተጣርቶ መረጃው ሁለቱን ወቅቶች በማካተት መጠየቅ ይኖርበታል።

## በቀን ውስጥ እንደሥራ ሰዓት የሚያዙት የሚከተሉት ናቸው፤

ሀ.

ዋነኛ ሥራቸውንና ሌላ ሥራ ካላቸውም በተጠቀሰው ቀን በሥራ ቦታው ተገኝተው ሥራ የሠሩበት ሰ ዓት፣

ለ.

ከስራ ቦታቸው በተለየ ሥፍራ ቢሆንም ለምሳሌ ለሥራው የሚሆኑ ዕቃዎችን በማዘጋጀት፣ በመጠገን፣ በማጽዳትና ስለ ሥራው ሪፖርት በማዘጋጀት የሚጠፉ ሰዓቶች፣

ሐ.

ዕቃ ለሽያጭ የሚያመርቱ ሰዎች ጥሬ ዕቃውን ለመግዛት የሚያጠፉት ሰዓትና ገዝተው እቤት ያደረሰ ቡት ሰዓት እንዲሁም ያመረቱትን ምርት ለመሸጥ ገበያ የሄዱ ሰዎች ምርቱን ይዘው ከቤት ከወጡ ጀምሮ ሸጠው እስካበቁ ድረስ ያለው ሰዓት እንደስራ ሰዓት ይያዝላቸዋል። በገበያ ውስጥ ለራስ ፍጆታ የሚሆኑ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችንና ለመግዛት የባከነው ሰዓት እንዳይደመር መጠንቀቅ ይገባል።

መ.

በስራ ቦታ ተገኝተው ለመሥራት ዝግጁ እስከሆኑ ድረስ በተለያየ ምክንያት ወይም ችግር ስራው ባይ ሰራም እዛ ቦታ የተገኙበት ሰዓት እንደሠሩ ይያዛል። እንዲሁም በስራ መካከል ለአጭር ሰዓት የባከኑ ጊዜ ዎች ለምሳሌ የሻይ እረፍት እንደ ስራ ሰዓት ይቆጠራሉ።

## የሚከተሉት ከስራ ሰዓት ውስጥ አይደመሩም፤

1.

ክፍያ ቢያገኙበትም ባያገኙበትም በስራ ገበታ ላይ ያልተገኙባቸው ጊዜያቶች እንደሥራ ሰዓት አይያ ዝም። ሥራ ቢኖራቸውም ሥራ ላይ ሳይገኙ ከቀሩ የሠሩት የሥራ ሰዓት ዜሮ ተብሎ ይመዘገባል።

2. ለምሳ የሚባክን ጊዜ እንደ ስራ ሰዓት አይቆጠርም።

3.

ከመኖሪያ ቤት ሥራ ለመጀመር ወደ ስራ ቦታ የሚደረግ የጉዞ ሰዓት እና ከስራ ቦታ ወደ መኖሪያ በ ት ለመመለስ የሚጠይቅ ጊዜ እንደሥራ ሰዓት አይቆጠርም። ይህም ማለት በአንድ በተወሰነ የሥራ ቦ ታ ለሚሠሩ ሰዎች እንደ ሥራ ሰዓት የሚቆጠረው የስራ ቦታ ከደረሱበት ጀምሮ በቀኑ ውስጥ የሚሠሩት ን ሥራ ጨርሰው ከሥራ ቦታ እስከወጡበት ያለውን ጊዜ ብቻ ነው። የሥራ ፀባያቸው ከቦታ ቦታ መዘ ዋወር የሚያስፈልገው ለምሳሌ ጋዜጣ ሻጭ:-

¨ ሊስትሮ እቃ ግዢ ሠራተኛ፣ ሾፎር ... ወዘተ ሥራ በማፈላለግ የሚያጠፉትን ጊዜ እንደሥራ ሰዓት ይ ያዛል።

4.

በግል ሥራ በሚተዳደሩና ለቤተሰብ ያለክፍያ ለሚሠሩ ሰዎች በተለይ ሥራው በቤታቸው አካባቢ ከ

ሆነ ከምርታማ ሥራቸው በተጨማሪ እንደ ቤት ውስጥ ሥራ ያሉ ምርታማ ያልሆኑ ሥራዎች የሠሩበት ሰዓት ከስራ ሰዓት ጋር እንዳይደመር ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

5.

በተለማማጅነት ያሉ ሰዎች በሚለማመዱት ሙያ ላይ በመስራት ተሳትፎ ሳያደርጉ በማየ ት ብቻ ያሳለፉት ሰዓት እንደሠሩ አይያዝላቸውም። ለምሳሌ አንድ በጋራዥ ውስጥ እየተለማመዱ ያ ሉ ግለሰቦች ከሰዓት በፊት በ"ቲዎሪ" መልክ ከ2-6 ሰዓት ቢማሩና ከሰዓት በሁዋላ ከ7 እስከ 11 ሰዓት ከጋራዥ ሰራተኞች ጋር ሥራ እየሠሩ (እያገዙ) ቢውሉ እንደስራ ሰዓት የሚመዘገብላቸው ከሰዓት በሁዋላ የሠሩበት 4 ሰዓት "04" ተብሎ ነው።

6.

በግለሰብ ቤት በዘበኝነት ተቀጥረው ቀንም ሆነ ማታ የሠሩት ሥራ እንደ ሥራ ሰዓት የሚወሰድላቸው ቢሆንም በእንቅልፍ የሚያጠፉት ሰዓት ግን እንደሥራ ሰዓት አይያዝም።

ባለፉት 7 ቀናት የተከናወኑ ሥራዎችን የሥራ ሰዓት ጥያቄን የማቅረቡም ሆነ ለመረጃ ሰጪው የየዕለቱን ሁኔ ታ ወደ ኋላ ተመልሶ በማስታወስ መመለሱ አስቸጋሪ እንደሆነ ግልጽ ነው። ሆኖም በመረጃ ሰብሳቢውም ሆነ በመረ ጃ ሰጪው በኩል ትዕግሥት ኖሮና ጊዜ ስጥቶ መልሱን ለማግኘትም ሆነ መልሱን ለመስጠት ቀናነቱ ካለ ጥሩ መ ረጃ ሊገኝ እንደሚችል ይታወቃል። ስለሆነም በተለይ መረጃ ሰብሳቢዎች መረጃ ሰጪዎችን አስቀድሞ ስለመረጃው አስፈላጊነት፣ መረጃውን በመስጠት በኩል ሳይቸኩሉ አስታውሰው መስጠት እንደሚገባቸው ማስረዳትና ማረጋጋት ይጠበቅባቸዋል።

በዚህ መሠረት ለእያንዳንዱ ቀን መረጃው ከተሞላ በኋላ በሳምንቱ ውስጥ የሠሩት የሥራ ሰዓት ተደምሮ የሳም ንቱ ድምር በሚለው ሥር መሞላት አለበት። በሳምንት ውስጥ የሠሩት የሥራ ሰዓት ድምር 97 እና ከዚያ በላይ ሰዓት ከሆነ 97 በካርድ ኮለሙ ይሞላል።

## ዓምድ 32 መረጃ ሰብሳቢ :- <u>በዓምድ 31 ባለፉት 7 ቀናት የሰሩት የስራ ሰዓት ድምር</u>

በዚህ ዓምድ መረጃ ሰብሳቢው ለመልስ ሰጪው ጥያቄ ሳያቀርብ በዓምድ 31 የተሞላውን የሳምንቱን የሥራ ሰዓት ድምር በማየት እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ስንት ሰዓት እንደሰራ ያገናዝባል። 4 ሰዓትና በላይ ለሰሩ ኮድ 1 ሞልቶ ወደ ዓምድ 35 ይሻገራል። ከ4 ሰዓት በታች ለሠሩ ግን ኮድ 2 ሞልቶ በተከታዩ ዓምድ ያለውን ጥያቄ ያቀርብላቸዋል።

## ዓምድ 33 <u>ሥራ እያሎት ነበር ባለፉት 7 ቀናት በሥራ ላይ ያልተሰማሩት?</u>

ይህ ጥያቄ የሚመለከታቸው ባለፉት 7 ቀናት ሥራ ላልሠሩ / በዓምድ 30 ላይ ኮድ 2 ለተሞላላቸው / እና ባለፉት 7 ቀናት ከ4 ሰዓት በታች ለሠሩ ( በዓምድ 32 ኮድ 2 ለተሞላላቸው) የቤተሰብ አባላት ነው። እነኚህ ሰዎች ሥራ እያላቸው ከስራቸው ለጊዜው ቀርተው እንደሆነ ለማወቅ "ሥራ እያለዎት ነበር ባለፉት 7 ቀናት በስራ ላይ ያልተሰማሩት?" ተብለው ተጠይቀው አዎን ካሉ ኮድ ፲፣ የለም ካሉ ኮድ 2 ይሞላላቸዋል። ኮድ 2 የተሞላላቸው ወደ ዓምድ 46 ይሻገራሉ። ሥራ አለኝ ለሚሉ ሰዎች ኮድ 1 ከመሞላቱ በፊት ሥራ ቸው ምርታማ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

ከስራቸው ቀሩ የሚባሉ ሰዎች ባለፉት 7 ቀናት በዓመት ፈቃድ፣ በወሊድ ፈቃድ፣ በሕመም፣ በትምህር ት ወይም ስልጠና ላይ ስለሆኑ፣ ለጊዜው ሥራው በተለያየ ምክንያት ስላቆመ (ለምሳሌ ዕድሳት፣ የጥሬ ዕቃ እጦ ት፣ የመብራት አለመኖር የመሳሰሉት) ያልሠሩ ግን ሁኔታው (ችግሩ) ሲቃለል ወይም ጉዳያቸው ሲያበቃ ወደ ስራቸው የሚመለሱ መሆን አለባቸው።

ሥራ አጥ(ፈላጊ) የነበሩ ነገር ግን ከጥናቱ ሳምንት በኋላ የሚጀምሩት ሥራ ያገኙ ሰዎች ከሥራ እንደ ቀሩ አይቆጠርም። ነገር ግን ያገኙትን ሥራ በጥናቱ ሳምንት ውስጥ መጀመር ኖሮባቸው በተለያየ እክል ምክን ያት ሳይጀምሩ የቆዩ ከሥራ እንደቀሩ ይቆጠራል።

<u>ከሥራቸው የቀሩ ሰዎች</u>

1. በቅጥር ለሚሠሩ በቀሩበት ወቅት ሙሉ ወይም ከፊል ክፍያ የሚያገኙ፣ ወይም

2. በቅጥር ለሚሠሩ ከሥራ ያስቀራቸው ምክንያት ሲቃለል ወደ ቀድሞ ሥራቸው የሚመለሱ፣ ወይም

3. በቅጥር ለሚሠሩ ከሥራ ከቀሩ 2 ወር ያልሞላቸው መሆን አለባቸው።

4. በግል ሥራ ለሚተዳደሩ እነሱ ከሥራ ቢቀሩም ድርጅታቸው ያልተዘጋ (ተመልሶ የሚከፈት) መሆን አለበት።

<u>ማስታወሻ :-</u>

ተባራሪ ስራ (የቀን ሠራተኞች) ለሚሠሩ በጥናቱ ሳምንት ስራ ካልሠሩ ከስራቸው እንደቀሩ አይቆጠርም እንዲሁም ያለክፍያ ለቤተሰቡ ሲሰራ የነበረ ነገር ግን በጥናቱ ሳምንት ያልሠራ ግለሰብ «ሥራ እያላቸው ከስራ የቀሩ» ተብሎ አይቆጠርም።

### ዓምድ 34 <u>ባለፉት 7 ቀናት ሥራዎን ያልሰሩበት ምክንያት ምንድነው?</u>

በዚህ ዓምድ ሥራ እያላቸው ባለፈው 7 ቀናት በሥራ ላይ ላልተሰማሩ ( በዓምድ 33 ኮድ 1 ለተሞላ ላቸው) ከስራቸው የቀሩበት ምክንያት ይጠየቃሉ። መልሶቹም በሚከተሉት ኮዶች አማካይነት ይመዘገባሉ።

1 = <u>በሕመም</u> - በመታመማቸው ምክንያት ከሥራ የቀሩ፣

2 = <u>እረፍት/በዓል</u> - የዓመት ወይም የእክል እረፍት ወስደው የቀሩ ወይም በዓል በመሆኑ ከስራቸው የቀሩ፣

3 = <u>ሥልጠና/ትምህርት</u> - በጥናቱ ሳምንት በትምህርት ምክንያት ወይም በስልጠና ላይ በመሆናቸው ከስራቸው የቀሩ፣

4 = <u>የሥራ ወቅት ባለመሆኑ</u> - የተሰማሩበት የሥራ መስክ በጥናቱ ወቅት ገበያ ስለሌለው ወይም የአየሩ ፀባይ ስለማያመች ወይም በሌላ ምክንያት የሥራ ወቅት ስላልሆነ ከስራቸው የቀሩ፣

5 = <u>ለጊዜው ሥራው ስለሌለ/ስለቆመ</u> - ለማምረቻ የሚሆኑ ወይም ለሥራው አስፈላጊ ቁሳቁሶች ለምሳሌ ጥሬ ዕቃ፣ መብራት ስለሌለ ከስራቸው የቀሩ

6 = <u>ሌላ/ይገለጽ/</u> - ከላይ ከተገለጹት በተለየ ምክንያት ከሥራቸው የቀሩበት ምክንያት በዓምዱ ተመዝግቦ ይህ ኮድ ይሞላላቸዋል፡

## ክፍል 4 ባለፉት 7 ቀናት በምርታማ ተግባር ለተሰማሩ -

<u>ማስታወሻ</u>:- የዚህ ክፍል መረጃዎች ከመሞላታቸው አስቀድሞ በመጠይቁ ራስጌ ላይ በተዘጋጀው ሥፍራ የተመ ረጠውን ቤተሰብ አድራሻና የአካባቢ መለያ ከገፅ 1 ክፍል 1 ማወራረስ ያስፈልጋል።

በዚህ ክፍል የሚሰበሰቡ መረጃዎች ከጥናቱ ቀን በፊት በነበሩበት (ባለፉት) 7 ቀናት ውስጥ ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ የሆናቸውና በምርታማ ተግባር የተሳተፉ የቤተሰቡ አባላት የሥራ ስምሪትን የሚመለከቱ ይሆናሉ።

ዓምድ 11 እና 10፡- ዓምድ 11 "ሙሉ ስም" እና ዓምድ 10 "የመስመር ቁጥር" የሚለው ከገፅ 1 ዓምድ 11 እና 10 ሁሉም የቤተሰብ አባላት ቅደም ተከተላቸውን እና የመስመር ቁጥራቸውን እንደጠበቀ የሚዛወሩበ ት ነው።

*ዓምድ 35-45፡- እነኚህ ዓምዶች የሚመለከቱት ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ ሆኗቸው ባለፉት 7 ቀናት ከ4 ሰዓት በ ላይ የሠሩ (በዓምድ 32 ኮድ 1 የተሞላላቸው) ወይም ሥራ እያላቸው ላልሠሩ (በዓምድ 33 ኮድ 1 ለተሞላላቸው) የቤተሰብ አባላት ብቻ ነው። በክፍል 4 የሚቀርቡት ጥያቄዎች 10 ዓመትና በላይ የ ሆናቸው የቤተሰብ አባላት ብቻ ስለሚመለከቱ ዕድሜአቸው ከ10 ዓመት በታች ለሆናቸው የቤተሰብ አባላት ከዓምድ 35-45 ያሉት ዓምዶች በሰረዝ ይታለፋሉ። እንዲሁም ባለፈው ሳምንት በምርታማ ተግባር ላይ ያልተሳተፉና ሥራ እያላቸው ከሥራ ያልቀሩ (በዓምድ 33 ኮድ 2 የተሞላላቸው) ከዓም ድ 35 - 45 ያሉት ጥያቄዎች ስለማይመለከቷቸው ዓምዶቹ "---" ይሞላባቸዋል ማለት ነው።*

ዓምድ 35- <u>የዋነኛ ስራዎ ዓይነት ምንድነው?</u>

በዚህ ዓምድ ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በምርታማ ተግባር ላይ ሲሳተፉ የነበሩ ሰዎች /በዓምድ 32 ኮድ 1 የተሞላላቸው/ እና ባለፉት 7 ቀናት በምርታማ ተግባር ላይ ባይሳተፉም ሥራ የነበራቸው /በዓምድ 33 ኮ ድ 1 የተሞላላቸው/፣ ስለ ዋነኛ ሥራቸው ዓይነት ይጠየቃሉ። ከአንድ በላይ ሥራ ለነበራቸው አባላት የሚጠ የቅላቸው ስለ ዋናው ሥራቸው ማለትም ከሌሎቹ የበለጠ ጊዜ የወሰደውን/የሚወስደውን ይሆናል። የሥራ ዓ ይነትም የሚገለጸው በአብዛኛው ጊዜ ግለሰቡ ምን በማድረግ እንደሚውል በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ በዝርዝር በመመዝገብ ይሆናል። የሥራ ዓይነት በእርሻ ሥራ ላይ ለተሠማሩ ግለሰቦች በሚገለጽበት ጊዜ ገበሬ፣ የእርሻ ሠራተኛ፣ እረኛ፣ ቅጥር እረኛ፣ አዳኝ፣ ዓሣ አጥማጅ ... ወዘተ እየተባለ ይሆናል።

*የሥራ ዓይነት ተብሎ የሚመዘገበው ግለሰቡ በአብዛኛው ሲያከናውን የነበረው የሥራ ዓይነት ነው እ ንጂ የሚሠራበት ድርጅት የሚያመርተውን የምርት ዓይነት መሆን የለበትም። ለምሳሌ ለአንድ በታይፒስትነት ለምታገለግል ሠራተኛ የሥራ ቦታዋ ሆስፒታልም ይሁን ፋብሪካ፥ ትምህርት ቤት፥ ...ወዘተ ሁልግዜም የሚ መዘገብላት «ታይፒስት» የሚለው የሥራ ዓይነት ነው። የሥራው ዓይነት በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ ከተመዘገበ በኋላ ለሥራው ዓይነት ተገቢው ኮድ በዋናው መሥሪያ ቤት ይሰጠዋል። የሥራው ዓይነት በሚመዘገብበት ወ ቅትም ተገቢውን ኮድ ለመስጠት በሚያስችል መልክ መሆን ይኖርበታል። ለዚህም ተግባር ከመልስ ሰጪዎች የ ሚሰበሰቡ መረጃዎች ሁሉ በትክክል የግለሰቡን የሥራ ዓይነት የሚያመለክቱ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ለ ምሳሌ ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራን፥ ለአንደኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራን፥ ለቄስ ት/ቤት መምህራን፥ ለታይፕ ት/ቤት መምህራን የተለያየ ኮድ ስለሚሰጣቸው የሥራ ዓይነት ሲመዘገብ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ። በተመሣሣይ ሁኔታም ለግብርና ሥራ ለተሠማሩ ሁሉ ገበሬ ብሎ መጻፍ ትክክል አይሆንም። ምክንያቱም የ ግብርና ሥራ እውቀት ላላቸው ገበሬዎች (ማለትም የማሣ አዘገጃጀት፥ አስተራረስ፥ መቼ እንደሚታረም፥ የማ ዘራበትን ሰዓትና ለግብርና አስፈላጊ የሆነውን ዕውቀት ከወላጅ ወይም ከልምድ የቀሰሙ) እና ዝቅተኛ የግብ ርና ሠራተኞች (የግብርና ዕውቀታቸው ደረጃ የሚታዘዙትን ሥራ ከመሥራት የማያልፈውን) የተለያዩ ኮዶች ስለሚሰጣቸው ነው። በተጨማሪም የሚሰሩበት መሥሪያ ቤትን ብቻ ጠይቆ መልሱን በዚህ ዓምድ መመዝገብ ት ክክል አይደለም። ምክንያቱም በአንድ መሥሪያ ቤት ውስጥ የተለያዩ የሥራ ዓይነቶች ስለሚገኙ እነዚህን ማጣ ራት ስለሚያስፈልግ ነው። ለምሳሌ በአንድ የማዕድን ማውጫ ድርጅት ውስጥ ዋና ሥራ አስኪያጁ፥ የመምሪያ ኃላፊዎቹ፥ ኬሚስቶቹ፥ ኢንጅነሮቹ፥ አካውንታንቶቹ፥ ቀያሾቹ፥ የአፈር ቴክኒሽያኖቹ፥ ኤክሲኩቲቭ ሴክሬተ ሪ፥ ታይፒስቶቹ፥ ገንዘብ ከፋዮቹ፥ ቴሌፎን ኦፕሬተር፥ ለማዕድን ማቅለጫ የተተከለ ማሽን ኦፕሬተሮቹ፥ የመኪ ና ሾፌሮቹ፥ የማዕድን አውጪ ተራ ወዛደሮች፥ ሁሉም የተለያየ ኮድ የሚሰጣቸው የተለያዩ የሥራ ዓይነቶች ስለሆኑ መረጃው በጥንቃቄ እየተጠየቀ ትክክለኛው የግለሰቡ የሥራ ዓይነት ይመዘገባል። ከዚህ በተጨማሪ ተመ ሣሣይ የሆኑ ሥራዎችም ቢሆኑ ሥራውን ለማካሄድ የሚያስፈልገው የትምህርት ደረጃ ወይም የእውቀት ደረጃ ና ሥራውን ለማካሄድ ሠራተኛው የሚጠቀምበት መሣሪያ ዓይነት የተለያዩ የሥራ ዓይነቶች ያደርጓቸዋል። ለ ምሳሌ የሕክምና ዶክተርና ነርስ የተለያዩ የሥራ ዓይነቶች ናቸው። እንዲሁም የጨርቃ ጨርቅ ማምረቻ ማሽን ኦፕሬተሮችና የማምረቻ ፋብሪካ ተራ ወዛደሮች የተለያዩ የሥራ ዓይነቶች ናቸው። በንግድ መስክ ከሚገኙ የ ሥራ ዓይነቶች ውስጥም፥ ገንዘብ ተቀባዮች፥ የሱቅ አሻሻጮች፥ የኪዮስክ አሻሻጮች፥ እንጀራ ጋጋሪዎች፥ ጠላ*

ጠማቂዎች ቆሎ አዟሪዎች ሁሉም የተለያዩ የሥራ ዓይነቶች ናቸው:: አንዳንድ ግለሰቦች ከአንድ የበለጠ ሥራ ሊኖራቸው ይችላል:: በዚህ ጊዜ በዓምድ 35 መመዝገብ ያለበት የሥራ ዓይነት ግለሰቡ ከሁለቱ ወይም ከሶስቱ ሥራዎች ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ ይበልጡን ጊዜ ያጠፋበት ዋነኛ የሥራ ዓይነት ነው:: ሥራ እያላቸው ባለፉት 7 ቀናት ላልሠሩ (በዓምድ 33 ኮድ 1 የተሞላላቸው) ዋነኛ ሥራ ተብሎ የሚመዘገብላቸው ከሥራ ከመቅረታቸው በፊት ይሠሩት የነበረውን ዋነኛ ሥራ ነው:: በመጠይቁ ላይ የሥራውን ዓይነት በትክክል ለመጻፍ እንዲረዳ ከዚህ በታች የተወሰኑ የሥራ ዓይነቶች እንደምሳሌ ቀርበዋል:: ስለዚህ መልሱ ከነዚህ ውስጥ ወይም ከነዚህ ጋር ተመሣሣይ የሆነ የሥራ ዓይነት ሊሆን ስለሚችል ዝርዝሩን በቅድሚያ ማጥናት ያስፈልጋል:: የመልሱ አጻጻፍም በዝርዝሩ የቀረበው ወይም የሚመሳሰል መሆን አለበት:: የተሰጠው ባዶ ቦታ አነስተኛ ሆኖ ከተገኘ በተቻለ ያህል አብቃቅቶ መጻፍ ያስፈልጋል::

የቢሮ ኃላፊ
የዞን ባለሥልጣን
የወረዳ ባለሥልጣን
የፖለቲካ ድርጅት ባለሥልጣን
የሙያ ማሕበር ባለሥልጣን
የተራድኦ ድርጅት ባለሥልጣን
የቀበሌ ባለሥልጣን
የጎሣ መሪ

ዋና ሥራ አስኪያጅ

የመምሪያ ኃላፊ
የዋና ክፍል ኃላፊ
የአገልግሎት ኃላፊ

ኬሚስት
የኮምፒዩተር ፕሮግራመር
ኢንጂነር

ባዮሎጂስት
የሕክምና ዶክተር
የከብት ሕክምና ረዳት

የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መምህር
የት/ቤት ዳይሬክተር

አካውንታንት
ዳኛ
ጠበቃ
ኢኮኖሚስት

የምሕንድስና ቴክኒሽያኖች
ቀያሽ
የኮምፒዩተር ኦፕሬተር
ረዳት ፕሮግራመር
የቴሌኮሙኒኬሽን ቴክኒሽያን
የሕክምና መሣሪያ ቴክኒሽያን

የአፈር ቴክኒሽያን
የጤና ረዳት
የጥርስ ሕክምና ረዳት
ሳኒቴሪያን
የፊዚዮቴራፒ ረዳት
የፋርማሲ ረዳት
የከብት ሕክምና ረዳት
ነርስ
ዘመናዊ አዋላጅ

የ1ኛ ደረጃ ት/ቤት መምህር
የሕጻናትማሳደጊያ ት/ቤት
መምህር
የቄስ ት/ቤት መምህር
የቁርዓን ት/ቤት መምህር

የመኪና መንዳት መምህር
የታይፕ መምህር

ኤክስኩቲቭ ሴክሬተሪ
የስታቲስቲክስ ቴክኒሽያን
የፍርድ ቤት ጸሐፊ
የወንጀል ምርመራ ሠራተኛ
የዜና አንባቢ
ዘፋኝ
የመድረክ ተዋናኝ
ስፖርተኛ

ታይፒስት
ፅሐፊ
የሂሣብ ፀሐፊ
ማመልከቻ ፀሐፊ

ገንዘብ ተቀባይ
ገንዘብ ከፋይ
ቴሌፎን ኦፕሬተር

የቡና ቤት አሰተናጋጅ
ባሬስታ
የወጥ ቤት ሠራተኛ
ፀጉር አስተካካይ
የውበት ሣሎን ሠራተኛ
ባህላዊ መድሐኒት አዋቂ
የልምድ አዋላጅ
መጽሐፍ ገላጭ
ቄስ
ሼክ
ፖሊስ
የእሳት አደጋ ተከላካይ

የሱቅ አሻሻጭ
የኪዮስክ አሻሻጭ
የጉልት አሻሻጭ

ጥጥ ለንግድ አምራች
ሻይ ለንግድ አምራች
ወይን ለንግድ አምራች
ሸንኮራ ለንግድ አምራች
ሰብል ለንግድ አምራች
ዶሮ ለንግድ አምራች
ከብት ለንግድ አምራች
የደን ሠራተኛ
ከሰል አክሳይ
ዓሣ ለንግድ አስጋሪ

የግብርና ዕውቀት ያላቸው ገበሬ
ሙያው ያላቸው ዓሣ አጥማጅ

ድንጋይ ጠራቢ

ድንጋይ አውጪ
አሸዋ አውጪ
ማዕድን አውጪ
ግንበኛ
አናጺ
ለሳኝ
የባንቧ ሠራተኛ
ቀለም ቀቢ

ብረት በያጅ
ቀጥቃጭ
የመኪና ሜካኒክ
የሬዲዮ አዳሽ
የቴሌፎን መስመር ዘርጊ

አንጥረኛ
ሸክላ ሠሪ
የእንጨት እደጥበብ ሠራተኛ
የቀርክሃ እደጥበብ ሠራተኛ
የቃጫ እደጥበብ ሠራተኛ
ፎቶግራፍ አንሺ

የልኳንዳ ሠራተኛ
የእንጀራ ጋጋሪ
ጠላ ጠማቂ
አረቄ አውጪ
ትምባሆ አዘጋጅ
የእንጨት ቁሳቁስ አምራች
ሸማኔ
ፈቃይ
ልብስ ሰፊ
ፋቂ
ጫማ ሰፊ

ለእንጨት መሠንጠቂያ የተተከለ ማሽን አ
ፕሬተር
ለማዕድን ማቅለጫ የተተከለ ማሽን
አፕሬተር
የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ኦፕሬተር

የላስቲክ ማምረቻ ማሽን ኦፕሬተር
የጎማ ማምረቻ ማሽን ኦፕሬተር
የኬሚካል ማምረቻ ማሽን ኦፕሬተር

የሕትመት ማሽኖች ኦፕሬተሮች
የጨርቃ ጨርቅ ማምረቻ ማሽን ኦፕሬተር
የስኳር ማምረቻ ማሽን ኦፕሬተር
የቢራ ማምረቻ ማሽን ኦፕሬተር
የለስላሳ መጠጥ ማምረቻ ማሽን
አፕሬተር
የቆዳ ማልፊያ ማሽን ኦፕሬተሮች

ጫማ መስሪያ ማሽን ኦፕሬተሮች

የምግብ ማምረቻ ማሽን ኦፕሬተሮች
የአውቶቡስ ሹፌር
የመኪና ሹፌር
የትራክተር ሹፌር

ቆሎ አዟሪ
የልዋጭ ነጋዴ
ጋዜጣ አዟሪ
በየመንገዱ ዕቃ ሻጭ
ሊስትሮ
የቤት ሠራተኛ
ሹሩባ ሠሪ
ልብስ አጣቢ
የቡና ቤት ሣህን አጣቢ
የቡና ቤት አልጋ አንጣፊ
ዘበኛ
ተላላኪ

የድንጋይ ማውጣት ተራ ወዛደር
የአሸዋ ማውጣት ተራ ወዛደር
የማዕድን ቁፋሮ ተራ ወዛደር
የኮንስትራክሽን ሥራ ተራ ወዛደር

የጥገና ሥራ ተራ ወዛደር
የማምረቻ ፋብሪካ ተራ ወዛደር
የትራንስፖርት ተራ ወዛደሮች

እረኛ
ዝቅተኛ የእርሻ ሥራ ሠራተኛ
ዝቅተኛ የዓሣ ማስገር ሠራተኛ

የጦር ኃይል አባል

ዓምድ 36 -

<u>በዋነኛነት የሚሠሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነ ት ምንድን ነው</u> ?

ይህን ዓምድ ለመሙላት ግለሰቡ የት ወይም በየትኛው ድርጅት እንደሚሠሩ በመጠየቅና ከዚያም ደርጅቱ ምን እንደሚያመርት፥ እንደሚነግድ /የጅምላ ወይም የችርቻሮ ንግድ/ ወይም ምን ዓይነት አገልግ ሎት እንደሚሰጥ መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ ድርጅት ሲባል  የተለየ ክፍል ወይም ቦታ ሳይኖራቸው በመኖሪያ ቤት ውስጥ፥ በበረንዳ፥ በትናንሽ ገበያዎች /ጉልቶች/፥ በመንገድ ላይ፥ ...ወዘተ ከሚከናወኑ ጥቃቅን ሥራ ዎች አንስቶ የተለየ አድራሻና አደረጃጀት ያላቸውን ፋብሪካዎችና እንዱስትሪዎችን ያጠቃልላል፡፡ ለምሳሌ በ ሚኖሩበት ቤት ውስጥ የሽመና፥ የልብስ ስፌት፥ ጠላ ወይም አረቄ ንግድ፥ ... ወዘተ ምርታማ ሥራዎችን የሚያከናውኑ ምንም እንኳ የሚያከናውኑት ተግባር ሥርዓት ባለው ሁኔታ ተደራጅቶ ባይገኝም በዚህ ዓም ድ እንደ ድርጅት ተቆጥሮ ምርቱ፥ ንግዱ ወይም አገልግሎቱ መገለጽ ይኖርበታል፡፡ አንዳንድ አነስተኛ ድር ጅቶችን ወይም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን በአምራች፥ በአገልግሎት ወይም በንግድ ዘርፍ ለይቶ ለመመደብ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡ ከአንድ በላይ የሆነ የምርት ዓይነት ያላቸው ወይም አገልግሎት የሚሰጡ ድር ጅቶች ሲያጋጥሙ የድርጅቱ ምርት ወይም የአገልግሎት አይነት ተብሎ የሚጠቀሰው ድርጅቱ በአብዛኛው የሚሰጠው የምርት ዓይነት ወይም አገልግሎት አይነት ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ የሲጋራ ፋብሪካ በተጨማሪነት ክብሪት የሚያመርት ቢሆን ድርጅቱ እንደ ሲጋራ አምራች ይመዘገባል፡፡ በተጨማሪም የምርት ዓይነቶች ወይ ም የአገልግሎት ዓይነቶች ተመሣሣይ እስከሆኑ ድረስ የሚመረቱት በግል ድርጅቶችም ሆኑ በመንግሥት ድ ርጅቶች በተመሣሣይ ክፍል ይመደባሉ፡፡ ለምሳሌ ከብት እርባታ በግለሰብም ይካሄድ በትልቅ የመንግሥት እ ርሻ ሁለቱም ተመሳሳይ ክፍል ይመደባሉ፡፡ ወይንም አንድን ምርት የሚያመርተው ድርጅት የመንግስት ፋብ ሪካ ይሁን ወይም የግለሰብ ድርጅት ተመሣሣይ መልስ ይመዘገብላቸዋል፡፡ በተጨማሪም አመራረቱ በዘመናዊ መልክ (ዘመናዊ መሣሪያዎችን በመጠቀም) ይሁን በባሕላዊ ዘዴ (በእጅ በመሥራት) የምርቱ ዓይነት ወይም አገልግሎት ላይ ልዩነት አይፈጥሩም፡፡ ለምሳሌ በፋብሪካ ጫማ ለሚያመርት ወዛደር እና በእጁ ጫማ ለሚ ሰፋ ለሁለቱም «ጫማ ማምረት» ይመዘገብላቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ድርጅቱ ለሚያመርተው ዋና ምርት ወይም አገልግሎት በአጋዥነት የሚያስፈልጉ ሌሎች ግልጋሎቶች ሁሉ ለየብቻቸው የሚመዘገቡ ሳይሆኑ የሚ መዘገበው ዋናው ምርት ብቻ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ የጫማ ምርት በሚያስገኝ ፋብሪካ ውስጥ ጫማ የማምረት ሂደቱን የሚያግዙ የሂሣብ ሥራ፥ የአስተዳደር ሥራ፥ የጽዳት ሥራ፥ የጥበቃ ሥራ፥ ወዘተ. የሚከናወኑ ቢ ሆንም ለሁሉም የሚመዘገብላቸው «ጫማ ማምረት» የሚል መልስ ይሆናል፡፡

መረጃ በሚመዘገብበት ወቅት ችግር እንዳይፈጥሩ አንዳንድ የምርትና አገልግሎት አይነቶች ሰፋ ያ ለ ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው በመሆኑ ከዚህ በታች ቀርበዋል፡-

የእርሻ ምርት ማምረት፡-

ሰብል፥ አትክልት፥ ጫት፥ ቡና፥ ...ወዘተ. (የሚያመርቱ ለማምረቻ መ ሣሪያነት የማረሻ ከብቶችን አጣምረው ሊያረቡ ይችላሉ)

የከብት እርባታ፡-

በሬ፥ ላም፥ ግመል፥ በግ፥ ፍየል፥ ዶሮ ... ወዘተ. የሚያረቡ (የጓሮ ማ ሣ ሊኖራቸው ይችላል)

እርሻና ከብት እርባታ፡- የእርሻና የከብት እርባታ አጣምረው የሚያመርቱ

የግብርና አገልግሎት፡-

የከብት ማዳቀልና የእርሻ ዘዴ ማስፋፊያ አገልግሎት፥ የትራክተር አገል ግሎትና የመሳሰሉት

የጉልት ንግድ፡-

ማንኛውንም ዓይነት ዕቃ ወይም ምግብ በሱቅ ሳይሆን በጉልት ወይም በ

ገበያ የሚሸጡ (በሱቅ ውስጥና ከሱቅ ውጭ የሚካሄዱ የንግድ ዓይነቶች የተለያዩ ኮዶች ስለሚሰጧቸው በግልጽ አጣርቶ መጻፍ ተገቢ ይሆናል።)

ሆቴል፡- የመኝታ አገልግሎት ያላቸው ድርጅቶች (ምግብና መጠጥም ሊኖራቸው ይችላል)።

ቡና ቤት፡- የመኝታ አገልግሎት የሌላቸው

ጠላ ቤት፡- ጠላ የሚሸጥባቸው ቤቶች (ጠላው እዚያው ቤት የተጠመቀ ወይም የተ ገዛ ሊሆን ይችላል)

ጠጅ ቤት፡- ጠጅ የሚሸጥባቸው ቤቶች (ጠጁ እዚያው ቤት የተጣለ ወይም የተገዛ ሊሆን ይችላል)

ጠጅ ማምረት፡- ጠጅ ጥለው ለሌላ ቸርቻሪ በጅምላ የሚሸጡ

የትምህርት አስተዳደር፡- በሚኒስቴር መ/ቤት ወይም በክልል፥ ዞን፥ ... ወዘተ ጽ/ቤት የሚካሄዱ የአስተዳደር ተግባሮች

የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት፡- የትምህርት ቤቱ መምህራን፥ አስተዳደር ክፍልና ሌሎችን ይጨምራል።

የግብርና አስተዳደር፡- የሚኒስቴር መ/ቤቱና የክልል፥ የዞን፥ ... የአስተዳደር አገልግሎት የሚ ሰጡ ጽ/ቤቶች። በወረዳ ደረጃና ሌሎች የግብርና አገልግሎት የሚሰጡ ጽ/ቤቶች ግን በግብርና አገልግሎት ይመደባሉ።

በዓምድ 36 የሚመዘገቡት የድርጅቱ ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነቶች ለምሳሌነ ት እንዲያገለግሉ የተወሰኑት ከዚህ በታች ቀርበዋል። በመረጃ ምዝገባው ወቅትም የሚቀርቡት ከዚህ በታች የቀረቡት ወይም በተመሳሳይ ሁኔታ የተጻፉና በዋናው መሥሪያ ቤት የድርጅት ምርት ወይም አገልግሎት ኮድ ሊያሰጡ በሚችል ሁኔታ የቀረቡ መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል።

እርሻ ምርት ማምረት
የከብት እርባታ
እርሻና ከብት እርባታ
የግብርና አገልግሎት
አደን
ያደን ምርት ማምረት
ዓሣ ማስገር

ድንጋይ ማውጣት
አሸዋ ማውጣት
ወርቅ ማምረት

የምግብ ዘይት ማምረት
የታሸገ ሥጋ ማምረት
የታሸገ ወተት ማምረት
የእህል ዱቄት ማምረት
ዳቦ መጋገር
እንጀራ መጋገር
ስኳር ማምረት
አልኮል መጠጥ ማምረት
አረቄ ማምረት
ቢራ ማምረት
ጠጅ ማምረት
ለስላሳ መጠጥ ማምረት
ሲጋራ ማምረት

ድርና ማግ ማምረት

ጨርቃ ጨርቅ ማምረት
የሽመና አገልግሎት
ገመድ ማምረት
ሥጋጃ ማምረት

የተሰፉ ልብሶች ማምረት
የልብስ ስፌት አገልግሎት
የቆዳ ምርት ማምረት
ኮርቻ ማምረት
ጫማ ማምረት
ጣውላ ማምረት
ሰሌን ማምረት
ዘንቢል ማምረት
ወረቀት ማምረት
የሕትመት አገልግሎት
ቀለም ማምረት
ሣሙና ማምረት
ጎማ ማምረት
ሲሚንቶ ማምረት
ብረት አቅልጦ ማምረት
የብረት በርና መስኮት ማምረት
ማረሻ ቀጥቅጦ ማምረት
ቢላዋ ቀጥቅጦ ማምረት
የኤሌክትሪክ ሽቦ ማምረት
ጋሪ ማምረት
የቤት ዕቃዎች ማምረት
ጌጣጌጥ ማምረት

ኤሌክትሪክ ሟረትና ማሰራጨት
የመጠጥ ውሃ ማምረት

የሕንፃ ግንባታ
የግድግዳ ቀለም መቀባት
የቤት መታወት ማስገባት

የመኪና ጥገና
ቤንዚን ማከፋፈል
የእህል ጅምላ ንግድ
የጨርቃ ጨርቅ የጅምላ ንግድ
የጫማ የጅምላ ንግድ

የአትክልት ግሮሰሪዎች ንግድ
የምግብ ግሮሰሪዎች ንግድ
የጨርቃ ጨርቅ ሱቅ ንግድ
የተለያዩ ቁሳቁሶች ኪዮስክ ንግድ

የሥጋ ልኳንዳ ቤት
የአሣ መሸጫ ሱቅ
መድሐኒት ቤት
የብረታ ብረት መሸጫ ሱቅ
መጽሐፍ መሸጫ ሱቅ
የጉልት ንግድ
የመንገድ ዳር ሸንኩርት ንግድ

ሆቴል

ቡና ቤት
ምግብ ቤት
ሻይ ቤት
ጠላ ቤት
ጠጅ ቤት
አረቄ ቤት

የባቡር ትራንስፖርት
የጋማ ከብት ማከራየት አገልግሎት
የከተማ አውቶቡስ
የከተማ ታክሲ
ዕቃ በጋማ ከብት ማጓጓዣ
ዕቃ ተሸክሞ መጓጓዝ
ዕቃና ሰው በባሕር ላይ ማጓጓዝ
የአየር ትራንስፖርት
የፖስታ አገልግሎት
ቴሌኮሙኒኬሽን

የባንክ አገልግሎት

የኢንሹራንስ አገልግሎት

የቤት ዕቃዎች ኪራይ
የብስክሌት ኪራይ
የቪዲዮ ካሴት ኪራይ
የጥብቅና አገልግሎት
የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት
የሕንፃ ሥራ ምክር አገልግሎት
የፎቶግራፍ አገልግሎት

የአገር አስተዳደር
የመንግሥት አስተዳደር
የውጭ ጉዳይ አገልግሎት
የአገር መከላከያ
የፖሊስ አገልግሎት

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት
የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት
የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት

መደበኛ ሆስፒታሎች
መደበኛ ክሊኒኮች
የግል ክሊኒኮች
የከብት ሕክምና አገልግሎት
የኃይማኖት ድርጅቶች አገልግት
የሬዲዮ ጣቢያዎች
የኪነት አገልግሎት
የሙዚቃ አገልግሎት
የቤተመጻሕፍት አገልግሎት
የልብስ እጥበት አገልግሎት
የፀጉር ስራ አገልግሎት
የሊስትሮ አገልግሎት

የግለሰብ ቤት ዘበኞች
የግለሰብ ቤት የቤት ሠራተኞች

የዓለም አቀፍ ድርጅቶች

## ዓምድ 37 የዋነኛ ሥራዎ የቅጥር አይነት ምንድን ነው?

በዚህ ዓምድ ያለው ጥያቄ የሚመለከተው ተቀጣሪዎችን ብቻ ነው፡፡ ቀጣሪ፣ በግል ሥራ የሚተዳደሩ፣ ያለክፍያ ለቤተሰብ የሚሠሩ፣ ተለማማጆች፣ የአምራቾች ኅ/ሥራ ማህበር አባል የሆኑ ግለሰቦች ካጋጠሙ ሌላ የሚለው ኮድ 4 ይሞላላቸዋል፡፡ አማራጮቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1 =

ቋሚ፦ በሥራው መስክ/ድርጅት ሥራ ተካፋይ የሆነና ላልተወሰነ ጊዜ በቋሚነት በደመወዝ (በገንዘብ/በዓይነት ወይም በሁለቱም ሊሆን ይችላል) ተቀጥሮ የሚሠራ፣

2 =

ኮንትራት፦ በሥራው መስክ/ድርጅት ባለቤትና በሠራተኛው መካከል በሚደረግ የጽሁፍ ስምምነት ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ሠራተኛ ነው፡፡ ሆኖም ሠራተኛው የውል ስምምነቱ እየታደሰለት ከአንድ ጊዜ (ለምሳሌ ዓመት) በላይ በሥራው መስክ/ድርጅቱ ውስጥ ሊሠራ የሚችል ሲሆን በስምምነቱም መሠረት የቅጥር ሁኔታው ሊቋረጥ ይችላል፡፡

3 =

ጊዜያዊ፦ በሥራው መስክ/ድርጅት ባለቤትና በሠራተኛው የቃል ስምምነት ላልተወሰነ ቀን ወይም ወር የተቀጠሩ፣ ክፍያውም በቀን፣ በሳምንት ወይም በወራት ሂሳብ ሊሆን ይችላል፡፡

4 = ሌላ /ይገለጽ/፦ ከላይ ከተዘረዘሩት ውጭ በሆነ በሌላ የቅጥር ዓይነት፡፡

## ዓምድ 38- የዋነኛ ሥራዎ የቅጥር ሁኔታ ምንድን ነው?

የሥራ ዓይነትና የድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ለተሞላላቸው የቤተሰብ አባላት ሁሉ የቅጥር ሁኔታ ተጠይቆ ከዚህ ቀጥሎ በተዘረዘሩት ኮዶች መሠረት በዓምድ 38 ሥር በሚገኘው ክፍት ቦታ ሁኔታው ይመዘገባል፡፡ በካርድ ኮለሙም ትክክለኛው ኮድ ይሞላል፡፡

መ/ቤት ወይም ድርጅት የሚያመለክተው የቅጥር ሠራተኞችን ሲሆን የሥራ መስክ ደግሞ በግል ለሚተዳደሩ፣ የኅ/ሥራ ማህበር አባላትንና ቀጣሪዎችን ነው፡፡ ሳይከፈላቸው ለቤተሰብ የሚሠሩ ባለፈው ሳምንት ሲሰሩት የነበረውን የሥራ መስክ ይመለከታል፡፡

01 = ተቀጣሪ-ለመንግሥት /የመንግሥት ተቀጣሪዎች/_

በቋሚነት፥ በኮንትራት፥ በቀን ወይም በሳምንት ክፍያ እያገኙ ለመንግሥት መ/ቤቶች ለምሳሌ ሆስ ፒታሎች፥ ት/ቤቶች፥ የመከላከያ ተቋማት፥ ...ወዘተ የሚሠሩ፤

02 = <u>ተቀጣሪ - ለመንግሥት ልማት ድርጅት</u>

ሙሉ በሙሉ ወይም በአብዛኛው በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የሚገኙ ድርጅቶች (ለምሳሌ፥ የመንግ ሥት እርሻዎች፥ የመንግሥት ፋብሪካዎች... ወዘተ) ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩ::

03 = <u>ተቀጣሪ መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች /NGO/</u>

በቋሚነት፣ በኮንትራት በቀን ወይም በሳምንት ክፍያ እያገኙ መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች /NGO / በUN

እና በሌሎች ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና በመሳሰሉት ውስጥ የሚሰሩትን ይጨምራል) ተቀጥረው የሚ ሠሩ በዚህ ኮድ ይጠቃለላሉ::

04 = <u>ተቀጣሪ - ለግል ድርጅት/ ለግለሰብ /የግል ተቀጣሪዎች/</u>

በቋሚነት፥ በኮንትራት፥ በቀን ወይም በሣምንት ክፍያ እያገኙ ለግል ድርጅት፥ ለግለሰብ ወይም ለ ማሕበራት ተቀጥረው የሚሠሩ:: ከመንግሥት ድርጅቶች ውጭ በማንኛውም ድርጅት ተቀጥረው የ ሚሠሩ በዚህ ኮድ ይጠቃለላሉ:: ክፍያው በገንዘብ ወይም በዓይነት ሊሆን ይችላል:: መንግሥት ከ ግለሰብ/ከግል ድርጅት ጋር በሽርክና የሚሠራበት ድርጅት ውስጥ የሚሠራ ሠራተኛ አብዛኛውን ድርሻ የያዘው ግለሰቡ/የግል ድርጅቱ ከሆነ ይህ ኮድ ይሞላለታል::

05 = <u>ቀጣሪ</u>

በግል የማምረቻ ወይም አገልግሎት መስጫ ድርጅታቸው ውስጥ ቢያንስ አንድ ሰው ቀጥረው የሚ ያሠሩ:: ቀጥረው የሚያሠሩ ሁሉ በሥራው ላይ አብረው ቢሠማሩም እንደ ቀጣሪ ይቆጠራሉ::

06 = <u>በግል ሥራ የሚተዳደሩ</u>

በግል ሥራ ወይም ድርጅታቸው ውስጥ የሚሠሩ ነገር ግን ምንም ተቀጣሪ የሌላቸው ናቸው:: የቤ ተሰብ አባላትን አለክፍያ በማስተባበር ሥራቸውን የሚያካሂዱ ኃላፊዎች በዚህ ኮድ ይካተታሉ::

07 = <u>ሳይከፈላቸው ለቤተሰብ የሚሠሩ</u>

አንድ ግለሰብ የሚኖርበት ቤተሰብ ለሚያካሄደው እርሻ ወይም ሌላ ዓይነት ድርጅት ወይም ምርት የማምረት ተግባር ያለምንም ክፍያ የሚሠራ ከሆነ በዚህ ክፍል ይመደባል::

08 = <u>ተለማማጅ</u>

እነዚህ ግለሰቦች በአንድ መ/ቤት ወይም ድርጅት በተወሰነ የትምህርት ዘርፍ ሰልጥነውም ሆነ ሳይሰለጥኑ በተወሰነ ክፍያ ለምሳሌ ምግብ፣ መጠለያ ወይም ልዩ የኪስ ገንዘብ እየተሰጣቸው ወይም ከነጭራሹ ምንም ሳይከፈላቸው ሥራ በመለማመድ ላይ ያሉ ናቸው:: በቀጥታ ሥራ ላይ ምንም ተሳትፎ የሌላቸው በዚህ ኮድ አይካተቱም::

09 = <u>የአምራቾች የሕብረት ሥራ ማህበር አባላት</u>

በአምራቾች የሕብረት ሥራ ማህበር አባልነት በመሥራት ከማሕበሩ በሚያገኙት ድርሻ የሚተዳደሩ በዚህ ኮድ ይመዘገባሉ:: ነገር ግን በማህበሩ አባልነት ሳይሆን በማህበሩ በተቀጣሪነት የሚሠሩ ሠራ ተኞች በኮድ 04 ይመዘገባሉ::

10 =

<u>ሌሎች</u> ከላይ ከተዘረዘሩት የቅጥር ሁኔታዎች በአንዱም ሊካተት ካልቻለ በዚህ ኮድ ይጠቃ ለላል:: ለምሳሌ ለበጎ አድራጎት ድርጅት፥ ለሕዝባውያን ድርጅት፥ ለሃይማኖት ድርጅት የሚሠሩ ና ምንም ክፍያ የማይሰጣቸው፥

**ዓምድ 39-41 <u>በዓምድ 38 ኮድ 04፣ 05፣ 06፣ 07፣ 08፣ እና 10 ለተሞላላቸው ብቻ</u>**

በገጠር ቆጠራ ቦታዎች በግል የግብርና ስራ ለተሰማሩ በእነኚህ ዓምዶች ያሉት ጥያቄዎች ለመልስ ሰጪው ሳይቀርቡ በካርድ ኮለሞቹ ኮድ 2 ይሞላል።

## ዓምድ 39 ድርጅቱ/የሥራ መስኩ/ የሂሣብ መዝገብ ይይዛል?

አንድ ድርጅት ወይም የሥራ መስክ የሂሣብ መዝገብ ይይዛል የሚባለው በገንዘብ መልክ መግለጽ የሚቻሉትን የድርጅቱን ወይም የሥራ መስኩን የሥራ እንቅስቃሴዎች ለምሳሌ በየአርዕስታቸው ዘርዝሮና የሂሣብ አያያዙን ሕግ ተከትሎ ሲመዘገብ፣ ከላይ በተመዘገበው መሠረት በዓመት ወይም በወር መጨረሻ ቢያንስ የትርፍና ኪሣራ መግለጫ (Income Statement) እና የሂሣብ ቋት (Balance Sheet) ሲያዘጋጅ ነው። በግል ድርጅት ተቀጣሪ፣ ቀጣሪ፣ በግል ሥራ ለሚተዳደሩ፣ ሳይከፈላቸው ለቤተሰብ የሚሠሩ ሠራተኞች የሆኑ ሠራተኞች በዚህ ዓምድ የሚሠሩበት ድርጅት የሂሣብ መዝገብ ይይዝ እንደሆነ ይጠየቃል። አማራጭ መልሶቹም 1= አዎን 2 = የለም 3 = አላውቅም ናቸው።

"የሂሣብ ቋት" እና የ"ትርፍና ኪሳራ መግለጫ" ትርጉም ቀጥሎ ቀርቧል።

<u>የሂሣብ ቋት</u>:- ማለት ድርጅቱ የሚገኝበት ሁኔታ (Financial Position) የሚያሣይ፣ በዓመቱ መጀመሪያ ላይ መነሻ ያለው፣ በዓመቱ ውስጥ የተካሄደው እንቅስቃሴ የሚያሣየውን ለውጥ በዓመቱ መጨረሻ ላይ የሚመዘገብበትና ለሚቀጥለው ዓመት አዲስ መነሻ (Balance) የሚይዝ ማለት ነው።

<u>ትርፍና ኪሣራ መግለጫ</u>:-
የድርጅቱን የወጪና የገቢ መጠን በየወጪና ገቢው አርዕስት ዘርዝሮ የሚይዝ፣ በድርጅቱ እንቅስቃሴ ትርፍ ወይም ኪሣራ እንደተገኘ የሚያሣይ ነው።

## ዓምድ 40 ድርጅቱ/የሥራ መስኩ ስንት የሥራው ተካፋይ ሠራተኞች አሉት?

በዚህ ዓምድ ዓመታዊ የሒሣብ መዝገብ በሌላቸው ድርጅቶች ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች (በዓምድ 39 ኮድ 2 ወይም ኮድ 3 የተሞላላቸው) የሥራው ተካፋይ የሆኑ ሠራተኞች ብዛት ተጠይቆ መልሱ በዓምዱ ክፍት ቦታ ይመዘገባል። የኮድ አመዘጋገቡም እንደሚከተለው ነው:-

1 = 10 እና በላይ ሠራተኞች
2 = ከ10 በታች

## ዓምድ 41 ድርጅቱ/የሥራ መስኩ የሥራ/የንግድ ፈቃድ አለው?

ከ10 ሠራተኞች በታች የሥራው ተካፋይ ሠራተኞች ያለው ድርጅት/የሥራ መስክ (በዓምድ 40 ኮድ 2 የተሞላለት) ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች የሚሠሩበት ድርጅት የሥራ ወይም የንግድ ፍቃድ እንዳለው ተጠይቆ፣ መልሱ አዎን ከሆነ ኮድ 1 መልሱ የለውም ከሆነ ኮድ 2 በዚህ ዓምድ ይሞላል።

## ዓምድ 42 ይህ ድርጅት ወይም መሥሪያ ቤት የመጀመሪያዎ ነው?

በዚህ ዓምድ አሁን እየሠሩበት ያሉት መ/ቤት ወይም የሥራ መስክ ወይም ድርጅት የመጀመሪያቸው እንደሆነ ተጠይቆ የሚሰጡት መልስ በተገቢው ካርድ ኮለም ይሞላል። አሁን የሚሠሩበት ድርጅት ወይም መ/ቤት ወይም የሥራ መስክ የመጀመሪያቸው ከሆነ ኮድ 1 ተሞልቶ ወደ ኮድ 4 ይታለፋል። አንድ ሰው አንድ መ/ቤት ወይም ድርጅት ወይም የሥራ መስክ እንደሠራ የሚቆጠረው ቢያንስ 1 ቀን ያህል ሣያቋርጥ በዚያ መ/ቤት ወይም ድርጅት ወይም የሥራ መስክ ከሠራ ብቻ ነው።

## ዓምድ 43 ካለፈው ድርጅት/ መሥሪያ ቤት ወይም የሥራ መስክ ለምን ቀየሩ?

በዚህ ዓምድ አሁን የሚሰሩበት መ/ቤት ወይም ድርጅት ወይም የሥራ መስክ የመጀመሪያቸው ላልሆነ /በዓ ምድ 42 ኮድ 2 የተሞላላቸው/ በፊት ይሰሩበት ከነበረው መ/ቤት ወይም ድርጅት ወይም የሥራ መስክ ለ መቀየር ያበቃቸውን ምክንያት ተጠይቀው የሚሰጡት መልስ በዓምዱ መዝግቦ በሚከተሉት ኮዶች አማካይ ነት በተገቢው ካርድ ኮለም ይመዘገባል፡፡

1 = ለተሻለ ክፍያ

2 = ለተሻለ የሥራ እርካታ

3 = የተሻለ አካባቢ /የቦታ ቅያሪ/

4 = ካለፈው ሥራዬ ስለወጣሁ

5 = ከአሰሪ/ቀጣሪ ጋር ባለመስማማት

6 = ድርጅቱ ስለተዘጋ/ሥራ ስላቆመ

7 = ሌላ/ ይገለጽ

ዓምድ 44

ባለፉት 7 ቀናት ይሠሩ ከነበረው ተጨማሪ ሰዓት ለመሥራት አቅምም ፍላጎትም ነበረዎት? (ከ4 ሰዓት በላይ ለሰሩ-በዓምድ 32 ኮድ 1 ለተሞላላቸው፣ ሥራ እያላቸው ላል ሰሩ-በዓምድ 33 ኮድ 1 ለተሞላላቸው

በዚህ ዓምድ ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በምርታማ ተግባር ላይ ከአራት ሰዓት በላይ ተሠማርተው የ ነበሩ የቤተሰብ አባላት /በዓምድ 32 ኮድ 1/እና ሥራ እያላቸው በምርታማ ተግባር ያልተሠማሩ /ዓምድ 33 ኮድ 1 ለተሞላላቸው/ ተጨማሪ ሰዓት ለመሥራት አቅምም ፍላጎትም እንደነበራቸው ይጠየቃሉ ፡፡ ተጨ ማሪ ሰዓት ለመሥራት አቅምም ፍላጎትም አላቸው የሚባሉት አሁን በመሥራት ላይ ካሉት ዋና ሥራና ሌ ሎችም ሥራዎች በተጨማሪ፣ ሥራ ለመሥራት ጊዜ፣ ፍላጎትና አቅምም አብሮ ሲኖራቸው ነው፡፡ ተጨማሪ ሥራ ለመሥራት ፍላጎት እያላቸው ሥራውን ለመሥራት ግን አቅሙ የሌላቸው /በባሕል ወይም በጤና ም ክንያት፣ ባለመመቸት፣ በትምህርት ላይ ስላሉ፣ ዕድሜያቸው ብዙ ለመሥራት ስለማያስችላቸው… ወዘተ/ ወ ይም ተጨማሪ ሰዓት ለመሥራት አቅሙ እያላቸው ግን ፍላጎት የሌላቸው የቤተሰብ አባላት ተጨማሪ ሥራ ለመሥራት አቅምም ፍላጎትም እንደሌላቸው ይወሰዳል፡፡ ለጥያቄው የሚሰጡ መልሶች በሚከተሉት ኮዶች አ ማካይነት ይመዘገባሉ፡፡ ተጨማሪ ሰዓት ለመሥራት አቅምም ፍላጎትም የነበራቸውና በዚህ ዓምድ ኮድ 1 ይ ሞላላቸዋል፡፡ ተጨማሪ ሰዓት ለመሥራት አቅምም ፍላጎትም ያልነበራቸው ኮድ 2 ይሞላላቸዋል፡፡

ዓምድ 45 ተጨማሪውን ሰዓት በምን ዓይነት ሥራ መስማራት ይፈልጉ ነበር?

ተጨማሪ ሰዓት ለመሥራት አቅምም ፍላጎትም አለን ላሉ /በዓምድ 44 ኮድ 1 ለተሞላላቸው/ ሰዎ ች ተጨማሪውን ሰዓት በያዙት ስራ ወይም ከያዙት ስራ በተጨማሪ ሌላ ስራ ላይ መሆንና አለመሆኑን ለማረ ጋገጥ በዚህ ዓምድ ላይ ይጠየቃሉ፡፡ አማራጮቹም ከዚህ በታች ተገልፀዋል፡፡

1 = በያዙት ሥራ፡- በጥናቱ ሳምንት እየሠሩ በነበረው ስራ ተጨማሪ ሰዓት

2 = ከያዙት ሥራ በተጨማሪ ሌላ ሥራ፡- እየሠሩ ከነበረው ሥራ በተጨማሪ ለተለየ ቀጣሪ ወይም በተለየ የሥራ መስክ መስራት

3 = ሙሉ ሰዓት በሚያሰራ ሌላ ሥራ፡- የሥራው ዓይነት አሁን ከሚሰሩት ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም ባይሆንም አሁን ከሚሰሩት ረዘም ያለ የሥራ ሰዓት በሚያሠራ ሌላ ሥራ ለመቀየር የሚያስቡ

# ክፍል 5 ሥራ አጥነትና የሥራ አጦች ባህሪይ፤

ማስታወሻ፡- የዚህ ክፍል መረጃዎች ከመሞላታቸው አስቀድሞ በመጠይቁ ራስጌ ላይ በተዘጋጀው ሥፍራ የተ መረጠውን ቤተሰብ አድራሻና የአካባቢ መለያ ከገፅ 1 ክፍል 1 ማወራረስ ያስፈልጋል፡፡

**ዓምድ 11 እና 10፡-** ዓምድ 11 "ሙሉ ስም" እና ዓምድ 10 "የመስመር ቁጥር" የሚለው ከገፅ 1 ዓምድ 11 እና 10 ሁሉም የቤተሰብ አባላት ቅደም ተከተላቸውን እና የመስመር ቁጥራቸውን እንደጠበቀ የሚዛ ወሩበት ነው፡፡ በዚህ ክፍል የሚቀርቡት ጥያቄዎች 10 ዓመትና በላይ የሆናቸውን የቤተሰብ አባላ ት ብቻ ስለሚመለከቱ ዕድሜአቸው ከ10 ዓመት በታች ለሆናቸው የቤተሰብ አባላት ከዓምድ 45-5 7 ያሉት ዓምዶች "__" ይታለፋሉ፡፡

*ዓምድ 46-57 በዓምድ 33 ኮድ 2 ለተሞላላቸው ብቻ፡፡*

*በእነኚህ ዓምዶች የሚጠየቁት በዓምድ 33 ላይ "ሥራ እያሉት ነበር ባለፉት 7 ቀናት በ ሥራ ላይ ያልተሠማሩት?" ተብሎ ሲጠየቅ የለም ለመለሱ የቤተሰብ አባላት ብቻ ነው፡፡ ይህ ሁኔ ታ በመጠይቁ ክፍል 5 እንደ አርዕስት ሆኖ ባይቀመጥም መረጃ* ሰብሳቢው *እነኚህን ጥያቄዎች የሚ ያቀርበው በዓምድ 33 ኮድ 2 ለተሞላላቸው ብቻ መሆኑን መገንዘብ አለበት፡፡ በዓምድ 33 ኮድ 1 ለተሞላላቸው እነኚህ ዓምዶች በ "__" ይታለፉሉ፡፡*

**ዓምድ 46** **ባለፉት 3 ወራት ሥራ ለማግኘት ወይም የግል ሥራ ለመጀመር ጥረት አድርገው ነበር?**

በዚህ ዓምድ ሥራ የሌላቸው ነገር ግን ሥራ ቢያገኙ የሚሰሩ ሰዎች ባለፉት ሦስት ወራት (የጥናቱን ሣምንት ጨምሮ) ሥራ ለማግኘት ወይም የግል ሥራ ለመጀመር ጥረት ማድረጋቸውን እንጠይቃለን፡፡ የ ሥራ መፈለጉ ተግባር በሚፈለገው የሥራ ዓይነትና ጊዜ አይወሰንም፡፡ ይህም ማለት የሥራው ዓይነት የግል ሥራ፥ የትርፍ ግዜ ሥራ፥ ጊዜያዊ ሥራ፥ በወቅት የሚገኝ ወይም በዚህ ጥናት ውስጥ እንደሥራ ከሚቆጠ ሩት አንዱን ዓይነት የሥራ ዓይነት ለመጀመር ወይም ለመሥራት ጥረት ካደረጉ ሥራ እየፈለጉ እንደሆነ ይ ቆጠራል፡፡ መረጃ ሰጪው የሚሰጠው መልስ አዎን ከሆነ በተገቢው ካርድ ኮለም ኮድ 1 ይሞላል፤ የለም ከ ሆነ ደግሞ በካርድ ኮለሙ ኮድ 2 ተሞልቶ ወደ ዓምድ 48 ይታለፋል፡፡

**ዓምድ 47** **ሥራ ለማግኘት ወይም ለመጀመር ምን ጥረት አደረጉ?**

ይህ ጥያቄ የሚቀርበው በዓምድ 46 ላይ "አዎን" ለመለሱ ማለትም ሥራ እየፈለግኩ ነው ላሉት ብ ቻ ነው፡፡ በዚህ ዓምድ ሥራ ለማግኘት ወይም ለመጀመር ምን ተጨባጭ የሆነ ጥረት እያደረጉ እንደሆነ ተጠይቆ፥ በዚህ ጥያቄ ሥር ከተዘረዘሩት ውስጥ በተገቢው ዓምድ ያደረጉት አንዱ ጥረት ይመዘገባል፡፡ ከአ ንድ ዓይነት በላይ ጥረት ላደረጉ ዋነኛውን የሥራ መፈለጊያ ዘዴአቸውን ወይም ብዙ ጊዜ የሚከታተሉት /አንዱ/ ብቻ ይመዘገባል፡፡

አንድ ሰው የግል ሥራ ለመጀመር ጥረት እያደረገ ነው የሚባለው ስራ ለመጀመር የሚያስችለውን ገንዘብ፣ ቦታ ወይም የመስሪያ ዕቃዎች ለማግኘት የሚያስችለው ሁኔታዎች ለማመቻቸት ጥረት እያደረገ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ የግል ስራ ለመጀመር ከማሰብ አልፎ ዕቃ መግዛት፣ ቦታ ማፅዳት የመሳሰሉትን ሲሰራ የነበ ረ ሰው ግን በስራ ላይ ተሰማርቶ እንደነበረ ተቆጥሮ በዓምድ 30 ላይ ማስተካከያ መደረግ አለበት፡፡ የኮዶቹ ም ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1 =

የሥራ አጥ ካርድ አውጥቻለሁ ፡- ባለፉት 3 ወራት ውስጥ ከሚኖሩበት ቀበሌ ወ ይም ወረዳ ወይም የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ወይም ከሌላ ድርጅት ሥራ እንደሌ ላቸው የሚገልጽ ካርድ (ደብዳቤ) ያወጡ፣

2 =

የሥራ ማመልከቻ ለመ/ቤቶችና ድርጅቶች አስገብቼአለሁ፡- ባለፉት 3 ወራት ው ስጥ ሥራ ለመቀጠር ማመልከቻ ለመ/ቤቶች ወይም ድርጅቶች ያስገቡ፣

3 =

<u>በተለያዩ ቦታዎች የሚለጠፉ ማስታወቂያዎችን አነባለሁ</u> :- ባለፉት 3 ወራት ውስጥ የሥራ ዕድል ያለበትን ቦታ ለማወቅ ሲሉ የተለጠፉ ማስታወቂያዎችን ሲከታተሉ የነበሩ፡

4 =

<u>በጋዜጣ፣ በሬዲዮና በቴሌቪዥን እየተከታተልኩ ነው</u> :- ባለፉት 3 ወራት ውስጥ በሬድዮ፣ በጋዜጣ ወይም በቴሌቪዥን ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያዎችን ሲከታተሉ የነበሩ፡

5 =

<u>በዘመድ፣ በጓደኛ እየተከታተልኩ ነው</u> :- ባለፉት 3 ወራት ውስጥ ሥራ እንዲያስገቡአቸው ወይም ሥራ እንዲፈልጉላቸው ዘመድ ወይም ጓደኛ አማካይነት የሞከሩ፡

6 =

<u>ሥራ ያለባቸውን ቦታዎች ተዘዋውሬ እየጠየቅሁ ነው</u> :- የጉልበት ሥራ ወይም በግል እየተዘዋወሩ የሚሠሩ ሥራዎችን ለማግኘት በየቦታው ሲፈልጉ የነበሩ፡

7 =

<u>የግሌ ሥራ ለመጀመር እየሞከርኩ ነው</u> :- የግል ሥራ ለመጀመር ገንዘብ/የቦታ ወይም ሌሎች ሁኔታዎች እንዲሟሉላቸው ጥረት ያደረጉ፡

8 = <u>ሌላ/ይገለፅ/</u> :- ከላይ ከተዘረዘሩት የተለየ ጥረት ያደረጉ

<u>ማስታወሻ:-</u> ይህን ዓምድ የተጠየቁ በሙሉ ዓምድ 48 ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 49 ያልፋሉ::

## ዓምድ 48 <u>ለምንድነው ሥራ ለመሥራት ወይም ለማግኘት ጥረት ያላደረጉት</u>?

በዓምድ 46 ኮድ 2 ለተሞላላቸው ማለትም ባለፉት 3 ወራት ሥራ ለማግኘት ወይም ለመጀመር ምንም ጥረት ያላደረጉትን ሰዎች በዚህ ዓምድ ጥረት ያላደረጉበትን ምክንያት በመጠየቅ በዓምዱ ግርጌ ከተዘረዘሩት አማራጭ መልሶች ውስጥ ዋነኛው ምክንያት በዓምዱ ይመዘገባል:: በካርድ ኮለሙም ተገቢው ኮድ ይሞላል:: የኮዶቹም ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል::

01 =

<u>በሕመም፣ በአካል ጉዳት:-</u> ባይታመሙ ወይም አካል ጉዳት ባይደርስባቸው ኖሮ ባለፉት ሶስት ወራት ስራ ለማግኘት ወይም ለመጀመር ጥረት ያደርጉ የነበሩ፡

02 =

<u>በግል ወይም በቤተሰብ ጉዳይ:-</u> በራስ ወይም በቤተሰብ ምክንያት ሥራ ለማግኘት ጥረት ያላደረጉ (ከታች ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ)

03 =

<u>የቤት ውስጥ ሥራ/ኃላፊነት:-</u> ስራ ያልፈለጉት ወይም ጥረት ያላደረጉት በቤት ውስጥ ኃላፊነት ስላለባቸው፣ ለምሳሌ በቤት እመቤትነትና ልጅ አሳዳጊ ስለሆኑ፤

04 =

<u>እርጅና/ጡረታ:-</u> በእርጅና ወይም ዕድሜ በመግፋት እና ጡረታ በመውጣታቸው ምክንያት ባለፉት ሶስት ወራት ሥራ ያልፈለጉ፡

05 =

<u>በትምህርት/ስልጠና</u> :- በትምህርት/ስልጠና ላይ በመሆናቸው ምክንያት ባለፉት ሶስት ወራት ስራ ለመፈለግ ያልሞከሩ፤

06 =

<u>ሥራ አግኝቼ (የግል ሥራ) ለመጀመር በቀጠሮ ላይ ነኝ</u>:- የራሳቸውን የግል ሥራ ወይም በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ ተቀጥረው ሥራ ለመጀመር በሂደት ላይ ያለ ፡፤

07 =

<u>የቀድሞ ሥራዬ ለመመለስ እየተጠባበቅኩ ነኝ</u>:- ሥራ ለማግኘት ጥረት ያላደረጉ ት ወደ ቀድሞ ሥራቸው ለመመለስ ተስፋ ስላላቸውና እየተጠባበቁ ስለሆነ፤

08 =

<u>ሥራ አገኛለሁ ብዬ ስለማላስብ</u>:- ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ሥራ ለማግኘት ሞክ ረው ሳይሳካላቸው ተስፋ የቆረጡ እና በሌሎችም ምክንያቶች ባለፉት ሶስት ወራት ስራ ያልፈለጉት ከሥራ ዕድሉ መጥበብ የተነሳ ስራ አላገኝም በማለት ተስፋ የቆረጡትን ይ ጨምራል፤

09 =

<u>የግል ሥራ ለመጀመር የጥሬ/የገንዘብ/ የቁሳቁስ/ ዕቃ እጥረት ይኖራል ብዬ ስለ ማስብ</u>:- የግል ሥራ ለመጀመር ለሚያስቡ ሰዎች የግል ሥራ ያልጀመሩት በጥሬ/ገንዘብ ወይም በቁሳቁስ እጥረት ይኖራል ብለው የሚያስቡ፤

10 =

<u>ልጅ ስለሆነ/ች</u>:- ሥራ ለማግኘት ጥረት ያላደረጉት ዕድሜዬ ገና ለስራ ብቁ አይ ደለም ብለው ስለሚያስቡ፤

11 = <u>ሌላ(ይገለፅ)</u>:- ከላይ ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ውጭ ሥራ ለማግኘት ጥረት ያላደረጉት፤

<u>ማስታወሻ</u>

ኮድ 02 የሚሞላላቸው ከትምህርት፤ ከቤት ውስጥ ሥራ፤ ወይም ከመታ መም የተለየ ሌላ የግል ወይም የቤተሰብ ጉዳይ ለምሳሌ በሐዘን፣ ቤት በመጠበቅ፣ ዘመድ በማስታመም የመሳሰሉ በምርታማ ተግባር ውስጥ በማይካተቱ ሥራዎች ላይ የነበሩትን ነው::

## ዓምድ 49 <u>በሚቀጥለው 1 ወር ውስጥ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ ቢያገኙ ይሰራሉ</u>?

በዚህ ዓምድ ጥያቄ የምናቀርብላቸው "ስራ ያልሰሩ" ሰዎችን ነው:: ይህም ማለት በጥናቱ ወቅት በ ቅጥርም ሆነ በግል ምንም ዓይነት ሥራ ያልሰሩ እና ወደፊት የሚጀምሩት የተዘጋጀ ሥራ የሌላቸውን ማለ ት ነው:: ይህ ጥያቄ ሥራ እያላቸው በጥናቱ ሳምንት በተለያየ ምክንያት ሥራ ያልሰሩትን አይመለከትም::

መረጃ ሰጪዎች የጥናቱን ሣምንት ጨምሮ በአራት ሳምንታት ውስጥ "ስራ ቢያገኙ" እንደሚሰሩ ይ ጠየቃሉ:: የሚሰጡት መልስ በተገቢው ካርድ ኮለም ይመዘገባል:: ለዚህ ጥያቄ አዎን ለመለሱ በካርድ ኮለ ሙ ኮድ 1 ይሞላል:: የለም ለመለሱ ኮድ 2 ተሞልቶ ወደ ዓምድ 51 ይታለፋል:: መረጃ ሰጪው ከተጠቀሰ ው የጊዜ ገደብ ውጭ በኋላ መሥራት እንደሚችሉ እንኳን ቢነግሩአቸው የለም የሚለው ኮድ 2 ነው የሚ ሞላው:: ለምሳሌ ተማሪዎች ትምህርቴን እንደጨረስኩ መጀመር እችላለሁ ቢሉ ወይም አንድ ጉዳይ ያለበት

ሰው ጉዳዩን እንደጨረስኩ መሥራት እችላለሁ ቢል በዚህ ጥያቄ በተጠቀሰው ጊዜ ሥራውን መጀመር የማ ይችሉ ከሆነ በዓምዱ ኮድ 2 ይሞላላቸዋል።

ዓምድ 50

<u>በአቅምዎ ተቀጥረው ሊሰሩት የሚችሉት ስራ ቢገኝልዎት ወይም በግል ሥራ ለመ ሰማራት አስፈላጊ ነገሮች ቢሟሉ ስራ ለመጀመር ዝግጁ ነዎት? ከሆኑ የት?</u>

ይህ ጥያቄ የሚቀርብላቸው በዓምድ 49 ላይ አዎን ብለው ኮድ 1 ለተሞላላቸው ነው። በዚህ ዓም ድ በአቅማቸው ተቀጥረው ሊሰሩ የሚችሉት ሥራ ቢገኝላቸው ወይም የግል ሥራ ለመጀመር ሁኔታዎች ቢ መቻችላቸው (ስልጠና፣ ገንዘብና ቦታ ...ወዘተ) ለመሥራት ዝግጁ መሆናቸው ወይም አለመሆናቸው ይጠ የቃል። ዝግጁ ነኝ ለሚሉ የሥራ ቦታው የት ቢሆን ዝግጁ እንደሆኑ ይጠየቃሉ። በዚህ ጥያቄ ውስጥ ለማወ ቅ የተፈለገው መልስ ሰጪው በችሎታው መጠን ደመወዝ ሚያማርጥ ሥራ ቢያገኝ ለመስራት ፈቃደኛ መ ሆኑን ለማወቅ ነው። የኮዶቹ አሞላል (አማራጮቹ) ከዚህ በታች ቀርበዋል።

1 = <u>ዝግጁ አይደለሁም</u>

2 = <u>በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ብቻ</u> :-መኖሪያ ቤታቸው ካልሆነ በስተቀር ለመስራት ዝግጁ ያልሆኑ

3 = <u>በሚኖሩበት ከተማ/ገጠር ብቻ</u> :- ከሚኖሩበት ከተማ (ወይም ገጠር) ካልሆነ በስ ተቀር ለመስራት ዝግጁ ያልሆኑ

4 = <u>በማናቸውም ከተሞች፣</u> በማንኛውም የአገሪቱ ከተማ ለመስራት ዝግጁ የሆኑ (ቦ ታ የማያማርጡ)

5 = <u>በተገኘው ቦታ</u> :- በየትኛውም ሥፍራ (ገጠርም ከተማም) ለመሥራት ዝግጁ የሆኑ

6 = <u>ከአገር ውጪ ብቻ</u>:- በውጭ አገር እንጂ በአገር ውስጥ ስራ ቢያገኙ ለመሥራ ት ዝግጁ ያልሆኑ

ማስታወሻ:- በዓምድ 50 ከኮድ 2 – 5 የተሞላላቸው በሙሉ ወደ ዓምድ 53 ይሻገራሉ።

ዓምድ 51 <u>ለምንድነው ሥራ ቢያገኙ የማይሰሩት?</u>

በዚህ ዓምድ የሚጠየቀት በዓምድ 49 "የለም" ብለው ኮድ 2 ለተሞላላቸው ወይም በዓምድ 50 ኮ ድ 1 ለተሞላላቸው ማለትም ሥራ ቢያገኙ አልሰራም ወይም ዝግጁ አይደለሁም ላሉ ግለሰቦች ብቻ ነው። እነኚህ ሰዎች ሥራ ቢያገኙ ለመሥራት ዝግጁ ያልሆኑበት ዋና ምክንያት ምን እንደሆነ በዚህ ዓምድ ይመዘ ገብላቸዋል። ሥራ ቢያገኙ ሊሰሩ የማይችሉባቸው ምክንያቶች ይሆናሉ ተብለው የሚገመቱ አማራጮች ከዚ ህ በታች በዝርዝር ቀርበዋል። ግለሰቡ የሚሰጡትን መልስ ከተዘረዘሩት አማራጮች ጋር በማስተያየት ተስማ ሚውን ምክንያት በዓምዱ ክፍት ቦታ ሞልተን ተገቢውን ኮድ ደግሞ በካርድ ኮለሙ እንሞላለን። አንድ ሰ ው ሥራ ቢያገኝ ላለመስራት ከአንድ በላይ ምክንያት ሲኖረው በዝርዝሩ ላይ በቅድሚያ የተገኘውን እንወስ ዳለን። ለምሳሌ ተማሪው አካል ጉዳተኛ መሆኑን እንደምክንያት ቢያቀርብ በዝርዝሩ ላይ “ተማሪ“ በቅድሚያ ስለተዘረዘረ የምንሞላለት “ተማሪ“
የሚለውን ነው። ተማሪ ሆነው፣ ወይም የቤት ውስጥ ሥራ እየሠሩ፣ ወይም አካል ጉዳተኛ ሆነው <u>በምርታ ማ ተግባር ተሠማርተው ለነበሩ</u> የቤተሰብ አባላት
ይህ ጥያቄ ስለማይመለከታቸው በዓምዱ ላይ «-» ይደረጋል። ዋናው ምክንያት የሚመዘገበው በሚከተሉት ኮዶች አማካይነት ነው።

1 = <u>ያለክፍያ የቤት ውስጥ ሥራ ስለምሠራ</u> :- ያለክፍያ የቤት ውስጥ ሥራ ስለሚሰሩ፣

2 = <u>ተማሪ፣</u>

3 = <u>አካል ጉዳት</u> :- አካል ጉዳተኛነታቸው በምርታማ ተግባር ለመሠማራት ያገዳቸው፣

4 = <u>ሕመም፣</u>

5 =

<u>ልጅ</u> :- ልጅ ስለሆኑ ወይም አቅማቸው ለሥራ አልደረሰም ብለው ስለሚያስቡ ሥራ ቢያገኙ ለመሥራት ዝግጁ ያልሆኑ፡፡ ዕድሜያቸው 15 ዓመትና በላይ የሆኑ ይህ ዓምድ ሊሰጣቸው አይችልም፡፡ በመማር ላይ የሚገኙ የሚሞላላቸው ኮድ 2 እንጂ ኮድ 5 አይደለም፣

6 = <u>ሴተኛ አዳሪ</u> :- በሴተኛ አዳሪነት የሚተዳደሩ በመሆናቸው፣

7 =

<u>ጡረታ /እርጅና</u> :- በእርጅና ምክንያት ወይም ጡረተኛ ስለሆኑ ለመሥራት ዝግጁ ያለሆኑ ይህ ኮድ ይሞላላቸዋል፡፡ እነዚህ ግለሰቦች በቤት አበል፣ በጡረታ፣ ባጠራቀሙት ገንዘብ፣ በቤት ኪራይ ገቢ ወይም በቤተሰብ ዕርዳታ የሚተዳደሩ ናቸው፤

8 = ሌላ /ይገለጽ/ :- ከላይ ከተጠቀሱት በተለየ ምክንያት ለመሥራት ዝግጁ ያልሆኑ፡፡

## ዓምድ 52 <u>ለምን ከቤት ውስጥ ሥራ ወጭ መስራት አይፈልጉም?</u> (በዓምድ 51 ኮድ 1 ለተሞላላቸው (በቤት ውስጥ ስራ ለተሰማሩ))

በዓምድ 51 ላይ ሥራ ባገኝ የማልሠራው በቤት ውስጥ ሥራ ስለተሰማራሁ ነው ላሉ በዚህ ዓምድ ለምን ከቤት ውስጥ ሥራ ውጭ መስራት እንደማይፈልጉ ይጠየቃሉ፡፡ የሚሰጡትም መልስ በሚከተሉት ኮዶች አማካይነት ይመዘገባል፡፡ ለዓምዱ በተሰጠው ክፍት ቦታም ምክንያታቸው ይፃፋል፡፡

1 = በቂ ገቢ ስላለኝ

2 = ከትዳር ጋር ስለማይመች

3 = ትምህርት/ሙያ ስለሌለኝ

4 = የልጆች እናት/አሳዳጊ ስለሆንኩ

5 = ለቤተሰብ ገቢ ማምጣት የባል ጉዳይ ስለሆነ

6 = በጤንነት ምክንያት

7 = ሌላ /ይገለጽ/

## ዓምድ 53 <u>የሚፈልጉት ሥራ ምን ዓይነት ነው?</u>

ለመረጃ ሰብሳቢ:- ለመልስ ሰጭው አማራጮችን አሳውቃቸው/ቂያቸው፡፡

በዓምድ 49 አዎን ብለው ኮድ 1 ለተሞላላቸው እንዲሁም በዓምድ 50 ከኮድ 2 – 6 ለተሞላላቸው ማለትም ስራ ብናገኝ እንሠራለን ላሉና ለመሥራት ዝግጁ ሆነው የሚሰሩበትን ቦታ ለገለፁ በዚህ ዓምድ ይጠየቃሉ። አማራጭ መልሶቹም ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

1 = <u>የራስን ድርጅት ማቋቋም፡</u>- የግል ሥራ ለመጀመር የራሳቸውን ድርጅት ማቋቋም ለሚፈልጉ፤

2 = <u>በቅጥር-በግል ድርጅት፡</u>- በግል ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው መሥራት ለሚፈልጉ፤

3 = <u>በቅጥር-ለመንግሥት፡</u>- በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ ተቀጥረው መሥራት ለሚፈልጉ፤

4 = <u>የተገኘውን፡</u>- በግል ወይም በመንግሥት ወይም በማናቸውም በተገኘው ቦታ ተቀጥረው መሥራት ለሚፈልጉ፤

5 = <u>ሌላ(ይገለፅ)፡-</u> ከላይ ከተዘረዘሩት ውጭ የተለየ ዓይነት ሥራ ለሚፈልጉ፤

<u>ማስታወሻ</u>፤ በዚህ ዓምድ ከኮድ 2 – 5 የተሞላላቸው ወደ ዓምድ 55 ያልፋሉ።

## ዓምድ 54 <u>የራስን ድርጅት ለማቋቋም የገጠሞት/የሚገጥሞት ችግር አለ ካለ ምንድነው</u>?

(በዓምድ 53 ኮድ 1 ለተሞላላቸው (የራስን ድርጅት ማቋቋም ለሚፈልጉ)

በዓምድ 53 የራስን ድርጅት ማቋቋም እንደሚፈልጉ ለገለጹ /ኮድ 1 የተሞላላቸው/ ማቋቋም የሚፈልጉትን ድርጅት ለማቋቋም የገጠማቸው ወይም ይገጥመኛል ብለው የሚያስቡት ችግር ካለ በሚከተሉት ኮዶች አማካይነት ይገለጻል።

00 = ችግር የለብኝም

01 = የገንዘብ እጥረት

02 = ሥልጠና አለማግኘት

03 = ቦታ (መሬት) አለማግኘት

04 = ገንዘብና ሥልጠና አለማግኘት

05 = ገንዘብና ቦታ አለማግኘት

06 = የመሥሪያ ፈቃድ አለመኖር/ማጣት

07 = የማምረቻ መሣሪያ አለመሟላት/ማጣት

08 = አላውቅም

09 = ሌላ/ይገለጽ/

## ዓምድ 55 <u>ለምን ያህል ወራት ያለ ሥራ ቆይተዋል?/በወራት ይገለፅ/</u>

ስራ የሌላቸውና ስራ ለመስራት ዝግጁ መሆናቸው የገለፁ ግለሰቦች ለምን ያህል ወራት ያለሥራ እንደቆዩ ተጠይቆ በካርድ ኮለሞቹ ይሞላል:: 1 ወር ላልሞላቸው ኮድ 00 ሲሞላ 97ና በላይ ወራት (ከ8 ዓመት በላይ) ለሆናቸው ኮድ 97 ይሞላል::

## ዓምድ 56 <u>ከዚህ በፊት በቅጥር ወይም በግል ሥራ ሠርተው ያውቃሉ?/ለሥራ አጦች/</u>

ሥራ አጥ የሆኑ ግለሰቦች ሁሉ በሁለት ክፍሎች ይመደባሉ:: እነዚህም የመጀመሪያ ጊዜ ሥራ አጦች (ሥራ ይዘው የማያውቁ) እና ምንም እንኳን በወቅቱ ሥራ አጥ ቢሆኑም ከዚህ በፊት ሥራ የነበራቸው ሥራ አጦች ናቸው:: በዚህ ዓምድ ውስጥ ሥራ አጦች ሁሉ / ዓምድ 50 ከኮድ 2-5/ሥራ ከማጣታቸው በፊት ሥራ ይዘው ያውቁ እንደሆነ ይጠየቃሉ:: ከዚህ በፊት ሥራ የነበራቸው የሚባሉት ከላይ እንደተገለጸው ሁሉ በግላቸው ወይም ለቤተሰቡ ገቢ በሚያስገኝ ምርታማ ተግባር ላይ በአንድ ወቅት ተሠማርተው የነበሩ ግለሰቦች ሁሉ ናቸው:: ከዚህ በፊት ሥራ ያልነበራቸው የሚባሉት ደግሞ በምንም ዓይነት ገቢ በሚያስገኝ ምርታማ ተግባር ተሠማርተው የማያውቁ የቤተሰብ አባላት ናቸው:: ሥራ አጥ የሆኑ ግለሰቦች ሁሉ ከዚህ በፊት ሥራ እንደነበራቸው ተጠይቀው መልሱ በሚከተሉት ኮዶች አማካይነት ይመዘገባል:: ከዚህ በፊት ሥራ ለነበራቸው ሥራ አጦች ኮድ 1 ሲሞላ ከዚህ በፊት ሥራ ላልነበራቸው ሥራ አጦች ደግሞ ኮድ 2 ተሞልቶ ወደ ልጆች መጠይቅ ክፍል 6 ይታለፋል::

## ዓምድ 57 <u>ለምን የቀድሞ ሥራዎን መስራት አቆሙ ?</u>

ከዚህ በፊት ሥራ ሰርተው ለሚያውቁ (በዓምድ 56 ኮድ 1 ለተሞላላቸው) የቀድሞ ሥራቸውን የተውበት ወይም የለቀቁበት ምክንያት ተጠይቆ በሚከተሉት ኮዶች አማካይነት ይመዘገባል::

01 = <u>ለመማር</u> :- ትምህርት ቤት ለመግባት (ለመማር) ብለው የለቀቁ፡

02 = <u>በሕመም/አደጋ</u>:- ስለታመሙ ወይም አደጋ ስለደረሰባቸው ከስራ የለቀቀ /ሥራውን ያቋረጡ/፡

03 = <u>ለግል/የቤተሰብ ጉዳይ</u> :- ከስራ የሚያስቀር የግል ወይም የቤተሰብ ጉዳይ ስላላቸው ሥራቸውን የተው ለምሳሌ ልጅ ለማሳደግ፡ በሽተኛ ማስታመም፡ ...ወዘተ፡

04 = <u>ድርጅቱ ስለተዘጋ/ስለዘጋሁት</u> :- የሚሰሩበት ድርጅት ሥራ በማቆሙ ወይም የግል ድርጅታቸውን ገበያ በማጣት ወይም በተለያየ ምክንያት ስለዘጉት ሥራውን የተው፡

05 = <u>ከስራ ስለተቀነስኩ</u>:- ከሚሰሩበት ድርጅት እንዲወጡ/እንዲቀነሱ በመደረጉ ሥራ የተው፡

06 = <u>ክፍያ ስላነሰኝ</u>:- ክፍያ ስላነሳቸው ቀድሞ ይሰሩበት የነበረውን ሥራ የተው፡

07 = <u>ከአሰሪዬ/ቀጣሪዬ ጋር ስላልተስማማሁ</u>:- ከአሰሪያቸው/ቀጣሪያቸው ጋር ባለመስማማት ሥራ የተው፡

08 = <u>ስራው ለጤናዬ ስላልተስማማኝ</u>:- ይሰሩት የነበረው ሥራ ለጤናቸው ስላልተስማማቸው፡

09 = <u>የስራ ቦታውን ስላልወደድኩት</u>:- ይሠሩበት የነበረውን የሥራ ቦታ ስላልወደዱት ከሥራው የለቀቁ፡

10 =

<u>ከትዳሬ ጋር ስላላመቹኝ</u>፡- ትዳር በመያዛቸው ምክንያት ወይም ከትዳራቸው ጋር ሥራውን ማስኬድ ስላልቻሉ ሥራቸውን የለቀቁ /ያቋረጡ/፡፡

11 = <u>ሌላ ይገለፅ</u>፡- ከላይ ከተዘረዘሩት በተለየ ምክንያት ሥራቸውን የተው፡፡

# ምዕራፍ 5 የክፍል 6 አሞላል መመሪያ

## ክፍል 6 ዕድሜያቸው ከ5-14 ዓመት ለሆናቸው ልጆች የሥራ ሁኔታ (ከዓምድ 58-69)፣

ማስታወሻ:- የዚህ ክፍል መረጃዎች ከመሞላታቸው አስቀድሞ በመጠይቁ ራስጌ ላይ በተዘጋጀው ሥፍራ የተመረጠው ን ቤተሰብ አድራሻና የአካባቢ መለያ ከገፅ 1 ክፍል 1 ማወራረስ ያስፈልጋል።

ይህ ክፍል ዕድሜያቸው ከ5-14 ዓመት ለሆኑ የቤተሰቡ አባላት የትምህርት ሁኔታ፣ የሥራ ሁኔታ፣ የወላጆች በሕይወት መኖር አለመኖር እና የወላጆች በትዳር ላይ መሆን አለመሆን የሚጠየቅበት ነው። በዚህ ክፍል የመረጃ አሞላሉ አመቺ የሚሆነው ለእያንዳንዱ አባል ከዓምድ 58-69 ያሉትን ጥያቄዎች ወደጎን በማጠናቀቅ ወደሚቀጥለው የቤተሰቡ አባል በመሸጋገር ስለሆነ በዚሁ መሠረት መረጃውን መሙላት ያስፈልጋል። በዚህ ክፍል የቀረቡት ጥያቄ ዎች በተቻለ መጠን ከሚመለከታቸው ልጆች መሰብሰብ ይኖርበታል። ሆኖም አንዳንድ ጥያቄዎችን ልጆቹ መልስ ለ መስጠት ከቸገራቸው ሌላው የቤተሰብ አባል ሊያግዛቸው ይችላል።

### ዓምድ 11 እና 10

ዓምድ 11 «ሙሉ ስም» እና ዓምድ 10 «የመስመር ቁጥር» ሲሆን ይህም ከገጽ 1 ዓምድ 11 እና 10 ሁሉም የቤተሰብ አባላት ቅደም ተከተላቸው እና የመስመር ቁጥራቸው እንደጠበቁ የሚዛወሩበት ነው፡ ፡ በእነዚህ ዓምዶች ሁሉም የቤተሰብ አባላት የሚተላለፉ ቢሆንም ከ58-69 ያሉት ዓምዶች የሚየጠቁት ዕድ ሜአቸው ከ5-14 የሆናቸው ብቻ ናቸው። ከተጠቀሰው ዕድሜ ክልል (5-14 ዓመት) ውጭ የሆኑ የቤተሰቡ አባላት ከ58-69 ያሉት ዓምዶች ስለማይመለከታቸው በሠረዝ «____ » ይታለፋሉ። በተጨማሪም ከገጽ 1 ዓምድ 14 ዕድሜአቸው ከ5-14 ዓመት የሆኑትን ልጆች በመለየት ሁሉም በዚህ ክፍል ሳይጠይቁ እንዳይዘ ሉ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

### ዓምድ 58 በያዝነው የትምህርት ዘመን የመደበኛ ትምህርት እየተማርክ/ሽ ነው?

ጥናቱ በሚካሄድበት ዓመት ባለው የትምህርት ዘመን ዕድሜአቸው ከ5-14 ዓመት የሆናቸው የቤተ ሰቡ አባላት ትምህርት እየተማሩ መሆንና አለመሆናቸው ተጠይቆ እየተማሩ ላሉ በካርድ ኮለሙ ኮድ «1» ተሞልቶ ወደ ዓምድ 62 ይታለፋል። በያዝነው የትምህርት ዘመን ለማይማሩ ኮድ 2 ይሞላል። <u>በዚህ ዓመት ለመማር ተመዝግበው ነገር ግን ትምህርታቸውን ያቋረጡ የቤተሰቡ አባላት በመማር ላይ እንዳሉ ተደርጎ እንዳይመዘገብ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።</u> ይህ ዓምድ መደበኛ ትምህርትን የሚመለከት ቢሆንም በቄስ/ቀ ርዓን ት/ቤቶች፣ በመዋዕለ ህፃናት ትምህርት እየተከታተሉ ያሉትን እንደሚጨምር መገንዘብ ያስፈልጋል።

### ዓምድ 59 ከዚህ ቀደም ተምረህ/ሽ ነበር?

ይህ ዓምድ በዓምድ 58 ኮድ 2 የተሞላላቸው የቤተሰብ አባላትን ብቻ የሚመለከት ነው። ማለትም በያዝነው የትምህርት ዘመን በትምህርት ላይ ለማይገኙት ከጥናቱ ዓመት በፊት ባሉት በማናቸውም ዓመታ ት ውስጥ ተምረው ያውቁ እንደሆነና እንዳልሆነ ተጠይቆ ከተሰጡት 3 አማራጭ መልሶች ውስጥ አንዱን ብቻ የምንሞላበት ዓምድ ነው። በዚህ ዓምድ ምንም ተምሬ አላውቅም ብለው ኮድ 3 ለተሞላላቸው አባላት በቀጥታ ወደ ዓምድ 61 በመሻገር ባለፉት 7 ቀናት (ሳምንት) ምን ይሠሩ እንደነበር ይጠየቃሉ።

1 = <u>በዚህ ዓመት ጀምሬ አቋርጬአለሁ</u>:- በያዝነው የትምህርት ዘመን በመደበኛ ት/ቤት ትምህርት ጀምረ ው ነገር ግን ትምህርታቸውን በተለያዩ ምክንያቶች በማቋረጣቸው በመማር ላይ ለማይገኙ ልጆች ይህ ኮድ ይሞላላቸዋል። በተለያየ ምክንያት ለጥቂት ቀናት ከትምህርት ገበታ ቀርተው ነገር ግን ወደ ትምህርታቸው መመለስ የሚፈልጉና ት/ቤቱም እንዲመለሱ የሚፈቅድላቸው ልጆች ጀምረው እንዳቋረጡ አይቆጠርም።

2 = <u>ከዚህ ዓመት በፊት ተምሬ ነበር፡-</u> ከጥናቱ ዓመት በፊት በነበረ በማንኛውም ዓመት በመደበኛ ት/ቤት ተምረው የነበሩ የቤተሰቡ አባላት የሚሞላላቸው ኮድ ነው፡፡ ተምረው ያቋረጡ ሲባል ባለፉት ዓመታት ውስጥ ቢያንስ አንድ የተወሰነ ክፍልን አጠናቀው ያቋረጡ ማለት ነው፡፡

3 = <u>ምንም ተምሬ አላውቅም፡-</u>

በጥናቱ ዓመትም ሆነ ከጥናቱ ዓመት በፊት መደበኛም ሆነ መደበኛ ባለሆኑ ት/ቤቶች ምንም ተምረው ለማያውቁ ልጆች የሚሞላ ኮድ ነው፡፡

## ዓምድ 60 <u>ትምህርት ያቋረጥክበት/ሽበት ምክንያት ምንድነው?</u>

ይህ ዓምድ በዓምድ 59 በዚህ ዓመት ጀምሬ አቋርጫለሁ በማለት ኮድ «1» ለተሞላላቸውና ከዚህ ዓመት በፊት ተምሬ ነበር በማለት ኮድ «2» ለተሞላላቸው ልጆች የሚጠየቅ ሲሆን ትምህርት ያቋረጡበት ምክንያት ከተዘረዘሩት አማራጭ መልሶች ውስጥ ተቀራራቢ ከሆኑት ዋነኛ የሆነውን ምክንያት ብቻ በዓምዱ በተሰጠው ክፍት ቦታ በአጭሩ ተመዝግቦ ኮዱ በካርድ ኮለሙ ይሞላል፡፡ ለምሣሌ ልጁ በያዝነው የትምህርት ዓመት ወይም ከዚያ በፊት ትምህርቱን ጀምሮ ያቋረጠው በበሽታ ምክንያት ከሆነ ከተሰጡት አማራጮች መካከል «ሕመም» የሚለው በዓምዱ ተመዝግቦ በካርድ ኮለሙ ኮድ «01» ይሞላለታል፡፡ ከአንድ በላይ በሆኑ ምክንያቶች ትምህርቱን ላቋረጠ ዋናውን ብቻ እንዲመርጥ ይደረጋል፡፡ ለምሣሌ በሕመምና በቤተሰብ የማስተማር አቅም ማጣት ምክንያት ላቋረጠ ከሁለቱ ዋነኛው ምክንያት ተለይቶ ይሞላል፡፡ የኮዶቹም ዝርዝር ከዚህ በታች ተገልጿል፡፡

01= <u>በሕመም፣</u>
02= <u>በቤተሰብ የማስተማር አቅም ማጣት፣</u>
03= <u>በቤተሰብ ውስጥ ሠላም ማጣት፣</u>
04= <u>የቤተሰብ መበተን፡-</u> ቤተሰባቸው ባለመግባባት፣ በፍቺ፣ በሞት በመለያየታቸው ምክንያት ትምህርት ያቋረጡ፣
05= <u>በቤተሰብ ዝውውር፡-</u> ቤተሰባቸው ሥራ በማግኘቱ፣ የመ/ቤቱ አድራሻ በመቀየሩ፣ ለሥራ ወይም በሌላ ምክንያት ከሚኖሩበት ወደ ሌላ አካባቢ በመዛወራቸው ምክንያት ትምህርት ያቋረጡ፣
06= <u>ት/ቤቱ ሩቅ ስለሆነ፣</u>
07= <u>ሥራ ለመስራት፡-</u> እራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ለመርዳት ሲሉ ሥራ የሚሠሩና በዚህም ምክንያት ትምህርት ያቋረጡ፣
08= <u>ከትምህርት ስለወደኩ፣</u>
09= <u>በጋብቻ ምክንያት፡-</u> በዚህ ዕድሜ ክልል (5-14 ዓመት) የሚገኙ ልጆች በማግባታቸው ምክንያት ትምህርት ያቋረጡ፣
10= <u>በቤተሰብ ማስተማር አለመፈለግ፡-</u> ቤተሰባቸው በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ትምህርት እንዳይማሩ በማድረግ ወይም በመከልከል ትምህርት ያቋረጡ፣
11= <u>በመፈናቀል፡-</u> ከቤተሰባቸው ጋር በጦርነት በረሀብ ...ወዘተ በመፈናቀል ትምህርት ያቋረጡ፣
12= <u>ሌላ (ይገለፅ)</u>፡- ከላይ ከተገለፁት ውጭ በሌላ ምክንያት ትምህርት ያቋረጡ፣

## ዓምድ 61 <u>ባለፉት 7 ቀናት ምን እየሠራህ/ሽ ነበር?</u>

ይህ ዓምድ የሚጠየቅላቸው በያዝነው የትምህርት ዘመን ለማይማሩት ማለትም በዓምድ 58 የለም ብለው ኮድ «2» ለተሞላላቸው ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ በያዝነው ዓመት እየተማሩ ላሉ ባለፈው 7 ቀናት (ሳምንት) ምን እየሠሩ እንደሆነ በዚህ ዓምድ እንዳይጠየቁ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ አንድ ልጅ ባለፉት 7 ቀናት (ሳምንት) እንደሠራ የሚቆጠረው (ከኮድ 1-6 የሚሞላለት) በእነዚህ ቀናት ውስጥ በድምሩ ቢያንስ 4 ሰዓት ያህል ከሰራ ነው፡፡ በጥያቄው ሥር ለቀረቡ እማራጭ ኮዶች ማብራሪያ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1= <u>ለቤተሰብ-በግብርና ሥራ፡-</u>

ይህ ኮድ የሚሞላላቸው ቤተሰቦቻቸውን ያለክፍያ በተለያዩ የግብርና ሥራዎች እያገዙ ላሉ ልጆች ነው፡፡ ለምሣሌ በማረስ፣ በመጎልጎል፣ በመዝራት፣ በማረም፣ በማጨድ፣ በመሰብሰብ ወይም ከብቶችን በመጠበቅ

ና በመሳሰሉት የግብርና ሥራዎች ውስጥ በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ በሆነ ሥራ ላይ ለተሠማሩ ይህ ኮድ ይ ሞላላቸዋል።

2 = <u>ለቤተሰብ-ከግብርና ሌላ ምርታማ ሥራ፡-</u>
ቤተሰቦቻቸውን ከግብርና ውጪ በምርታማ ሥራ ለምሣሌ በዕደጥበብ፣ በንግድና በመሳሰሉት ዘርፎ ች ያለክፍያ ለሚያገለግሉ ልጆች የሚሞላ ኮድ ነው።

3 = <u>በቅጥር-በግብርና ሥራ፡-</u> ይህ ኮድ በተለያዩ የግብርና ሥራዎች በክፍያ ተቀጥረው ለሚሠሩ ልጆች የሚሞ ላ ነው። ለምሣሌ፡- ለሚኖርበት ቤተሰብ ወይም ለሌላ ቤተሰብ በእረኝነት እየተከፈለው የሚሠራ ልጅ እንዲ ሁም ተቀጥሮ በግብርና ሥራ ለተሠማራ በዓምዱ በተሰጠው ክፍት ቦታ «በቅጥር-በግብርና ሥራ» ተብሎ ይፃፍና በካርድ ኮለሙ ኮድ 3 ይሞላል።

4 = <u>በቅጥር-ከግብርና ሌላ ሥራ</u>፡- ከግብርና ሥራ ውጭ እንደ ንግድና ዕደጥበብ በመሳሰሉት ምርታማ ሥራዎች ውስጥ ለተሰማሩ ወይም ለሌላ ቤተሰብ በክፍያ ተቀጥረው የሠሩ/የሚሠሩ ልጆችን የሚመለከት ነው። ለምሣ ሌ፡- በክፍያ ሱቅ ውስጥ የማሻሻጥ ሥራ የሚሠራ ልጅ ይህ ኮድ ይሞላለታል።

5 = <u>በክፍያ-የቤት ሠራተኝነት፡-</u> ለሚኖሩበት ቤተሰብ ወይም ለሌላ ቤተሰብ በቤት ሠራተኝነት ተቀጥረው በክፍ ያ ለሚሠሩ ልጆች የሚሞላ ኮድ ነው። አንዳንድ ልጆች ክፍያውን በቀጥታ ላያገኙ ይችላሉ። ማለትም ክፍ ያውን ወላጆቻቸው እየተቀበሉ እነሱ በጉልበት የሚያገለግሉበት ሁኔታ ስላለ ያለክፍያ-የቤት ውስጥ ሥራ ተብሎ እንዳይመዘገብ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። በተጨማሪ ክፍያ በገንዘብ ወይም በዓይነት ወይም በገንዘብና በዓይነት ሊሆን ይችላል። እንዲሁም አከፋፈሉ በቀን፣ በሳምንት፣ በወር፣ በዓመት ወይም በሌላ አመቺ መንገ ድ ሊፈፀም ይችላል።

6 = <u>በግል ሥራ</u>፡- በራሱ የግል ሥራ ወይም ድርጅት ውስጥ የሚሰራ ልጅ የግል ሥራ እንደሰራ ይቆጠራል። ለም ሳሌ ሊስትሮነት፣ ልዩ ልዩ ሸቀጣ ሸቀጦች መነገድ፣ ...ወዘተ። እንዲሁም በቤተሰብ ኃላፊነት (ያለክፍያ) ቤ ተሰቡን በማስተባበር ሥራቸውን የሚያካሂዱ ልጆችም በዚህ ኮድ ይካተታሉ።

7 = <u>ያለክፍያ-የቤት ውስጥ ሥራ</u>፡- በቤት ውስጥ ወላጆቻቸውን/አሳዳጊዎቻቸውን ወይም ሌላ ቤተሰብን
በቤት ውስጥ ሥራ ያለክፍያ ለሚያገለግሉ ልጆች
የሚሞላ ኮድ ነው። የቤት ውስጥ ሥራ ማለት ለቤተሰቡ አባላት ጥቅም እንደ ምግብ ማዘጋጀት፣ ልብስ ማጠብ፣ ልጅ ማሳደግ፣ መላላክ የመሣሰለው ነው። ነገር ግን ማጥናት፣ ኳስ ወይም ሌላ ነገር መጫወት እንደ ቤት ውስጥ ሥራ መቆጠር የለባቸውም።

8 = <u>ምንም አልሠራሁም፡-</u> በተለያየ ምክንያት ባለፈው ሳምንት ምንም ሥራ ያልሠሩ ልጆች በዚህ ኮድ ሥር ይካተታሉ። ለምሣሌ፡- በሕመም፣ በአደጋ፣ ዕድሜአቸው ለሥራ ባለመድረሱና በመሳሰሉት ምክንያት ባለፉት 7 ቀናት (ሳምንት) ያልሠሩ ልጆችን ይመለከታል።

ዓምድ 62 <u>ባለፉት 7 ቀናት (ሳምንት) ከትምህርቱ በተጨማሪ ምን እየሠራህ/ሽ ነበር?</u>

ይህ ዓምድ የሚሞላው በያዝነው የትምህርት ዘመን እየተማሩ ላሉ ልጆች ማለትም በዓምድ 58 ኮ ድ «1» ለተሞላላቸው ብቻ ነው። የሚጠየቁትም ባለፉት 7 ቀናት (ሳምንት) ከትምህርታቸው በተጨማሪ ለ ራሳቸው/ለቤተሰብ/ ወይም ለሌላ ድርጅት በምን ዓይነት ሥራ ላይ እንደተሰማሩ ነው። ከትምህርታቸው ው ጭ ሌላ ምንም ሥራ ያልሰሩ ከሆነ ኮድ «8» ተሞልቶ «ምንም አልሠራሁም» በዓምዱ በተሰጠው ክፍት ቦ ታ ይመዘገባል። ለዚህ ጥያቄ የቀረቡት አማራጮችና ፅንሰ-ሀሳቦቹ ከላይ ለዓምድ 61 ከተሰጡት ጋር አንድ ዓይነት ስለሆኑ በዚያ የተሰጠውን መግለጫ መመልከት ይገባል። በዚህ ዓምድ ኮድ 7 ያለክፍያ የቤት ውስ ጥ ሥራ የሠሩና ኮድ 8 ምንም አልሠራሁም ብለው የመለሱ ወደ ዓምድ 66 ይሻገራሉ።

ዓምድ 63 <u>ለመጀመሪያ ጊዜ ሥራ መስራት የጀመርከው/ሽው በስንት ዓመት/ሽ ነው?</u>
<u>(ዕድሜ በሙሉ</u>
<u>ዓመት ይመዝገብ)</u>

ባለፉት 7 ቀናት (ሳምንት) በምርታማ ስራ ላይ እንደተሰማሩ ለገለፁ (በዓምድ 61 ወይም በዓምድ 62 ከኮድ 1-6 ከተገለፁት አንዱ ኮድ ለተሞላላቸው) በዚህ ዓምድ በተሰጡት ካርድ ኮለሞች ልጁ/ልጅቷ ሥራ መስራት የጀመረበት/ችበት ዕድሜ በሙሉ ዓመት ይመዘገባል፡፡ ሥራ መስራት ሲባል ማንኛውንም ም ርታማ ሥራ በክፍያም ሆነ ያለክፍያ (በዓምድ 61 ወይም በዓምድ 62 ከኮድ 1-6 ሊካተት የሚችል ሥራ) መስራት ማለት ነው፡፡

## ዓምድ 64 <u>ለመጀመሪያ ጊዜ ሥራ ለመስራት ያበቃህ/ሽ ምክንያት ምንድነው?</u>

ይህ ዓምድ በዓምድ 61 ወይም በዓምድ 62 ላይ ያለ ክፍያ የቤት ውስጥ ሥራ ሠርቼአለሁ በማለት ኮድ «7» ወይም «ምንም ሥራ አልሠራሁም» ብለው ኮድ «8» ከተሞላላቸው ውጭ ሁሉንም ልጆች የሚ መለከት ነው፡፡ ምክንያቶቹም ራስን ለመርዳት፣ ቤተሰብን ለማገዝ ወይም ለቤተሰብ ገቢ ለማስገኘትና የመሳ ሰሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለምሣሌ፡- አንድን ልጅ «ለመጀመሪያ ጊዜ» ሥራ ለመሥራት ያበቃው ምክንያት ቤ ተሰቡን በግብርና ሥራ ለማገዝ ከሆነ «በግብርና ሥራ ቤተሰብን ለማገዝ» የሚለው በዓምዱ ተመዝግቦ ኮድ 1 በካርድ ኮለሙ ይሞላል፡፡ ምክንያቶቹ ከአንድ በላይ ለሆነ ልጅ አንዱና ዋነኛው ብቻ ተለይቶ ይመዘገብለ ታል፡፡ የኮዶቹም ዝርዝር ከዚህ በታች ተገልፀዋል፡፡

<u>ማሳሰቢያ</u>፡- ኮድ 3 ለዚህ ጥያቄ ስለሚያገለግል እንደ መልስ አይሞላም፡፡ በመጠይቁም ላይ ይህ አማራጭ መልስ ይሰረዛል፡፡

1 = <u>ቤተሰብን ለማገዝ- በግብርና ሥራ፡-</u> ሳይከፈላቸው ቤተሰባቸውን በግብርና ሙያ ለመርዳት ሲሉ ሥራ የሚሠሩ፣ ለምሳሌ በማረስ፣ በመጎልጎል፣ ...ወዘተ፣

2 = <u>ቤተሰብን ለማገዝ ከግብርና ውጭ በቤተሰብ ድርጅት ውስጥ፡-</u> ሳይከፈላቸው ቤተሰባቸውን ለመርዳት ሲሉ ከግብርና ውጭ በሆነ በሌላ ቤተሰብ ድርጅት ውስጥ የሚሠሩ ለምሳሌ በ ንግድ፣ በዕደጥበብ ...ወዘተ፣

3 = <u>ቤተሰብን ለማገዝ - በቤት ውስጥ ሥራ</u>፡-

4 = <u>ለቤተሰብ ገቢ ለማስገኘት ፡-ከቤተሰብ ድርጅት ውጭ ሠርቼ</u>፡- ቤተሰባቸውን በገንዘብ ለመ ርዳት ሲሉ ከቤተሰብ ድርጅት ውጭ ለምሳሌ ተቀጥሮ ሱቅ ውስጥ መስራት፣ በጋራዥ ሠ ራተኝነት፣ ሥራ የሚሠሩ፣ ...ወዘተ፣

5 = <u>እራሴን ለመርዳት</u>፡- እራሳቸውን ለመርዳት ሲሉ ሥራ የሚሠሩ ለምሳሌ ሊስትሮ፣ ጋዜጣ ሻ ጭ፣ ቆሎ ሻጭ፣ ...ወዘተ፣

6 = <u>ሌላ (ይገለፅ)</u>፡- ከላይ ከተጠቀሱት ውጭ በሌላ ምክንያት ሥራ የሚሠሩ፣

## ዓምድ 65 <u>በሥራህ/ሽ ምክንያት በአካልህ/ሽ ላይ የገጠመህ/ሽ ጉዳት አለ? ካለ ደረጃው?</u>

በዚህ ዓምድ የቤተሰቡ አባላት የሆኑ ልጆች በሥራቸው ምክንያት ጉዳት ደርሶባቸው ከሆነ የጉዳቱ ዓይነትና መጠኑ በዓምዱ ተመዝግቦ ኮዱ በካርድ ኮለሙ ይሞላል፡፡ በሥራቸው ምክንያት ጉዳት ላልደረሰባቸ ው በዓምዱ በተሰጠው ክፍት ቦታ «አልደረሰብኝም» ተመዝግቦ በካርድ ኮለሙ ኮድ 3 ይሞላል፡፡ ጉዳት የ ደረሰባቸው ልጆች የደረሰባቸውን ጉዳት መጠን መግለጽ ሊቸግራቸው ስለሚችል መረጃ ሰብሳቢው ጉዳቱን እንዲያሳዩት ወይም በዝርዝር እንዲገልፁለት በማድረግ መጠኑን ከባድ ወይም መጠነኛ መሆኑን ለመለየት የሚያስችሉ ጥያቄዎችን በማቅረብ መለየት ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ልጆቹ ጉዳቱ/አደጋው ከደረሰባቸው ጊዜው የቆየ ሊሆን ስለሚችልና በጥናቱ ወቅት ጉዳቱ ላይታይ ስለሚችል ጥያቄው ሲቀርብ በተቻለ ማብራ ራት ይኖርበታል፡፡ እዚህ ላይ ጉዳት አደጋ ሲባል በሥራ ምክንያት የደረሰ ጉዳት/አደጋ መሆን አለበት፡፡ በ ሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ/ጉዳት መንስኤ የተለያየ ነው፡፡ በዚህ ዓምድ የተፈለገው ልጆች ከዕድሜአቸው ወ ይም ከአቅማቸው በላይ የአዋቂ ጉልበት የሚጠይቅ ሥራ እንዲሠሩ በመደረጋቸው ወይም በመሥራታቸው ምክንያት የሚደርሰው ጉዳት/አደጋ ዓይነት ነው፡፡ ለምሳሌ ዕድሜው በሬ ጠምዶ ለማረስ ሳይደርስ በእርሻ

ሥራ ላይ በመሰማራቱ ማረሻው እግሩን ወግቶት በመጎዳቱ ወይም እርፉን ተቆጣጥሮ ለመጨበጥ የሚያስችል አቅም በማጣቱ ወድቆ በመሰበሩ፣ ...ወዘተ የደረሰ ጉዳት/አደጋ ከሥራው ጋር እየተገናዘበ በመረጃ ሰጪው ድጋፍ የተፈለገው መረጃ መገኘት አለበት። ይህም ሲሆን ጥቃቅንና ቀላል ጉዳቶች ጎልተው እንዳይመዘገቡ መጠንቀቅና እንዲህ ዓይነት ጉዳቶች እንደ ጉዳት ሊወሰዱ እንደማይገባቸው ግልጽ መሆን አለበት።

<u>ማስታወሻ፡</u> ለዚህ ጥናት ከባድ ጉዳት የሚባለው ዘወትር ከሚያከናውኑት ተግባር ቢያንስ ለ1 ወር ያህል ከስራ ያስተጓጎለ ከሆነ ነው። ጉዳቱ ከ1 ወር በታች ከስራ ያስተጓጎለ ከሆነ እንደ መጠነኛ ጉዳት ሊወሰድ ይችላል። ሆኖም ለ1 ቀን ከስራ የሚያግድ ከሆነ እንደ ቀላል ጉዳት ተቆጥሮ «አልደረሰብኝም» የሚል ተመዝግቦ ትክክለኛ ኮድ ይሞላል።

## ዓምድ 66 <u>ወላጅ እናትህ/ሽ በሕይወት አሉ ?</u>

በዚህ ዓምድ ዕድሜያቸው ከ5-14 ዓመት የሆኑ ልጆች በሙሉ ወላጅ እናታቸው በሕይወት እንዳሉና እንደሌሉ ተጠይቀው በሕይወት ካሉ በካርድ ኮለሙ ኮድ «1» ይሞላላቸዋል። በሕይወት ከሌሉ በካርድ ኮለሙ ኮድ «2» ይሞላላቸዋል።

## ዓምድ 67 <u>ወላጅ አባትህ/ሽ በሕይወት አሉ ?</u>

በዚህ ዓምድ ዕድሜያቸው ከ5-14 ዓመት የሆኑ ልጆች በሙሉ ወላጅ አባታቸው በሕይወት እንዳሉና እንደሌሉ ተጠይቀው በሕይወት ካሉ በካርድ ኮለሙ ኮድ «1» ሲሞላላቸው በሕይወት ከሌሉ ግን በካርድ ኮለሙ ኮድ «2» ይሞላላቸዋል።

## ዓምድ 68 <u>ከማን ጋር ነው የምትኖረው/ሪው?</u>

ዕድሜያቸው ከ5-14 ዓመት ያሉ ልጆች እያንዳንዳቸው ከማን ጋር እንደሚኖሩ ተጠይቀው ከተሰጡት አማራጭ መልሶች ውስጥ አንደኛው ብቻ በዓምዱ ይመዘገባል፣ በካርድ ኮለሙም ተገቢው ኮድ ይሞላል። የኮዶቹም ዝርዝር ከዚህ በታች ተገልጿል።

1= <u>ከእናትና ከአባቴ ጋር፡-</u> ቤተሰቡ በትዳር ላይ ያሉና ከእናትና ከአባቱ ጋር የሚኖር፣

2= <u>ከአባቴ ጋር፡-</u> እናቱ በፍቺ፣ በሞት ወይም በሌላ ምክንያት ከአባቱ ጋር የማትኖርና ልጁ ከአባቱ ጋር የሚኖር ከሆነ፣

3= <u>ከእናቴ ጋር፡-</u> አባቱ በፍቺ፣ በሞት ወይም በሌላ ምክንያት ከእናቱ ጋር የማይኖር ልጁ ከእናቱ ጋር የሚኖር ከሆነ፣

4= <u>ከሌሎች ዘመዶች ጋር፡-</u> ዘመድ ካልሆኑ እንደ ጓደኛ ከመሳሰሉት ጋር የሚኖር ከሆነ፣

5= <u>ከአሠሪ ጋር (ዘመድ ያልሆነ)፡-</u> በቀጥር ከሚሠራበት ቤት ወይም ከአሠሪው ቤት ወይም ድርጅት ውስጥ የሚኖር ከሆነ፣

6= <u>ለብቻ ራሴን ችዬ፡-</u>

7 = <u>ሌላ (ይገለፅ)፡-</u> ከላይ ከተገለፁት ውጭ ከሆነ፣

## ዓምድ 69 <u>እናትና አባትህ/ሽ በትዳር ላይ ናቸው?</u>

ዕድሜአቸው ከ5-14 የሆኑ ልጆች እናትና አባታቸው በትዳር ላይ መሆንና አለመሆናቸው ተጠይቆ በትዳር ላይ ካሉ ኮድ «1» ሲሞላላቸው ከተፋቱ ወይም ከተለያዩ ደግሞ ኮድ «2» በካርድ ኮለሙ ይሞላላቸዋል። ወላጆቻቸው በትዳር ላይ መሆንና አለመሆናቸው ለማያውቁ ልጆች ማለትም «አላውቅም» የሚለው ኮድ «3» በኮርድ ኮለሙ ይሞላላቸዋል። በሌላ በኩል ከወላጆቻቸው አንዳቸው ወይም ሁለቱም በሕይወት ለሌሉ ልጆች አይመለከታቸውም የሚለው ኮድ "4" ይሞላላቸዋል። በዚህ ጥያቄ እናት/አባት በሚባልበት ጊዜ

ወላጅ እናት/አባት እንጂ እንደ እናት/አባት ሆነው የሚያሳጉትን እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በመ ሆኑም በአንዳንድ ቤተሰብ ወላጅ ሳይሆኑ ራሳቸውን እንደ አባት/እናት በመቁጠር ወይም አለመሆናቸው ሲ ጠየቅ ሊያስቆጣቸው ስለሚችል ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ መረጃ ሰብሳቢው አጠራጣሪ ሁኔታዎችን አጣር ቶ መረጃውን መሙላት ይገባዋል፡፡

# ምዕራፍ 6 በከተማና በገጠር የሚጠኑ የናሙና ቤተሰቦች አመራረጥ ዘዴ

## በከተማ

በቆጠራ ቦታው ውስጥ ያሉት ቤተሰቦች ምዝገባ በተሟላ ሁኔታ መጠናቀቁን ማለትም ቤተሰቦች ሳይዘለሉ ወይም ሳይደገሙ መመዝገባቸውና የተመዘገቡትም የቤተሰብ ተራ ቁጥር ተከታታይ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ 35 ናሙና ቤተሰቦች ይመረጣሉ።

እነዚህ 35 ቤተሰቦች የሚመረጡት በሚከተለው አኳኋን ይሆናል። በቆጠራ ቦታው ውስጥ ከተመዘገቡት ጠቅላላ የመደበኛ ቤተሰቦች ብዛት ማለትም በመመዝገቢያ ቅፅ 91/0 ከተማ ክፍል 2 ዓምድ 11 የመጨረሻውን የቤተሰብ ተከታታይ ተራ ቁጥር በመውሰድ ለ35 ይካፈላል። በዚህ ስሌት የተገኘው ቁጥር «ኢንቲጀር» ካልሆነ ክፍልፋዩን ትቶ ሙሉ ቁጥር ይወሰዳል። ይህ ቁጥር «መ» ነው እንበል። ከዚህ በኋላ «መ»ን በመያዝ የራንደም ሠንጠረዥ በመጠቀም ከ1-መ ካሉት ቁጥሮች መካከል /«1» እና «መ»ን ጨምሮ/ በመጀመሪያ የተገኘው ቁጥር ይመረጣል። ይህም የተመረጠው ቁጥር በመጀመሪያ የተመረጠውን ቤተሰብ ያመለክታል። በዚህ መሠረት ቤተሰቡ መጀመሪያ መመረጡን ለማመልከት በመመዝገቢያ ቅፅ 91/0 ክፍል 2 ዓምድ 11 የቤተሰብ ተራ ቁጥር ይከበብና በዚህ ቅፅ ክፍል 2 ዓምድ 13 በተመረጠው ቤተሰብ አንፃር «01» ተብሎ ይጻፋል።

በሁለተኛ ደረጃ የሚመረጠውን ቤተሰብ ለማግኘት በመጀመሪያ ለተመረጠው ቤተሰብ በዓምድ 11 የተከበበው ተራ ቁጥር ላይ «መ» ይደመራል የሚገኘውን ቁጥር በዓምድ 11 ከተዘረዘሩት ተራ ቁጥሮች የያዘው ቤተሰብ ተራ ቁጥር ይከበብና በዓምድ 13 «02» ይፃፋል። ይህ አሰራር 35ቱም ቤተሰቦች እስኪመረጡ ይቀጥላል ማለት ነው።

<u>ምሳሌ</u>፦ አንድ በዚህ ጥናት በተመረጠ የቆጠራ ቦታ የተመዘገቡ ቤተሰቦች
ጠቅላላ ብዛት/ዓምድ 11 የመጨረሻ ተራ ቁጥር/125 ቢሆን፦
መ = 125/35 = 3.57

ከነጥብ በኋላ ያለው ቁጥር ይተውና መ = 3 ተብሎ ይወሰዳል። የራንደም ቁጥር ሠንጠረዥ በመጠቀም ከ1-3 ካሉት ቁጥሮች ውስጥ በቅድሚያ የተገኘው ቁጥር ይመረጣል። ይህን በማድረግ የተገኘው ቁጥር 02 ቢሆን በመጀመሪያ የተመረጠው ይህን ቁጥር የያዘው በዓምድ 11 ላይ 002 የቤተሰብ ተራ ቁጥር የተሰጠው ቤተሰብ ይሆናል ማለት ነው። 002 የቤተሰብ ተራ ቁጥር በዓምድ 11 ይከበብና በአንፃሩ በዓምድ 13 «01» ይጻፋል።

በሁለተኛ ደረጃ የሚመረጠው ቤተሰብ ደግሞ 02+3 =
05 በስሌቱ መሠረት በዓምድ 11 አምስተኛ ተከታታይ ተራ ቁጥር የያዘው ቤተሰብ ይሆናል ማለት ነው። ይህ ቁጥር በዓምድ 11 ይከበብና በአንፃሩ በዓምድ 13 «02» ይፃፋል። ይህ አሠራር ሰላሳ አምስቱም ቤተሰቦች እስኪመረጡ ድረስ ይቀጥላል።

## ለገጠር

ለገጠር ሰው ሃይል ጥናት የናሙና ቤተሰቦችን ለመምረጥ የሚያገለግለው መመዝገቢያ ቅጽ ቀደም ብሎ በግብርና ናሙና ጥናት የተዘጋጀ ሲሆን ቅጹም መመዝገቢያ ቅጽ 90/0 ነው። የሚመረጡት ቤተሰቦች ብዛት 35 ናቸው። በመመዝገቢያ ቅጽ 90/0 ክፍል 2 ዓምድ 1 የመጨረሻውን የቤተሰብ ተራ ቁጥር በመውሰድ ለ35 ይካፈላል። በዚህ ስሌት የተገኘው ቁጥር (ኢንቲጀር) ካልሆነ ክፍልፋዩን በመተው ሙሉ ቁጥር ይወሰዳል። ይህ ቁጥር «መ» ነው እንበል። ከዚህ በኋላ «መ»ን በመያዝ የራንደም ሠንጠረዥ በመጠቀም ከ1-መ ካሉት ቁጥሮች መካከል /«1» እና «መ»ን ጨምሮ/ በመጀመሪያ የተገኘው ቁጥር ይመረጣል። ይህም የተመረጠው ቁጥር በመጀመሪያ የተመረጠውን ቤተሰብ ያመለክታል። በዚህም መሠረት ቤተሰቡ መጀመሪያ መመረጡን ለማመልከት በመመዝገቢያ ቅፅ 90/0 ክፍል 2 ዓምድ 1 የቤተሰብ ተከታታይ ተራ ቁጥር ይከበብና በዚህ ቅፅ ክፍል 2 ዓምድ 10 (ለሰው ኃይል ጥናት አመራረጥ ቅደም ተከተል) ከተመረጠው ቤተሰብ አንፃር «01» ተብሎ ይፃፋል።

በሁለተኛ ደረጃ የሚመረጠውን ቤተሰብ ለማግኘት በመጀመሪያ በተመረጠው ቤተሰብ በዓምድ 1 የተከበበው ተራ ቁጥር ላይ «መ» ይደመርና የሚገኘውን ቁጥር በዓምድ 1 ከተዘረዘሩት ተራ ቁጥሮች የያዘው ቤተሰብ ተራ ቁጥር ይከበብና በዓምድ 10 «02» ይፃፋል። ይህ አሠራር 35ቱም በጥናቱ የሚሸፈኑ ቤተሰቦች እስኪመረጡ ድረስ ይቀጥላል። ለተጨማሪ ማብራሪያ ለከተማ አመራረጥ ቅደም ተከተል የተሰጠውን ምሳሌ ይመልከቱ።

የገጠር መመዝገቢያ ቅፅ ከተሠራ 6 ወራት ያለፋት በመሆኑ የተወሰኑ ቤተሰቦች በሰው ሃይል ጥናት ወቅት በቆጠራ ቦታው ጨርሰው ላይገኙ ይችላሉ። በመሆኑም በናሙና ምርጫው ውስጥ እነዚህ ቤተሰቦች ሊመረጡ ስለሚ ችሉ ተጨማሪ 3 ቤተሰቦች በተጠባባቂነት ይመረጣሉ። የአመራረጡም ዘዴ የመጨረሻው (35ተኛ) የተመረጠ ቤተሰብ ተራ ቁጥር ላይ «መ» በመደመር የተገኘውን ቁጥር ዓምድ 1 ከተዘረዘሩት ቁጥሮች የያዘው ቤተሰብ ተራ ቁጥር ይ ከበብና በዓምድ 10 «36» ይፃፋል። ሆኖም የተገኘው ድምር በዓምድ 1 ላይ ከተፃፈው የመጨረሻ ተከታታይ የቤተ ሰብ ተራ ቁጥር ከበለጠ ወደ መጀመሪያው ገጽ መመለስ ያስፈልጋል። ይህ አሠራር ለ3ቱም በተጨማሪ ለሚመረጡት ተጠባባቂ ቤተሰቦች ይከናወናል።

<u>ማሳሰቢያ</u> ለገጠር የናሙና ምርጫ የሚካሄደው በስልጠና ወቅት ነው። በዚህም ጊዜ በጽ/ቤቱ ኃላፊ አማካይነት ተ ቆጣጣሪዎች በስራቸው ላሉ ቆጠራ ቦታዎች በተሰጠው የአመራረጥ መመሪያ መሠረት ምርጫውን በዚህም ገ ‹ዜ በጽ/ቤቱ ኃላፊ አማካይነት ተቆጣጣሪዎች በስራቸው ላሉ ቆጠራ ቦታዎች በተሰጠው የአመራረጥ መመሪ ያ መሠረት ምርጫውን በማድረግ የተመረጡ ቤተሰቦችን ዝርዝር ለሚመለከታቸው መረጃ ሰብሳቢዎች ያሳ ያሉ። መረጃ ሰብሳቢዎችም የተመረጡ ቤተሰቦችን ዝርዝር ከቅጽ 90/0 ወደ ቅጽ 91/1 ያወራርሳሉ። ስለሆ ነም እያንዳንዱ መረጃ ሰብሳቢ ወደተመደበበት የገጠር የቆጠራ ቦታ ከመሥማራቱ በፊት የተመረጡትን የና ሙና ቤተሰቦች ዝርዝር መያዙን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

ምርጫው እንደተጠናቀቀም ምዝገባውን ያካሄደው መረጃ ሰብሳቢ፣ የመስክ ሥራ ተቆጣጣሪና የቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ስታቲስቲክስ ኃላፊ ስለ ሥራው ትክክለኛነት ስማቸውን፣ ፊርማቸውንና ሥራው የተጠናቀቀበት ቀን በተሰጠ ው ቦታ ማስፈር አለባቸው።

# *እዝል 1 የዋና ዋና የታሪካዊ ድርጊቶች ዝርዝር*

| ተራ ቁጥር | ታሪካዊ ድርጊቶች | ድርጊቱ የተፈጸመበት ዓመተ ምሕረት | ድርጊቱ ከተፈጸመበት እስከ 1991 ዓ.ም. ያሉት ዓመታት ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በጋራ ሙለታ ደጃዝማች ተብለው የ ተሾሙበት | 1897 | 94 |
| 2 | ልዑል ራስ መኮንን ያረፉበት | 1898 | 93 |
| 3 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሲዳሞ የተሾሙበት | 1900 | 91 |
| 4 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐረርጌ የተሾሙበት | 1902 | 89 |
| 5 | አጼ ምኒልክ ያረፉበት (ልጅ ኢያሱ የነገሱበት) | 1906 | 85 |
| 6 | ራስ ሚካኤል በወሎ፣ በትግሬና በጎጃም የነገሱበት | 1907 | 84 |
| 7 | ንግሥት ዘውዲቱ የነገሱበት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አልጋ ወራሽ የሆኑበት | 1909 | 82 |
| 8 | የሰገሌ ጦርነት የተካሄደበት | 1909 | 82 |
| 9 | እቴጌ ጣይቱ ያረፉበት | 1910 | 81 |
| 10 | የኅዳር በሽታ የነበረበት | 1911 | 80 |
| 11 | ልጅ ኢያሱ የተያዙበት | 1913 | 78 |
| 12 | ኢትዮጵያ የዓለም መንግሥታት ማኅበር አባል የሆነችበት | 1916 | 75 |
| 13 | የባሪያ ነጻነት ደንብ የወጣበት | 1916 | 75 |
| 14 | ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት የተቋቋመበት | 1917 | 74 |
| 15 | ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ያረፉበት | 1918 | 72 |
| 16 | አቡነ ማቴዎስ ያረፉበት | 1919 | 72 |
| 17 | ንግሥት ዘውዲቱ ያረፉበት | 1922 | 69 |
| 18 | ራስ ጉግሳ ወሌ በጎንደር የሞቱበት | 1922 | 69 |
| 19 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የነገሱበት | 1923 | 68 |
| 20 | የወልወል ግጭት የተደረገበት | 1927 | 64 |
| 21 | የማይጨው ጦርነት የተካሄደበት ኢጣሊያ ወደ ኢትዮጵያ የገባችበት | 1928 | 63 |
| 22 | የኢትዮጵያ ሰማዕታት ቀን | 1929 | 62 |
| 23 | በጂማ ገነቴ ላይ የአርበኞች ውጊያ የተደረገበት | 1930 | 61 |

| ተራ ቁጥር | ታሪካዊ ድርጊቶች | ድርጊቱ የተፈጸመበት ዓመተ ምሕረት | ድርጊቱ ከተፈጸመበት እስከ 1991 ዓ.ም. ያሉት ዓመታት ብዛት |
|---|---|---|---|
| 24 | እንግሊዝ ኢጣልያን ከኢትዮጵያ ለማስወጣት የመጣበት | 1933 | 58 |
| 25 | ኢጣሊያን ድል የተመታችበት | 1933 | 58 |
| 26 | ለኢትዮጵያ ሰማዕታት ሀውልት የተሰራበት | 1937 | 54 |
| 27 | አቡነ ባስሊዎስ ሊቀ ጳጳስ የሆኑበት | 1943 | 48 |
| 28 | ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን የተዋሃደችበት | 1943 | 48 |
| 29 | የሸንቁጤ ረሀብ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የገባበት | 1950 | 41 |
| 30 | እነጀኔራል መንግሥቱ ነዋይ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ለመፈንቀል ሙከራ ያደረጉበት | 1953 | 38 |
| 31 | ኤርትራ ከኢትዮጵያ የተዋሐደችበት | 1955 | 36 |
| 32 | የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የተቋቋመበት | 1955 | 36 |
| 33 | ኮሌራ በሽታ የገባበት | 1963 | 28 |
| 34 | የኢትዮጵያ አብዮት የፈነዳበት | 1966 | 25 |
| 35 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን የወረዱበት | 1967 | 24 |
| 36 | የዕድገት በሕብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ | | |
| | በዓል የተከበረበት | 1967 | 24 |
| 37 | የገጠርን መሬት የመንግሥት ያደረገው አዋጅ የታወጀበት | 1967 | 24 |
| 38 | የከተማ ቦታ እና ትርፍ ቤት የመንግሥት ያደረገው አዋጅ የታወጀበት | 1967 | 24 |
| 39 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ያረፉበት | 1967 | 24 |
| 40 | ኢ.ሠ.ፓ.አ.ኮ. የተመሠረተበት | 1972 | 19 |
| 41 | የመጀመሪያው የሕዝብና ቤት ቆጠራ የተካሄደበት | 1976 | 15 |
| 42 | የኢ.ሠ.ፓ. ምሥረታና የ10ኛው አብዮት የተከበረበት | 1977 | 14 |
| 43 | የግንቦት 8 መፈንቅለ መንግሥት | 1981 | 10 |
| 44 | ኢሕአዴግ አዲስ አበባን የተቆጣጠረበት | 1983 | 8 |
| 45 | ሁለተኛው የሕዝብና ቤት ቆጠራ የተካሄደበት | 1987 | 4 |